## ክረምት እና ጥንቃቄ የሚሹ የጤና እክሎች

ገጽ 8



## "ልጄን አደራ! '

ገጽ 18




# አዲስ ዘመን

አፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 294 ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡ ፎቶ አጋፔ ገዮን

# "ጊዜው የሚጠይቀን የሀገር ወዳድነት ዓይነት በሥራ የሚገለጽ ነው"

ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል
የሥራና ክህሎት ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ጊዜው የሚጠይቀው የአገር ወዳድነት አይነት በሥራ የሚገለጽ ነው ሲሉ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ገለጹ። "ብቁ" የተሰኘ የሥራ ገበያ የመረጃ ሥርዓት መተግበሪያ ይፋ ሆኗል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር "ምርታማነት" ላይ ትኩረት አድርጎ ትላንት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ባካሄደው የምክክር መድረክ ላይ ሚኒስትሯ ባደረጉት ንግግር፤ ድህነትን የሚያሸንፍና የሚጠየፍ ብቻ ሳይሆን ዕድሎችን አውጥቶ ነባራዊ ሁኔታ የሚጠይቀውን አገር ወዳድነትን የመፍጠር ሥነ ልቡና ያለው ዜጋ ያስፈልጋል ብለዋል። ዜጎችን ብቁና ተወዳዳሪ ማድረግ፤ ቀጣዩን አሻግሮ የሚመለከትና ለሀገር የሚበቃ ትውልድ ማፍራት እንደሚገባም ገልጸዋል።

"ጊዜው የሚጠይቀን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በፌዴራል መንግሥት ለክልሎች የሚሰጠው በጀትና ድጎማ በፌዴራል ዋና ኦዲተር ስር ኦዲት ሊደረግ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ከቀጣይ ዓመት ጀምሮ ሁሉንም ክልሎች ከፌደራል መንግሥት የተሰጣቸውን በጀትና ድጎማ መሠረት በማድረግ በዋና ኦዲተር ስር ኦዲት ለማድረግ እንደሚሠራ ተገለጸ።

ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ ሰኔ 20 ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበውን ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አስመልክቶ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት እስካሁን የክልል ዋና ኦዲተሮች በየክልላቸው ምክር ቤት የተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የኦዲት ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል ።

ኦዲቱም የሚሠራው የፌደራል መንግሥት መመሪያና ደንብን መሠረት በማድረግ ሳይሆን የየክልሎቹን መሠረት በማድረግ በመሆኑ ተጠያቂነት ሲኖርም ጉዳዩ የሚታየው በክልሉ ነው ያሉት ወይዘሮ መሠረት፤ ለቀጣይ ግን ለተጠያቂነት በሚመች መልኩ ገንዘብ ሚኒስቴር ብሩን ሲለቅ ክልሎች ከራሳቸው ገቢ ለይተው እንዲመዘግቡና ለይተው ሪፖርት እንዲያቀርቡም ከስምምነት ላይ ተደርሷል ብለዋል ።

ክልሎች ከፌደራል መንግሥት የሚሰጣቸውን በጀት ሲጠቀሙ በየምክር ቤታቸው በማጽደቅ ከራሳቸው ገቢ ጋር ደርበው በመቀላቀል ነው። በመሆኑም ይህንን

በፌዴራል መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ








# ‹‹ለሀገር ሉዓላዊነት መረጋገጥ በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት ላይ መድረስ ይጠይቃል››

አቶ ብናልፍ አንዷለም
የሰላም ሚኒስትር

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ለሀገር ሉዓላዊነት መጠበቅ፣ለሕዝቦች ሰላምና ደህንነት በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት ደርሶ የጋራ አቋም የመያዝ ባሕልን ለማዳበር ርብርብ ማድረግ እንደሚገባ የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም ገለጹ፡፡

ሚኒስትሩ ‹‹ሀገራዊ እሴቶች ለብሔራዊ መግባባት›› በሚል መሪ ሀሳብ የሰላም ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት

‹‹ለሀገር ሉዓላዊነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በሦስት ክልሎች ከ8 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ተፈናቃዮች 4 ሚሊዮን ኩንታል የምግብ ድጋፍ ተደርጓል

ገጽ 4




# የበግ ዝርያን በማሻሻል የአርቢውን ማኅበረሰብ ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው

**ምሕረት ሞገስ**



ደብረ ማርቆስ፡- የማኅበረሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ እና አሳታፊ የበግ ዝርያን በማሻሻል የአርቢውን ማኅበረሰብ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የደብረ ማርቆስ ግብርና ምርምር ማዕከል አስታወቀ።

ሰሞኑን የዋሸራ በግ ዝርያ ለማሻሻል ከማኅበረሰብ ጋር በመተባበር የተሠራ ሥራ ላይ ያተኮረ የመስክ ጉብኝት ሲካሄድ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር አቶ ያለው ማዘንጊያ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ 14 የሚደርሱ የበግ ዝርያዎች መኖራቸውን እና ከበግ ዝርያዎች መካከል አንዱ የሆነው የዋሸራ ዳንግላ በግ ዝርያ በዋናነት በኢትዮጵያ ካሉ የበግ ዝርያዎች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ መሆኑ ተጠቁሟል።

የዋሸራ በግ ዝርያ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ የሥጋ ገበያ ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረው የበግ ዝርያ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ያለው፤ በምዕራብ ጎጃም፣ ምሥራቅ ጎጃም እና አዊ ዞኖች እንዲሁም በመተከል ዞንና በደቡባዊ የጣና ሐይቅ አካባቢዎች በስፋት ተሰራጭቶ የሚገኝ የበግ ዝርያ መሆኑን አብራርተዋል።

የዋሸራ በግ ዝርያን ማሻሻል አርቢውን በዘላቂነት የኑሮ ሁኔታውን ከማሻሻል ባለፈ ለአካባቢው ብሎም ለሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ለወጪ ንግድ ከፍተኛ አስተዋፅ ያበረክታል ብለዋል። ይህንንም እውን ለማድረግ የደብረ ማርቆስ ግብርና ምርምር ማዕከል ማኅበረሰብ አቀፍ የዋሸራ/ዳንግላ በግ ዝርያ ማሻሻል ሥራን በዳንጉሌ እና ጠለዛሞ ቀበሌዎች የአርቢዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ከሚመለከታቸው ጋር ተባብሮ በማቋቋም ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ አካባቢው የዋሸራ ዳንግላ በግ ዝርያ ምንጭ እንዲሆን ወደ ሥራ መግባቱን ገልፀዋል።

ዝርያዎች የየራሳቸው ጥሩ ባሕሪ ያላቸው ሲሆን፤ ለዘመናዊ የበግ ዝርያ ማሻሻል ሰፊ ዕድልን የሚሰጥ መሆኑን ጠቁመው፤ የዋሸራ በግ ዝርያ በአማካይ በውልደት ጊዜ 2 ነጥብ 8 ፣ በጡት መንጠፍ ጊዜ 13 ነጥብ 8 እና በስድስት ወር 17 ነጥብ 87 ኪሎ ግራም በአንድ ዓመት 23 ነጥብ 47 አካባቢ እንደሚሆኑ ገልፀዋል። ሴቶቹ በአንድ ዓመት ውስጥ ለመውለድ ብቁ ሆነው የጠራ ዘር የሚገኝበት ሁኔታም ማመቻቸት መቻሉን ገልፀዋል።

ዘሩን የማሻሻል ሥራ ከመጀመሩ በፊት እየተዳቀለ ለመጥፋት ጥቂት ቀርቶት እንደነበር አስታውሰው፤ ማኅበረሰቡ እና የምርምር ማዕከሉ ተግባብተው በትብብር በመሥራታቸው በአካባቢው ከጥንት ጀምሮ አካባቢውን ተላምዶ የቆየውን የዋሸራ በግ ዘር የጠራ ማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል።

በምሥራቅ ጎጃም ዞን በስናን ወረዳ የዳንጉሌ ቀበሌ ነዋሪው አርሶ አደር ባለው ወንዴ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በማኅበር ተደራጅተው የምርምር ማዕከሉ የሰጣቸውን አውራ በግ ተጠቅመው የአካባቢውን በግ ዘር በማሻሻል የተሻለ ገቢ ማግኘት ችለዋል።

የዋሸራ በጎች በዓመት ሁለት ጊዜ አንዳንዴም በስድስት ወር መንታ ግልገል እየወለዱ፤ የተወለዱትም በሦስት ወር ግልገል ሆነው ለመሸጥ እየደረሱ ለሚማሩ ልጆቻቸው የሚልኩት ገንዘብ ሲያጥራቸው በመሸጥ ገቢ እያገኙ መሆኑን ጠቁመዋል። በጎቹ ዓመት ከቆዩ በኋላ ዳብረው ከሌላው የበግ ዝርያ የተሻለ ክብደት ስለሚኖራቸው በገበያ ላይ በበዓላት ሰሞን በተሻለ ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩንም አብራርተዋል።

በጉብኝቱ ላይ ማኅበረሰብ አቀፍ አገር በቀል የዋሸራ በግ ዝርያ የማሻሻል ሥራ ሲከናወን፤ የተደራጀና ተከታታይነት ያለው የእንስሳት መለየትና የአፈፃፀምና መረጃዎችን የመመዝገብ ሥራ በተገቢው መልኩ መከናወኑ ተገልጿል። የዝርያ ማሻሻል መርሐግብሮችን ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣ አቅምን ለመገንባት እና በተሳታፊዎች መካከል ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ሥራው ዘላቂ እንደሚሆንም ተጠቁሟል።





አቶ ሳሙኤል ኡርቃቶ

## የሙስና ወንጀልን ለመዋጋት በሕግ ማዕቀፍ ሥርዓት መዘርጋት ይገባል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የሙስና ወንጀልን በሕግ ማዕቀፍ ሥርዓት ዘርግቶ መዋጋት አስፈላጊ መሆኑን የኢፌዴሪ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ገለጸ።

የኢፌዴሪ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ያዘጋጀውን የጥቅም ግጭት መከላከል ረቂቅ ደንብ ለአስፈፃሚና ለሚመለከታቸው አካላት በትናትናው ዕለት አቅርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

የኢፌዴሪ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ በመርሐ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ በተለያዩ ዘርፎች እየተፈጸመ ያለ ሙስና አስከፊ በመሆኑ ወንጀሉን ለመከላከል በሕግ ማዕቀፍ መሥራት ያስፈልጋል።

በጥቅማጥቅም በመታለል የመንግሥት አመራሮች ሀብት እንዳያባክኑ አስቀድሞ ለመከላከል ረቂቅ ደንቡ ትልቅ ሚና ይጫወታል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ደንቡ በአቋራጭ የሕዝብ ንብረትን ያለአግባብ በመመዝበር ሀብትን ለማጋበስ የሚሮጡ አንዳንድ የአመራር ሌቦችን በሕግ ማዕቀፍ መታገል እንደሚያስችል ጠቁመዋል። ረቂቁ ወደ ሥራ ሲገባም ማኅበረሰቡ ከመንግሥት ተቋማት ማግኘት የሚገባውን ጥቅምና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል መሆኑንም አብራርተዋል።

የሥነ ምግባር መርሆዎች በተጠያቂነት በመተግበር ተጠያቂነትንና ግልጸኝነት እንዲሰፍን ደንቡ ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለፃ፤ መንግሥት ሙስናን ከሀገር ለማጥፋት ትልቅ ሥራ እየሠራ ነው። ሙስና በማጥፋት መንግሥት በምቹ ሁኔታ ከሕዝብ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣና ሕዝባዊ ቅቡልነት እንዲኖረው ወንጀሉን በሕግ ማዕቀፍ ሥርዓት ዘርግቶ መዋጋት ያስፈልጋል። ለዚህም ረቂቅ ደንቡ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

ሙስናን መከላከልን ሕዝባዊ ጉዳይ እናደርገዋለን ያሉት ኮሚሽነሩ፤ አመራሩ በየደረጃው የመንግሥት መርሕን በመከተል ሙስናን ሊታገል ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ዳባ፤ የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣኖች የሀገሪቱን ሀብት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸው፤ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ የሀገር ውስጥ ሕጎችንና የዓለም አቀፍ የሕግ ስምምነቶችን አገናዝቦ የተዘጋጀ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ደንቡ መልካም አስተዳደርን በማጎልበት መንግሥት ሙስናን ለመከላከል የሚያደርገውን ከፍተኛ ጥረት የሚያግዝ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ረቂቅ ደንቡ የሀገርን ሀብት ከሙስና በመከላከልና የጥቅም ግጭትን በመቅረፍ የሀገርን ሰላም፣ ልማትና እድገትን የሚያፋጥን መሆኑን አስገንዝበዋል።

ረቂቅ ደንቡ ሁለት ዓመት ጥናትና የተለያዩ ውይይቶች እንደተደረጉበት ገልጸው፤ የተነሱ አስተያየቶች ተካተው በቀጣይ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚቀርብ አመላክተዋል።

ሙስና በሀገር ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ እድገት ላይ አሉታዊ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ በሕግ ማዕቀፍ መከላከል ይገባል ያሉት ደግሞ ምክትል ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው ናቸው።

የሙስና ወንጀልን በቀጣይነትና በወጥነት ለመከላከል ረቂቅ አዋጁ ትልቅ ፋይዳ አለው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ወጥ የሆነ ለውጥ ለማምጣት የሕግ ማዕቀፍ ሥርዓትን ለመዘርጋት እንሠራለን ሲሉ ጠቁመዋል።

# ስምንት ሚሊዮን ወጣቶች በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ይሳተፋሉ

## - ንቅናቄው ዛሬ በአሶሳ ከተማ ይጀመራል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የወጣቶች የክረምት በጎ ፈቃድ ንቅናቄ ስምንት ሚሊዮን ወጣቶች እንደሚሳተፉ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስታወቀ።

የሊጉ ምክትል ፕሬዚዳንትና የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ወጣት አበንግ ኩመዳን በሰጠችው መግለጫ፤ ንቅናቄው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ እንደሚጀመርና ስምንት ሚሊዮን በላይ ወጣቶች እንደሚሳተፉ ገልጻለች።

በዘንድሮው የክረምት ወቅት ወጣቱ በተለያዩ አገልግሎቶች በመሳተፍ አሻራውን እንዲያሳርፍ ዝግጅቶች ተደርገዋል ያለችው ኃላፊዋ፤ ለዚህም ዛሬ የንቅናቄው ማስጀመሪያ መርሐ ግብር በአሶሳ ይካሄዳል ብላለች።

በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከ400 ሚሊዮን በላይ ችግኝ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመትከል መታቀዱንና ከሚተከሉት ችግኞች አብዛኛዎቹ ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች መሆናቸውን ወጣት አበንግ ገልፃለች።

የሊጉ ምክትል ፕሬዚዳንት ወጣት ፈዲላ ቢያ በበኩሏ፤ በመርሐ ግብሩ በአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ በጤና ተቋማት ለሕሙማን ድጋፍ፣ የደም ልገሳ እና ለዓባይ ግድብ የቦንድ ግዥን ማካሄድ ላይ ተሳትፎ እንደሚደረግ አስረድታ፤ በተጨማሪም አርሶ አደሮችን በእርሻ ሥራ በማገዝ፣ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ከቀያቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን በመርዳት እና በገጠር ለሚገኙ አቅመ ደካማ ቤተሰብ ልጆች የትምህርት ቁሳቁስ በመርዳት እንዲሁም በሌሎች ተግባራት እንደሚሳተፉ አስገንዝባለች ።

በተለይ የህዳሴ ግድቡ ለወጣቶች ትልቅ ትርጉም ያለው በመሆኑ በሁለት ወራት የክረምት ወቅት የቦንድ



ከግራ ወደቀኝ ወጣት ፈዲላ ቢያ እና ወጣት አበንግ ኩመዳን

ግዥ ንቅናቄ የሚካሄድበት እንደሆነ ወጣት ፈዲላ አስረድታለች። በዚህም ወጣቶቹ በቀጣይ ሁለት ወራት በበጎ ፍቃደኝነት የነቃ ተሳትፎ እንደሚኖራቸው ገልጻለች።

በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ የሚገኘው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ላይ በርካታ ወጣቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ጠቁማለች። ይህም ወጣቶች በሀገራቸው የልማትና የማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በበጎ ፍቃደኝነት በመሳተፍ ብዙ ገንዘብ ማዳን የሚቻልበት እንደሆነ ጠቅሳለች።

በዘንድሮ የክረምት የበጎ ፈቃድ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ወጣቶች ቁጥር ባለፈው ዓመት ከነበረው አንጻር ጭማሪ ማሳየቱን የተናገረችው ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ በዚህም ወጣቶች በበጎነት ጊዜያቸውን ለሀገራቸው በመስጠት ኢትዮጵያ የምታልመውን ብልጽግና እውን ለማድረግ ሚናቸው የላቀ መሆኑን አብራርታለች።

መላው የኢትዮጵያ ወጣቶች በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ንቅናቄ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ሊጉ ጥሪ አቅርቧል።

ዜና

# የዘመናት ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ በማግኘቱ መደሰታቸውን የሰበታ ሐዋስ ነዋሪዎች ገለጹ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የዘመናት የልማት ጥያቄያቸው አፋጣኝ ምላሽ በማግኘቱ እንደተደሰቱ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የሰበታ ሐዋስ ወረዳ ነዋሪዎች ገለጹ።

ባለፈው ሐሙስ በዞኑ በ105 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገነቡት የአጤ በላ ድልድይና የአዋሽ መልካ ኩንቱሬ የውሃ ፕሮጀክት የኦሮሚያ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ፣ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ የኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሥራ ኃላፊዎች የዞኑ ሥራ አመራሮችና ነዋሪዎች በተገኙበት ተመርቀው ሥራ ጀምረዋል።

የወረዳው ነዋሪዎች በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ዞኑ ምርታማ ቢሆንም ምርታቸውን ለገበያ ለማቅረብ ብሎም የመጠጥ ውሃ ችግር በመኖሩ ለዘመናት ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ ነበር። አሁን ላይ የ150 ዓመታት የልማት ጥያቄዎች አምስት ዓመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ማግኘቱ አስደስቷቸዋል።

አቶ ታቦር አንበሳ የሰበታ ሐዋስ ወረዳ ነዋሪ ሲሆኑ ወንዙ 6 የዞኑ ወረዳዎች ከሰበታ ከተማ ብሎም የአሁኑ ሸገር ከተማ ጋር እንደሚያገናኝና በተለይ በክረምት ወቅት ከልክ በላይ ስለሚሞላ ክረምቱ እስኪያልፍና ወንዝ እስኪቀንስ ዘመድ አዝማድ በጥቅሉ የዞኑ ነዋሪዎች ለመገናኘት ይቸገሩ እንደ ነበር አውስተዋል። በክረምት ወቅት በወንዙ የተወሰዱ ከብቶች ስፍር ቁጥር እንደሌላቸውም አክለዋል።


በጉርምስና እድሜያቸው ሲመኙ የነበረውን ወንዙን በድልድይ አደብ የማስገዛት ምኞች በሽምግልና እድሜያቸው ተሳክቶ ማየት እንዳስደሰታቸው በመግለጽ



ተማሪ አለምነሽ ከበደ



አቶ ሌሊሳ ቢጅጋ



አቶ ታቦር አንበሳ

መንግሥትንም አመስግነዋል።

"አባቶቻችን የልማት ጥያቄ አንግበው አዲስ አበባ ድረስ በመሄድ ይጠይቁ ነበር፤ ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ምላሽ አላገኙም" ያሉት ደግሞ አቶ ሌሊሳ ቢጅጋ ናቸው። እንደ እሳቸው ገለጻ፣ ዞኑ ምርታማ ቢሆንም ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ ከፍተኛ የመንገድ ችግር ነበር። ወደ ሰበታ ከተማ እንኳ ለመሄድ በተለይ በክረምት ወቅት ዙሪያ ጥምጥም ሲኬድ ሰውና እንስሳት በስፋት ይጎዱ ነበር። አጤ በላ ወንዝም እንስሳት ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም ሲወስድ እንደ ነበር ጠቁመዋል።

የወረዳው ችግር የመንገድ ብቻ ሳይሆን የውሃም ጭምር ሲሆን በተለይ ውሃ ከሩቅ ኪሎሜትር በማምጣት ረገድ የሴቶች ጫና እጥፍ ድርብ መሆኑን የምትናገረው ደግሞ ተማሪ አለምነሽ ከበደ ናት። መኖር ግድ ስለሆነ አብዛኛው ጊዜዋን የምታጠፋው በውሃ ፍለጋ እንደሆነና ችግሩ በትምህርት ላይ ጫና እንደ ነበረም አልሸሸገችም ።

አሁን ያ ከሩቅ ኪሎ ሜትር ውሃ ለማምጣት የሚባክን ጊዜ ተረት ሆኖ ውሃ ከደጃፋችን ለመቅዳት በቅተናል ስትል ደስታዋን ትገልጻለች።

# የኦሮሚያ ክልል 484 ሺህ የ8ኛና ከ323 ሺህ በላይ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለማስፈተን መዘጋጀቱን አስታወቀ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከ484 ሺህ በላይ የ8ኛ እና ከ323 ሺህ በላይ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለፈተና ማዘጋጀቱን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዶክተር ቡልቶሳ ሂርኮ የ8ኛ እና 12ኛ ክፍል ፈተናዎች ዝግጅትን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ በክልሉ የስምንተኛና የአስራ ሁለተኛ ክፍል ፈተናዎች በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄዱ የሚያስችል ዝግጅት በመደረግ ላይ ነው። ለዚህም ከ323 ሺህ በላይ የ12ኛ እና 484 ሺህ 994 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለፈተና ተመዝግበዋል።

እንደ ዶክተር ቡልቶሳ ገለጻ፤ በክልሉ የ8ኛ ክፍል ፈተና ለመውሰድ 484 ሺህ 994 ተማሪዎች ተመዝግበዋል። በዚህም ፈተናው በአንድ ሺህ 441 የፈተና ጣቢያዎች ላይ ሰኔ 26 እና 27 ቀን 2015 ዓ.ም ይሰጣል።

ተማሪዎች በዘጠኝ ሺህ 735 ትምህርት ቤቶች ላይ ሲማሩ መቆየታቸውን የገለጹት ዶክተር ቡልቶሳ፤ ፈተናውን ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ለማካሄድ እንዲቻል በአንድ ሺህ 441 የፈተና ጣቢያዎች ላይ ለመስጠት ዝግጅት ተደርጓል። በየደረጃው በሚገኙ የማኅበረሰብ አካላት ድጋፎችን በማድረግ ተማሪዎች ፈተናውን መውሰድ እንዲችሉ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በክልሉ ለ12ኛ ክፍል ፈተና በማኅበራዊ ሳይንስ 175 ሺህ 389 ተማሪዎች መመዝገባቸውን ጠቅሰው፤ 147 ሺህ 842 የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ተመዝግበዋል። በዚህም ከ323 ሺህ 231 ተማሪዎች ይፈተናሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

የ12ኛ ክፍል ፈተና በ22 ዩኒቨርሲቲዎች ይሰጣል ያሉት ዶክተር ቡልቶሳ፤ 17 በክልሉ



ዶክተር ቡልቶሳ ሂርኮ

በሚገኙና አምስት አጎራባች ክልሎች በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ፈተናው ይሰጣል። በዚህም በአሶሳ፣ በሀዋሳ፣ በወራቤ፣ በወልቂጤና በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ተፈታኝ ተማሪዎች መመደባቸውን አስረድተዋል።

ፈተናው ለማኅበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ከሐምሌ 19 እስከ 21 ቀን 2015 ዓ.ም የሚሰጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ የተፈጥሮ ሳይንስ ደግሞ ከሐምሌ 25 እስከ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ይሰጣል። ለዚህም ተገቢው ዝግጅትና የተማሪዎች ድልደላ መካሄዱን ዶክተር ቡልቶሳ ተናግረዋል።

ፈተናው የተሳካ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ወደ ትግበራ ተገብቷል። በዚህም ከባለፈው ዓመት ልምድ በመነሳት ፈተናውን ተማሪዎች አንዳች ችግር ሳይገጥማቸው ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።



# አስተዳደሩ ከሦስት ሺህ በላይ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሰጠ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታቸው ለተረጋገጠላቸው ሦስት ሺህ 451 አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሰጥቷል።

የይዞታ ማረጋገጫ ርክክብ ሥነ ሥርዓቱ የከተማዋ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እና ይዞታቸው የተረጋገጠላቸው አርሶ አደሮች በተገኙበት በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ከተሞች ወደ ላይ እና ወደ ጎን ሲያድጉና ሲስፋፉ ብዙ ሕዝብ በአንፃራዊነት በጠባብ መሬት ላይ የሚኖርበት እድል ይፈጠራል። ይህም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ማኅበራዊ መስተጋብርን ያሳድጋል።

በዚህ ሂደት በዙሪያቸው ያሉ አርሶአደሮችን እና ገጠራማ ቦታዎችን አካተው አብረው ያድጋሉ እንጂ ሕይወታቸውን የሚመሩበት ገቢ እና የመኖሪያ ቦታ ታሳቢ ሳይደረግ ያላግባብ ሊፈናቀሉ አይገባም ብለዋል።

ለዚህም ከተማ አስተዳደሩ ሕጋዊነትን ለማረጋገጥ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታቸው ለተረጋገጠላቸው ሦስት ሺህ 451 አርሶ አደሮች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሰጥቷል ብለዋል።

የይዞታ ማረጋገጫ መሰጠቱ አርሶ አደሩ መሬቱን በደላሎች እንዳይነጠቅ፣ ሕገ-ወጥነትን ለመከላከል፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፣ የአርሶ አደሩን መብት ለማስከበር እንደሆነም አብራርተዋል።

እንደ ከንቲባዋ ገለፃ፤ በከተማዋ አርሶ አደሮች በይዞታቸው ላይ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ፣ ደላሎችን ጨምሮ በተለያዩ አካላት ሲጭበረበሩ እና በይዞታቸው የመጠቀም ሕጋዊ መብታቸው ሲነፈግ ቆይቷል። ይህን ለማስቀረትና የአርሶ አደሮችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በርካታ የውይይት መድረኮች ተካሄደዋል። በውይይቱ መሠረት ለአርሶ አደሩ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ተወስኗል።

የአርሶ አደሮችን መሠረታዊ ጥያቄዎች በመለየት መሻሻል ያለባቸው የሕግ ማዕቀፎች እና አሠራሮች መሻሻላቸውንም የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች፤ የይዞታ ካርታ መውሰድ ብቻውን ግብ ባለመሆኑ መሬቱን ለልማት ጠንክሮ መሥራት ይገባል። የከተማዋን የተሟላ ዕድገትና የነዋሪዎቿን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መንግሥት በቁርጠኝነት እየሠራ እንደሆነም ገልጸዋል።

በቀጣይም አርሶአደሮች በሕግ የተሰጣቸውን ይዞታ የመጠቀምና ያለ አግባብ ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብታቸውን በማስከበር ከከተማዋ እድገት ጋር አብረው በማደግ የልማቱ አካል እንጂ ተፈናቃይ እንዳይሆኑ እንሠራለን ብለዋል።

የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠው በቦሌ፣ በየካ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በለሚ ኩራና በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተሞች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ነው።

ዜና

# በሦስት ክልሎች ከ8 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ተፈናቃዮች 4 ሚሊዮን ኩንታል የምግብ ድጋፍ ተደርጓል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሰባት ወራት በአማራ፣ በትግራይና በአፋር ክልሎች በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ከ8 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ተፈናቃዮች 4 ሚሊዮን ኩንታል የምግብ ድጋፍ መደረጉን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ አታለል አቡሃይ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሰባት ወራት በአማራ፣ በትግራይና በአፋር ክልሎች በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተፈናቀሉ ወገኖች እርዳታ እየተደረገላቸው ነው። በሦስቱ ክልሎች ለ8 ሚሊዮን 358 ሺህ 196 ተፈናቃዮች 382 ሺህ 261 ነጥብ 9 ሜትሪክ ቶን ወይም 4 ሚሊዮን ኩንታል ድጋፍ ተደርጓል።

እንደ አቶ አታለል ገለጻ፤ በትግራይ ክልል የድጋፍ ፈላጊ ቁጥር 5 ሚሊዮን 202 ሺህ 297 ሲሆን 2 ሚሊዮን 706 ሺህ 230 ኩንታል እህል ተሰጥቷል። ከዚህ ውስጥ 35 በመቶው የሚሆነው ድጋፍ ለሕጻናት፣ ለአረጋውያንና ለነፍሰጡሮች የሚሆን አልሚ ምግብ ነው።

በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር፣ ሰሜን ወሎና በዋግኽምራ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ አካባቢዎች ለ2 ሚሊዮን 440 ሺህ 767 ድጋፍ ፈላጊ ዜጎች 83 ሺህ 287 ነጥብ 9 ሜትሪክ ቶን ድጋፍ ተሰጥቷል። እንዲሁም በአፋር ክልል 715 ሺህ 132 ድጋፍ ፈላጊዎች ያሉ ሲሆን 28 ሺህ 351 ሜትሪክ ቶን የምግብ ድጋፍ ስለመደረጉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ አታለል ማብራሪያ፤ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ ጉዳት ከደረሰባቸው ውጭ በድርቅና በተዛማጅ አደጋዎች ምክንያት የተጎዱ ወገኖች አሉ። ኮሚሽኑ በበልግና በመኸር ወቅት የዳሰሳ ጥናት ባካሄደው መሠረት በጥር፣ በየካቲትና በመጋቢት ወራት 11 ነጥብ 7 ሚሊዮን ተረጂ ሕዝብ ነበር። በሚያዝያ፣ በግንቦትና በሰኔ ወራት ደግሞ የድጋፍ ፈላጊዎች ቁጥር ወደ 12 ነጥብ 7 ከፍ ብሏል። እነዚህም ምርት ያላመረቱ፣ ዘርተው እህል ያልያዘላቸው፣ ሰብላቸው በጎርፍ የተወሰደባቸው ዜጎች ናቸው። በቀጣይ ብዙ ሰዎች በጓሯቸው በፍጥነት የሚደርሱ ሰብሎችን የዘሩ በመሆኑ የተረጂዎች ቁጥር ወደ 8 ሚሊዮን ይወርዳል ብለዋል።

በኦሮሚያ፣ በሱማሌ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በድርቅ አደጋ የተጎዱ ወገኖች መኖራቸውን ያነሱት ባለሙያው፤ በኦሮሚያ ክልል በቦረና፣ በባሌ፣ ምስራቅ ባሌ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች 161 ሺህ 700 የሚሆን ኩንታል ተሰራጭቷል ብለዋል። በሶማሌ ክልል በአፍዴራ፣ በዳናና በሊበን ዞኖች 50 ሺህ 840 ኩንታል ድጋፍ ተደርጓል። በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በደቡብ ኦሞ፣ ዳሰነች፣ ሰላማጎ ወረዳ፣ የኮንሶ ዞንና በሰገን ዞን ዙሪያ ለሚገኙ ወረዳዎች 36 ሺህ 800 ኩንታል የሚደርስ እርዳታ ተደርጓል። በድምሩ 249 ሺህ 340 ኩንታል ተሰራጭቷል።

ከዓይነትና ከምግብ እርዳታ ውጭ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች ለ1 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በድምር



605 ሚሊዮን 305 ሺህ 645 ብር ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል።

በያዝነው ወቅት በክልሎች ጊዜያዊ የምግብ እጥረት ያጋጠማቸው የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ወገኖች አሉ። በሲዳማ 27 ሺህ 950፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ 52 ሺህ 36፣ በአፋር 15 ሺህ 921 በድሬዳዋ 7 ሺህ 80 ፣ በሐረሪ ክልል 5ሺህ 85 መኖራቸውም ተገልጿል። በድምሩ 108 ሺህ 672 ኩንታል ምግብ በኮሚሽኑና በአጋር አካላት ተሰራጭቷል። አስፈላጊው ምላሽ እየተሰጠም መሆኑን ባለሙያው ገልጸዋል።

አቶ አታለል አያይዘውም እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ ከ20 ሚሊዮን በላይ እርዳታ ፈላጊ ዜጎች አሉ። በራሳችን አቅም ምላሽ መስጠት የሚያስችል ክምችት እያደረግን ነው። ይሁንና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ ያስፈልጋል፤ የርዳታ እህል እየተሰረቀ ነው፤ ከታለመለት ውጭ ገበያ ላይ እየታየ ነውና ለሚፈለገው አካል አልደረሰም በሚል አቁመዋል። መንግሥትም የእርዳታ እህል መሸጥ እንደሌለበት ያምናል። ጉዳዩንም እያጣራ እንደሆነ ገልጿል። ሆኖም ሕዝብ መጎዳት ስለሌለበት ባለው ርዳታ እያቀረበ ይገኛል ብለዋል።

# “ጊዜው የሚጠይቀን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኢትዮጵያ ከሥራ ሥነ ምግባር ጋር የተያያዙ ችግሮች መኖራቸውን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳየው ጥቂቶች በርካቶችን እየተሸከሙ መሆናቸውን ነው ብለዋል። ይህንን ለመቀየር በአዲስ መልክ ካሪኩለም መቀረጹንና ይህም አገር ወዳድነት እንዴት ይገለጻል የሚል አቅጣጫ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ተናግረዋል። በዚህም የክህሎት ልማት ላይ በአሠራርና በቴክኖሎጂ የታገዘ ስልት መቀመጡን አመላክተዋል።

በተለይም የውጭ አገር የሥራ ስምሪት ሂደት ዜጎች ሠርተው ራሳቸውን ከመለወጥ ባሻገር ሀገራቸውን የማስተዋወቅና የመውደድ ትልቅ ሚና እንዲኖራቸው በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥልጠናና ስምሪት እየተሰጠ እንዳለ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገልጸዋል።

ጊዜው የሚጠይቀን የሀገር ወዳድነት አይነት በሥራ የሚገለጽ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ "ለአንድ ሀገር ትልቁ ሀብቱ የሰው ኃይል መሆኑንና የሰው ኃይልን ምርታማነት ማረጋገጥ ካልተቻለ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ከፍላጐት ያለፈ እንደማይሆን ተናግረዋል።

እንደ አገር ከኢኮኖሚ እድገት ጋር የተሳሰረ ክህሎት ተኮር የሥራ ዕድል ፈጠራ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ ለኢኮኖሚው እድገት ዜጐችን በዕውቀትና በክህሎት በማልማት ማስተዳደር እንደሚገባም አመላክተዋል።

ዜጐቿ ደስተኛ ሆነው የሚኖሩባትን ሀገር ማየት የማይፈልግ የለም ያሉት ሚኒስትሯ፣ ይህ የጋራ መሻት እውን እንዲሆን እንደ ተቋም ለብቻ መሥራት እንደማይቻል ጠቅሰው፣ ማልማት፣ ማብቃትና ማስተዳደር ላይ ጠንካራ አጋርነት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገለጻ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዜጐች ሀገራዊ ፀጋዎችን በመጠቀም የሥራ ፈጣሪነት አስተሳሰባቸው እንዲጐለብትና አገር ወዳድነታቸውን በሥራ እንዲገልጹ እያደረገ ይገኛል።

የባንኮች የብድር አገልግሎት ክፍተት፤ የመንግሥት ትኩረት ማነስና ብልሹ አሠራሮች በሥራ ፈጠራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች መሆናቸውን ተሳታፊዎች በውይይቱ አንስተዋል።

ትላንት ከተካሄደው ምክክር ጎን ለጎን “ብቁ” የተሰኘ የሥራ ገበያ የመረጃ ሥርዓት መተግበሪያ ይፋ ሆኗል። ሥርዓቱ በሥራ ገበያው ላይ የሚያጋጥሙ መሠረታዊ ችግሮችን የሚፈታና ብቁ ሠራተኛና ቀጣሪ ለመፍጠር የሚያስችል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። የገበያ አዋጭነት ሥርዓትን ለማልማትና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚወጡ የሥራ ማስታወቂያዎችን ከአንድ ማዕከል ለማግኘት ያስችላል ነው የተባለው።

# በፌዴራል መንግሥት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለማስተካከል የፌደራል መንግሥት ለክልል የሚሰጠውን በጀት፤ ርዳታና ድጎማ ኦዲት በተመለከተ ድግግሞሹን ለማስቀረት በ2013 ዓ.ም አዲስ አዋጅ እንዲፀድቅ ተደርጓል ብለዋል።

በተደጋጋሚ ኦዲት ማድረግ በኦዲት ተደራጊዎች ላይ ጫና ስለሚፈጥር የክልል ኦዲተሮችን አቅም በማጎልበት እነሱ የሠሩትን ለመቀበል የሚያስችል መመሪያም ባለፈው ዓመት ጸድቋል። በዚህ መሠረት ከየክልሉ ባለሙያዎች በማሠልጠንና ከፌደራልም ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎችን በመመደብ እየተሠራ ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም ይህ አሠራር በተለያዩ ምክንያቶች ከአዋጁ ወጥቶ እንደነበር ያስታወሱት ዋና ኦዲተሯ በአሁኑ ወቅት ግን ከፌደራል መንግሥት የሚለቀቅ ገንዘብ ኦዲት የሚደረገው በዋና ኦዲተር ስር በመሆኑ አዲስ በወጣው አዋጅ መሠረት ከክልሎች ጋር ስምምነት ተደርጓል ሲሉም አስረድተዋል፤ ሊያሠራ የሚችል የጋራ መመሪያ መዘጋጀቱንም ጠቁመዋል።

በዚህ ዓመትም አማራ ክልል በጦርነት ውስጥ ስለነበር በሙከራ ደረጃ በአራት ክልሎች ማለትም ኦሮሚያ፤ አዲስ አበባ፤ ሲዳማና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ላይ ተተግብሯል። ይህ አሠራር ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ሁሉም ክልሎች በሕጉ መሠረት በዋና ኦዲተር ስር ኦዲት የሚደረጉ ይሆናል።

በተመሳሳይ ከክዋኔ ኦዲት ጋር በተያያዘም ዋና ኦዲተሯ እንደተናገሩት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንም ሆነ የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ ዘንድሮ 33 ተቋማት ኦዲት የተደረጉ ሲሆን በቀጣይ አርባ ለማድረስ እየተሠራ ይገኛል። ተቋሙ የመንግሥትና የሕዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ ሲባል ሕዝባዊ ድርጅቶችን የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን እነዚህም እንደ ዐቃቤ ሕግ፤ ፓርላማና ፖሊስ ከመሳሰሉ ሦስተኛ ወገን የሚመጣ ጥያቄን መሠረት በማድረግ እየሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ‹‹ለሀገር ሉዓላዊነት መረጋገጥ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በጋራ ባዘጋጁት የምክክር መድረክ ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንዳሉት፤ የሀገር ግንባታ ሥራ በየጊዜው የሚፈጠሩ ዓለማዊ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች በሀገር ላይ የሚያስከትሉትን አደጋ እየተገነዘቡ በትውልድ ቅብብሎሽ አደጋውን የመቀልበስ ሥራን የሚጠይቅ ነው።

ለዘመናት የገነባናቸውን እሴቶች ተጠቅሞ ለሕዝቦች ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ለሀገር ሉዓላዊነት መጠበቅ ብሔራዊ መግባባት ፈጥሮ በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ አቋም የመያዝ ባሕልን ለማዳበር ርብርብ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ የፖለቲካ፣ የቋንቋ፣ የባሕልና የኃይማኖት ብዝኃነት ያላት ሀገር ናት ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ልዩነቶች የሀገራችን ኅብረ ቀለም ሆነው በአብሮነታችን ውስጥ ለሺህ ዓመታት የዘለቁ ሀብቶቻችን ናቸው። ሆኖም በረጅሙ የሀገር ግንባታ ጉዞ ለሀገር ሰላምና ዕድገት ዕንቅፋት የሆኑ፣ ለዘመናት የቆየው የመከባበር፣ አብሮ የመኖር ባሕልና እሴቶቻችንን የሚሸረሽሩ፣ የሕግ የበላይነትን የሚጻረሩና የሀገር ሕልውናን አደጋ ላይ የሚጥሉ ችግሮች እያጋጠሙ መሆኑን ገልጸዋል።

እነዚህ ችግሮችን ለአገር ሰላም መጠበቅና ለብሔራዊ ጥቅም መከበር ትልቅ ተግዳሮት በመሆናቸውም የጋራ እሴቶቻችን በማበልጸግ በሁሉም መስክ ሀገራችንን ቀዳሚ ለማድረግ በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የማይለዋወጥ አቋም መያዝና ብሔራዊ ጥቅም ላይ የማንደራደር መሆን ይጠበቅብናል ብለዋል።

በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በማያቋርጥ ሁኔታ ብሔራዊ መግባባት እየፈጠርን ከሄድን መሠረቷ የፀና ጠንካራ ኢትዮጵያን መገንባት እንደሚቻል ሚኒስትሩ አመልክተው፤ በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ፈጣንና ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ አዎንታዊ ሰላምና የዳበረ ዴሞክራሲን ማስፈን፣ ማኅበራዊ ሀብቶችን፣ እሴቶችንና አካባቢያዊ ዕውቀቶችን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

ለዚህም የትውልዱን ሥነ ልቦና መገንባት፣ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማኅበረሰቡ አዎንታዊ ሰላምን በማስረጽ ሀገራዊ ጉዳዮችንና ብሔራዊ ጥቅሞችን መለየትና የጋራ መግባባት መፍጠር ይጠበቅብናል ያሉት አቶ ብናልፍ፤ ማኅበራዊ ሀብቶችን፣ ባሕላዊ እሴቶችንና የጥናት ውጤቶችን ወደ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ ማሳደግ ሀገራዊ የቤት ሥራችን መሆን እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ማኅበራዊ ሀብቶቻችንንና ባሕላዊ እሴቶቻችንን በመገንባት ሂደት የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት ተቋማትና የሲቪክ ማኅበራት በባለቤትነት እንዲሳተፉ ማድረግ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ግጭትን ለመከላከልና ዴሞክራሲን ለማስፈን በቅንጅት በመሥራት ለዘላቂ ሰላም ምቹ ምሕዳር መፍጠር አስፈላጊ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰይፈ ደርቤ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ብዝኃነትን የተላበሰችና ኅብረ ብሔራዊነት መገለጫዋ የሆነች አገር ናት።

ካለው ብዝኃነት አኳያ የተለያዩ ምልከታዎችና አተያዮች መኖራቸው ተፈጥሯዊ ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ብዝኃነቱ ሰላምን የማይጎዳ፣ ብሔራዊ ጥቅምን የማይጻረር፣ መግባባትና መተማመን እንዲሁም የሚያጋጥሙ ግጭቶችን የሚፈቱበት ሁኔታ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

# አገልግል


የቅዳሜ መጽሔት




## ‹‹ኢትዮጵያዊነትን በቅጡ ያስተማረኝ መከላከያ ነው ብዬ አምናለሁ››

-አቶ ናትናኤል አስመላሽ
የማኅበረሰብ አንቂ

ገጽ 6



## አዕምሮን እንደ አዲስ መቀየር

ገጽ 12



ገጽ 18

## ‹‹ልጄን አደራ! ››

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «ኢትዮጵያዊነትን በቅጡ ያስተማረኝ መከላከያ ነው ብዬ አምናለሁ»

-አቶ ናትናኤል አስመላሽ
የማኅበረሰብ አንቂ

አስቴር ኤልያስ

**ውልደቱና እድገቱ በኤርትራ ዋና ከተማ አስመራ ነው፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በዚያው በአስመራ የተማረ ሲሆን፣ ከደርግ ውድቀት በኋላ ግን ከቤተሰቡ ጋር በመሆን ቀሪ ቤተሰቦቹ ወዳሉበት ወደ ትግራይ በ1987 ዓ.ም መጣ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተማረው በዓደዋ ንግሥተ ሳባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡**

**በወቅቱ የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤቱ ለኮሌጅ የሚያበቃና በጊዜው ደግሞ አዲስ የተከፈተ የተምቤን የትምህርት ኮሌጅ ቢኖርም ወደኮሌጅ ገብቶ መማርን አልተመኘም፡፡ ይልቁኑ በወቅቱ የኢትዮ-ኤርትራ (የባድሜ) ጦርነት ስለነበር ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጎን ለመቆም ወሰነ፤ ብቁ የሚያደርገውንም ሥልጠና ወስዶ መከላከያን ተቀላቀለ፡፡ በጦር ግንባርም በመዋል ጦርነቱ በድል እስኪጠናቀቅ ድረስ በዚያው ቆየ፡፡**

**ጦርነቱ እንዳበቃ በመከላከያ ቤት ብዙም አልቆየም፡፡ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አዲስ ኑሮ መኖር ጀመረ፡፡ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ የኮሌጅ ትምህርቱን ተማረ፡፡ በዚያው በተማረው ዘርፍም ተቀጥሮ እየሠራ ሳለ የዲቪ ሎተሪ ስለደረሰው ወደ ሀገረ አሜሪካ ተጓዘ፡፡ በዚያም ለ13 ዓመት ያህል የቆየ ሲሆን፣ ዛሬም እየኖረ ያለው በዚያው ነው፡፡ ይህ የዛሬ የዘመን እንግዳችን የማኅበረሰብ አንቂ ናትናኤል አስመላሽ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ተገድዳ የገባችበትን የጦርነት ወቅት በጊዜው የነበረውን የሕወሓትን ሥርዓት በመቃወም ብቻውን ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል፡፡ ከዚህ እንግዳ ጋር አዲስ ዘመን ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡- ናትናኤል ሰላምን የሚረዳው እንዴት ነው? ከሚለው ጭውውታችንን ልጀምር?**

**አቶ ናትናኤል፡-** መልካም ነው፤ ለእኔ ሰላም ትልቅ ትርጉም አለው፤ እንዳልኩሽ ተወልጄ ያደግሁት በሀገረ ኤርትራ ነው። ከዚያም በደርግ ውድቀት ምክንያት ወደ ትግራይ ብመጣም ብዙም ሳይቆይ ሀገራችን ወደጦርነት በመግባቷ ሰላምን ማጣጣም አልተቻለም ነበር።

ምንም እንኳ በደርግ ዘመነ መንግሥት ልጅ ብሆንም ሕወሓት ወደሥልጣን ከመጣ በኋላ ቢያንስ በኢትዮጵያ ወደሦስት ያህል ጊዜ ጦርነትን ለማየት ተገድጃለሁ። ከዚህም የተነሳ ጦርነት ባለበት ሰላም አይታሰብምና ሕይወት ማለፉ፣ መፈናቀሉና መንሳቀሉ የማይቀር ጉዳይ ነው። በተለይም እኔ የብዙ ጊዜ ጥያቄዬ ትግራይ ለምን ድሃ ሆነች የሚል ነበር። ይሁንና በዚያን ጊዜ በልጅ አዕምሮዬ ለጥያቄዬ ምላሽ የሚሰጠኝ ባይኖርም አሁን ግን ምላሹን አግኝቼዋለሁ፤ እሱም ጦርነት ያመጣው ጣጣ ነው ብዬ ደምድሜያለሁ። እንደ እኔ እምነት ትግራይ ወይም አንዱ የሀገራችን ክፍል ድሃ ሆነ ማለት ኢትዮጵያ ድሃ ሆነች ማለት ነው። ስለዚህ ሰላምን የምመርጥበት ዋናው ምክንያት በጦርነት የተነሳ በትግራይ ከበፊቱም ጀምሮ የሚፈናቀል ሕዝብ በማየቴ ነው።

ትግራይ ገጠራማው አካባቢ ያለውን የአኗኗር ዘይቤ ዛሬም አልተቀየረም። ዘመዶቼ የዛሬ 30 እና 40 ዓመት በሁለት በሬ ያርሱ ነበር፤ ዛሬም እንደዚያው ነው። ዛሬም ቢሆን በነበረው ጦርነት ሳቢያ ምን ያህል እንደተጎዱ አስተውያለሁ። ስለዚህ ለእኔ ሰላም ማለት ሕይወት ላለው ፍጥረት ሁሉ በተለይ ደግሞ ለሰው ልጅ የመጀመሪያው ምርጫ ነው ብዬ እንዳስብ የሚያደርገኝ ነው። በተለይ ደግሞ ትግራይ አካባቢ ተወልዶ ላደገ ሰው፣ የጦርነት አስከፊነት በደንብ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- አንተ የትግራይ ፖለቲካ መስወጥ አለበት ከሚሉት ጎራ ነህ፤ መስወጥ ካለበት ደግሞ ወጣቱም ጭምር ነው የሚሉ አካላት አሉና ወጣቱ መስወጥ ያለበት እንዴት ነው ትላለህ?**

**አቶ ናትናኤል፡-** በአሁኑ ወቅት በትግራይ ክልል እያስተዳደረ ያለው ጊዜያዊ አስተዳደር ነው፤ ስለዚህ ይህን ጊዜያዊ አስተዳደር ወደድንም ጠላንም መደገፍ አለብን የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ምክንያቱም አሁን በጊዜያዊነት ክልሉን እየመሩ ያሉት አቶ ጌታቸው ረዳ ከነበሩ አመራሮች ከሙስናም ከወንጀልም የጸዳ ነው ብዬ አምናለሁ።

አሁን ባለው የትግራይ ፖለቲካ ከድሮው ሥርዓት ተላቅቆ በጊዜያዊ አስተዳደር የተሻለ የክልል መንግሥት ለውጥ ያመጣል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ከሳምንታት በፊት አቶ ጌታቸው በአማራ ክልል ተገኝተው የአማራን ክልል ጎብኝተዋል። ይህ አካሄዳቸው በራሱ የአማራ ሕዝብ ለትግራይ ሕዝብ ጠላት እንዳልሆነና የትግራይ ሕዝብም ለአማራ ሕዝብ ጠላት አለመሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ብቸኛው ምርጫ የአቶ ጌታቸው አስተዳደርን መደገፍና ቢያንስ በቀጣዮቹ አምስትና አስር ዓመታት ውስጥ ትግራይ በአዲሱ ትውልድ የምትመራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል። ያለን አማራጭ ይህ ነው።

እንዲያም ሆኖ ግን አቶ ጌታቸው ብዙ ተግዳሮቶች አሉባቸው። ባለፉት 27 ዓመታት በትግራይ ውስጥ የነበረው ፖለቲካ አሳሪ እና ቋጠሮ የበዛበት ነበር። ስለዚህም ይህን ቋጠሮ ለመፍታት አቶ ጌታቸው ትልቅ ሥራ ይጠብቃቸዋል። ለዚህ ታላቅ ሥራ ደግሞ የትግራይ አዲሱ ትውልድ አቶ ጌታቸውን ለመደገፍ መነሳሳት ይጠበቅበታል። ለውጥ መምጣት የሚችለው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መጓዝ ከቻልን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አንተም እንደጠቀስከው ቀደም ሲልም በአማራ እና በትግራይ ሕዝብ መካከል ጠላትነት የለም፤ ከዚህስ በኋላ በአማራና በትግራይ ብሎም በሌላውም ሕዝብ መካከል ያለው ተግባቦት ምን መሆን አለበት ትላለህ?**

**አቶ ናትናኤል፡-** አንደኛ ነገር ምናልባት ሌላው ኢትዮጵያዊ የማይገባው፤ እኛ የትግራይ ተወላጆች የምንረዳው አንድ ነገር አለ። በትግራይ ውስጥ ይህን ሰላም የሚፈልግ በተለይ በትግራይና በኢትዮጵያውያን መካከል ዘላለማዊ የሆነ ጦርነት እንዲኖር የሚፈልግ ቡድን አለ። አቶ ጌታቸው ወደአመራርነቱ ስፍራ ከመጡ በኋላ ቀደም ሲል የነበሩትን የድሮ ሚዲያዎችን ተጠቅመው አቶ ጌታቸው የሚመራውን መንግሥት ጥላሸት ለመቀባት የሚጥር ቡድን አለ። ይህ ቡድን በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የማይፈልግ ነው። ይህ ቡድን መሠረቱ የሕዝብ ጥላቻ ነው። በተለይ ደግሞ አማራን እንደጠላት የሚቆጥር ቡድን ነው።

> **መጀመሪያ ከአሜሪካ በመጣሁ ጊዜ ወደጎጃም አቅንቼ ነበር፡፡ እናም ባህርዳርንም ደብረማርቆስንም በደንብ አይቻለሁ፡፡ ውስጥ ለውስጥ ተዘዋውሬም ነበርና ሕዝቡ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ምንም ልዩነት እንደሌለው ተመልክቻለሁ። ያለው ልዩነት የቋንቋ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጪ ኃይማኖቱም፣ አለባበሱም ሆነ የአኗኗር ዘይቤው ብዙ የሚለያዩ አይደለም፡፡ ያንን ሁኔታ ባየሁ ጊዜ እውን ይህን ሕዝብ ነው የትግራይ ጠላት ነው ተብሎ ሲነገረን የነበረው በማለት ራሴን ስጠይቅ ነበር**

ቀንቶት ሥልጣን እንኳን ቢያዝ ቂሙን መውጣት የሚፈልገው በአማራ ሕዝብ ላይ ነው። ይህ ቡድን ፍላጎቱና ሲሰብከውም የነበረው ነገር ወጣቱ የትግራይ ተወላጅ ሁሌም አማራን እንዲጠላ ነው።

እንደሚታወቀው ሕዝብ ከሕዝብ ጋር አይጣላም። አንድ ሕዝብ የሌላ አንድ ሕዝብ ጠላቱ ሆኖም አያውቅም። ላለፉት ሰላሳ ዓመታት የነበረው ቡድን አሁንም መደበቅ የሚፈልገው ለትግራይ ሕዝብ ጠላት ለመፍጠር ነው።

እኔ እንደ አንድ የትግራይ ተወላጅ የማስበው አማራ ለትግራይ ሕዝብ መቼም ጠላት ሆኖ አለማወቁን ነው። ለምሳሌ መጀመሪያ ከአሜሪካ በመጣሁ ጊዜ ወደጎጃም አቅንቼ ነበር። እናም ባህርዳርንም ደብረማርቆስንም በደንብ አይቻለሁ። ውስጥ ለውስጥ ተዘዋውሬም ነበርና ሕዝቡ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ምንም ልዩነት እንደሌለው ተመልክቻለሁ። ያለው ልዩነት የቋንቋ ብቻ ነው። ከዚያ ውጪ ኃይማኖቱም፣ አለባበሱም ሆነ የአኗኗር ዘይቤው ብዙ የሚለያዩ አይደለም። ያንን ሁኔታ ባየሁ ጊዜ እውን ይህን ሕዝብ ነው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “ኢትዮጵያዊነትን በቅጡ ያስተማረኝ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

የትግራይ ጠላት ነው ተብሎ ሲነገረን የነበረው በማለት ራሴን ስጠይቅ ነበር። በዚሁ አጋጣሚ መናገር የምፈልገው ነገር የአማራ ሕዝብ ጠላት አለመሆኑን ነው።

በሌላ በኩል መናገር የምፈልገው በአማራው አክቲቪስት በኩል የማየው ነገር ልክ በትግራይ እንዳለው አንድ ቡድን ዓይነት ነው። በእርግጥ እነዚህ አክቲቪስቶች ጥቂት ናቸው። እነርሱም መጥተው የትግራይን ሕዝብ አኗኗር ቢያዩና ቢፈርዱ ደስ ይለኛል። ስለዚህ ሕዝቡ በጠላትነት እንዲፈራረጅ ጥረት የሚያደርጉ አካላት ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የሰላም ስምምነት መፈረሙ ያመጣው ለውጥ አለ ብለህ ታምናለህ?**

**አቶ ናትናኤል፡-** አንደኛ የሰላም ስምምነቱ የሚጠቅመው ለትግራይ ብሎም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ስለዚህ ለእኔ የሰላም ስምምነቱ ቢያንስ በየአስር ዓመቱ ይከሰት የነበረው ጦርነት ከዚህ በኋላ ዳግም እንዳይከሰት አድርጓል ብዬ አምናለሁ።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ብዙ ነገር አይተናል። ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ግን የትግራይ ወጣት ከፍራቻ ወጥቶ ጥያቄ መጠየቅ ጀምሮ አይተናል። ለወደፊቱ የትግራይ ወጣት በዚህ መልኩ ጠያቂ ከሆነ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የትግራይ ፖለቲካ ተስፋ የሚሰጥ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በትግራይ ክልል በጦርነቱ ሳቢያ ለችግር የተዳረጉ አካላት ድጋፍ የሚሹ ናቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበሩ የተራድኦ ድርጅቶች ድጋፉ በአግባቡ አይደርስም በሚል ሰበብ ድጋፍ ማቋረጣቸው ይታወሳል፤ እዚህ ላይ የአንተ አመለካከት ምንድን ነው?**

**አቶ ናትናኤል፡-** መንግሥታት የየራሳቸው ተልዕኮ አላቸው። ለምሳሌ የዛሬ ሦስት ዓመት ድጋፍ አድራጊው አካል የራሱን አላማ ማራመድ እንጂ የትግራይ ሕዝብን የመርዳት አይደለም። እኔ የዛሬ ሦስት ዓመት አካባቢ በትግራይ ውስጥ ነበርኩ፤ እናም እንቅስቃሴያቸውን እመለከት ነበር። በወቅቱ ይጠቀሙበት የነበረው ቴክኖሎጂ ሁሉ የዓለም ምግብ ፕሮግራም በሚያደርግላቸው ድጋፍ ነበር።

እንደሚታወቀው ደግሞ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየሀገሩ የየራሳቸው ተልዕኮ ያላቸው ናቸው። የዛሬ ሦስት ዓመት ለትግራይ የመጣው እርዳታ እየተሸጠ የሚገኘው ገበያ ላይ ነበር። በወቅቱ አብዛኛው እርዳታ ፈላጊ የትግራይ ተወላጅ ሊያገኘው አልቻለም።

ላለፉት ስድስት ወራት ምንም እርዳታ ያልተቀበለ በየገጠሩ የሚገኝ በርካታ የትግራይ ተወላጅ አለ። በተለይ ደግሞ ልጆቻቸውን ወደጦር ግንባር የላኩ እናቶች እርዳታ እንኳ በቅጡ አላገኙም።

የውጭ መንግሥታት ሲኮንኑ የነበረው የኢትዮጵያን መንግሥት ነበር፤ ሆኖም በጦርነቱ ወቅት መንግሥት በማይቆጣጠራቸው አካባቢዎች የእርዳታ እህል በትግራይ ገበያ ሲቸበቸብ ነበር። ምናልባት የውጭ መንግሥታት አሁን ጉዳዩን የተረዱት ይመስለኛል። ያም ቢሆን እየተጎዳ ያለው ሕዝብ ነው።

ከዚህ አንጻር ጊዜያዊ አስተዳደሩ ብዙ ተግዳሮቶች ያሉበት ነው። ስለዚህ ካልሆነ የፌዴራል መንግሥት ኃላፊነቱን ራሱ ወስዶ እርዳታውን ለትግራይ ቢያከፋፍለው መልካም ነው። ይህ ካልሆነ ከዚህ በኋላም የሚመጣው እርዳታ ለሕዝቡ በአግባቡ ይደርሳል የሚል



**የሰላም ስምምነቱ የሚጠቅመው ለትግራይ ብሎም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ስለዚህ ለእኔ የሰላም ስምምነቱ ቢያንስ በየአስር ዓመቱ ይከሰት የነበረው ጦርነት ከዚህ በኋላ ዳግም እንዳይከሰት አድርጓል ብዬ አምናለሁ**

እምነት ይኖረኛል። ከዚህ በፊት ሲወነጀል የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ግን አሁን ነፃ ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡-በጦርነቱ ለተጎዱ አካባቢዎች ዛሬም ቢሆን ድጋፍ ሲደረግ ይገባል የሚሉ አሉ፤ በተለይ ለትግራይ ሕዝብ፤ ከዚህ አኳያ በዳያስፖራው ዘንድ የታሰበ ነገር ይኖር ይሆን?**

**አቶ ናትናኤል፡-**አብዛኛው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ በትግራይ ሕዝብ ላይ ጥላቻ ያለው አይመስለኝም። ምክን ያቱም እኔ የዛሬ ሦስት ዓመት ገደማ ይዤ የመጣሁት ወደ 45 ሺ ዶላር ነው። እሱንም ትግራይ ሒጄ አከፋፍያለሁ። አብዛኛውን ርዳታ የሰጠው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። ስለዚህ በጦርነቱ ጊዜም ይሁን አሁንም በውጭ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ በትግራይ ሕዝብ ላይ መጥፎ አመለካከት የለበትም።

በዚሁ አጋጣሚ ከሳም ንታት በፊት አስመራ ስለነበርኩ የኤርትራ ወታደርም ሆነ ሕዝቡ ለትግራይ ሕዝብ የሚያዝኑ ሆነው ነው ያገኘኋቸው።

አሁን ከጦርነቱ በኋላ የምናያቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ደግሞም በውጭ ሀገር የሚኖር የትግራይ ተወላጅ እያንዳንዱ ዋጋ ከፍሏል፤ ወይ አባቱ፣ ወይ እህቱ፣ አሊያም ወንድሙ ሞቷል።

ከዚህም በተጨማሪ በፋይናንስ በኩል ተጎድቷል። በጦርነቱ ወቅት እያንዳንዱ የትግራይ ተወላጅ በነፍስ ወከፍ እስከ ስድስት ሺ ዶላር ድረስ ሲያዋጣ ነበር። በአሜሪካ፣ አውሮፓና ካናዳ የሚኖር እያንዳንዱ የትግራይ ተወላጅ በዚያ ልክ ሲያዋጣው የነበረው ዶላር አሁን የት እንደደረሰ አይታወቅም። ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ የት እንደገባ አይታወቅም።

በሌላ በኩል ደግሞ በአሜሪካ፣ አውሮፓና ካናዳ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች አሁንም ዝምታን መርጠዋል። መጨረሻም ላይ የተነገረውና የሆነው ለየቅል በመሆኑ የትግራይ ዳያስፖራ በትንሹም ቢሆን ጥያቄ እንዲያነሳ ሆኗል።

የትግራይ ዳያስፖራ በአሁኑ ወቅት ትንሽ የተማረው ነገር ቢኖር ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ወደሀገሩ መምጣት መጀመሩን ነው። ትግራይ ድረስ መሄድ ጀምሯል። በተወለደበት አካባቢ በመገኘትም በጦርነቱ የተጎዳው ማን እንደሆነ በመጠኑም ቢሆን አውቋል። የነበረው ፕሮፓጋንዳና ያየው እውነታን ሲያነጻጽር የሚጋጭ ሆኖ አግኝቶታል። ከዚህ የተነሳ በጦርነቱ የደረሰውን ጉዳት አይቶታል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል የመከላከያ ሠራዊት አባል እንደነበርክ ይታወቃል፤ የሀገር መከላከያን እንዴት ትገልጸዋለህ?**

**አቶ ናትናኤል፡-** የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ቀደም ሲል ስለነበርኩበት በደንብ አውቀዋለሁ። እንዲያውም እኔ መከላከያ ውስጥ ባልገባ ኖሮ ጠባብ ሰው የምሆን ይመስለኝ ነበር። ኢትዮጵያዊነትን በቅጡ ያስተማረኝ መከላከያ ነው ብዬ አምናለሁ።

በነገራችን ላይ መከላከያ በትግራይ ሕዝብ ላይ ምንም ዓይነት ጥላቻ የለውም፤ መከላከያ ላለፉት 20 ዓመታት 80 በመቶ ያህሉ በሚያስብል ደረጃ የነበረው በትግራይ ነው። ስለዚህ ለትግራይ ሕዝብ ጥላቻ የለውም።

ባለፈው በጦርነቱ ወቅት አብዛኛው የትግራይ ነዋሪ በተለይ እኔ ሃይስኩል የተማርኩበት አካባቢ አክሱምንም ሽሬንም በደንብ አውቀዋለሁ። በእነዚህ አካባቢዎች መከላከያ የሚመለስልን መቼ ነው በማለት ላይ ነው። ቀደም ሲል የመጣውን እርዳታ መከላከያ ለሕዝቡ ሲያከፋፍል እንደነበር ሕዝብ በደንብ ያውቀዋል።

ሌላው በአሁኑ ወቅት በትግራይ በተለያየ ቀበሌ ላይ አመሽቶ መግባት ከባድ ሆኗል። ጦርነቱ ባመጣው ጦስ ሥራ አጥ ወጣት በርክቷል። ሰፍኗል። ይህን ጉዳይ አቶ ጌታቸውም በቅርቡ ሲናገሩት ነበር። እነዚህ ነገሮች ስላሉ አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ መከላከያ ይመለስልን እያለ ነው።

መከላከያ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለሆነ መልካም ጊዜም ስለሚመጣ በዚህ አጋጣሚ የትግራይ ወጣቶች እንዲቀላቀሉት ጥሪዬን አቀርባለሁ። ምክንያቱም አይተነዋል፤ መከላከያ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ሆኖ አያውቅም። እኔ ባለኝ መረጃ መከላከያ ለሕገ መንግሥቱና ለዚህች ሀገር የቆመ ተቋም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያዊነትን አጠናክሮ ከመሄድ አኳያ ምን መሠራት አለበት ትላለህ?**

**አቶ ናትናኤል፡-** አሁን ኢትዮጵያዊነትን በቶሎ ለማምጣት የሚከብድ ይመስለኛል። ያለፈው ትውልድ በተለይ ከ27 ዓመታት በፊት የነበረው በብሔሩ፣ በመንደሩና በጎጡ የሚያምን ትውልድ ነው። የአሁኑ መንግሥት ዕዳ ነው ብዬ የማስበው ያለፈው መንግሥት አንድ ያወረሰው ነገር ቢኖር በዘሩና በብሔሩ ብሎም በወሰኑ የሚያምንን ትውልድ ነው። የዚህን ትውልድ አስተሳሰብ ለመቀየር ሌላ ትውልድ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ስለዚህ እንደእኔ አመለካከት መንግሥት ሥራ መሥራት አለበት ብዬ የማስበው ከ15 ዓመት በታች ባለው ትውልድ ላይ ነው።

እናም በአንድ ጊዜ ኢትዮጵያዊነት አሁን በዚህ ሁኔታ እያለ ማምጣት ከባድ ነው። አንዱ አማራ ሌላው ኦሮሞ፣ ሌላው ቤኒሻንጉል እያለ የሚሄድ ሆኗል። ሰው ከኢትዮጵያዊነት ወጥቶ ስለራሱ ጎጥ ብቻ የሚያስብ ሆኗል። እኔ በሃሳቤ ይህኛ ያኛው ብሔሬ ነው ማለት አልሻም፤ ሲጀመርም ብሔር የለኝም። ስለዚህ ይህ የእኔ ወሰን ነው፤ ያኛው የእኔ ብሔር ነው ማለቱን መተው አለብን።

እንዲያው በጥቅሉ ማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር አሁን የተጀመረው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ከጎለበተ ኢትዮጵያ ትድናለች። ፖለቲካው ጤነኛ ከሆነ ኢትዮጵያም ጤነኛ ትሆናለች ብዬ አስባለሁ። እዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ የገባነው ሚዛናዊ ባልሆነ ፖለቲካ ምክንያት ነው። ለአብነት ብናነሳ በትግራይ አሁን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በጣም የተሻለ ነው። ስለዚህ የትግራይ ፖለቲካን የበለጠ የተሻለ ለማድረግ አሁን የአቶ ጌታቸው ረዳ አመራርን ወጣቱ ሊደግፈው ይገባል።

ከዚህ በፊት የነበረው ፍራቻ ሰብሮ እንደሌላው ኢትዮጵያዊ ሕገ መንግሥታዊ መብቱን ተጠቅሞ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ የመቃወምም የመደገፍም መብቱን ራሱ ማረጋገጥ መቻል አለበት። ለውጥ ከየትኛውም ክልልም ሆነ የፌዴራል መንግሥት መጠበቅ የለበትም። ምክንያቱም ትግራይ ከዚህ በኋላ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ መመራት የለባትም። ብዙ የተማረ ሰው አለ፤ ጊዜያዊ አስተዳደሩም ጥሩ ነው፤ ከፌዴራል መንግሥትም ጥሩ የሆነ ድጋፍ አለ። ስለዚህ ወጣቱ ለዚህ ተባባሪ መሆን አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ናትናኤል፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ክረምት እና ጥንቃቄ የሚሹ የጤና እክሎች

እፀገነት አክሊሉ

የክረምት ስሜቱ ደብዛዛ ነው። ይህም ቢሆን ክረምት የሕይወትና ሕልውና ዑደት መሠረት ነው። የበጋ ወራት ፍስሐና ተድላ የክረምት ስጦታዎች መሆናቸውም የሚካድ አይደለም። በክረምት ሰማዩ ዝናብ ይለግሳል፤ መሬትም ረስርሳ ሕይወት ትሰጣለች። የሰው፣ እንስሳትና እጽዋት ቀጣይነትም በክረምት ወቅት በሚመጣው በረከት የሚወሰን ነው። የሰብል ልምላሜ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች አቅም ሳይቀር የሚወሰነው በዚሁ ወቅት ነው።

ክረምት ከአዎንታዊ ጎኑ ባሻገር አሉታዊ ጎንም አለው። በተለይ ከባድ ዝናብን ተከትሎ የጎርፍና ውሃ ሙላት ስጋቶች ይከስታል። ለሰው ሕይወትና ለሀገር ሀብት ጥፋት ምክንያትም ይሆናል። የጤና ቀውስ የመሆን ዕድሉም ከፍተኛ ነው። እንደ ጉንፋን፣ አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት የመሳሰሉ የጤና ችግሮች ይወልዳል።

በክረምት ወቅት በገጠርም ሆነ በከተሞች ውሃ ያቆሩ ሥፍራዎች የወባ ትንኝ ያራባሉ። የውሃ መፋሰሻ ቱቦዎች ይዘጋሉ። የክረምት ባህሪ እንደ ጉንፋን፣ የአፍንጫን ጨምሮ ሌሎች የአስም ዓይነቶች እንዲሁም በአለርጂ ሳቢያ የሚከሰቱ የመተንፈሻ አካላት የጤና ችግሮችን ይወልዳል።

የክረምት ወራት በተላላፊ በሽታዎች ብቻ አይወሰንም። የክረምት ክፋቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችንም እንዲስፋፉ ዕድል መፍጠሩ ነው። የካንሰር፣ የልብና ስኳር በሽታዎች በዚህ ወቅት የሚበረቱ ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ሳቢያ በየዓመቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ36 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ለሕልፈተ-ሕይወት እንደሚዳረጉ ጥናቶች ያሳያሉ። የጤና ባለሙያዎች እንደሚሉት በተለይ በክረምት ወቅት ጤነኛ ያልሆነ አመጋገብ፣ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ ሲጋራ ማጨስ፣ አልኮል መጠጣት፣ በቂ የአካል እንቅስቃሴ አለማድረግ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ያጋልጣሉ።

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ በኢትዮጵያ ሰፊ ጥናት ባይደረግም ወደ ሕክምና ተቋማት የሚመጡ በበሽታው የተያዙ ሕሙማን ቁጥርና ሥርጭት መጠን ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ስለመምጣቱ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚያስከትሉ ናቸው። የደም ግፊት፣ የስኳር፣ ኮልስትሮል፣ የልብና የተለያዩ የካንሰር በሽታዎች በተለይም ክረምት ላይ የኅብረተሰቡን ብርቱ ጥንቃቄ ይሻሉ።

በክረምት ወቅት በርካታ ሰዎች ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳያደርጉ በቤታቸው እንዲያሳልፉ ሊገደዱ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የማጋለጥ ሳይንሳዊ መሠረት እንዳለው ባለሙያዎች ይገልፃሉ። አንድ ሰው በቀን ከ30 ደቂቃ ያላነሰ እንቅስቃሴ ቢያደርግ በተወሰነ መጠን ላብ እንዲወጣ በማድረግ ብቻ የሰውነቱን የቅባት መጠን መቀነስ ስለሚያስችለው በስኳር፣ ደም ግፊትና የልብ በሽታ የመጠቃት ዕድሉን ማጥበብ ያስችለዋል። አብዛኛው ሰው ግን ይህንን እንቅስቃሴ በክረምት ጊዜ እንደማያደርግ ይነገራል።

በአመጋገብ ረገድ ስጋ፣ ወተት፣ እንቁላልና መሰል የእንስሳት ተዋፅኦ ምግቦችን መቀነስ እንደሚገባና ይልቁንም አትክልትና ፍራፍሬ ምግቦችን መመገብ የተሻለ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅምን መገንባት እንደሚያስችል በጤና ባለሞያዎች ይመከራል።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በክረምት ወቅት እንደሚያርፉ ይገመታል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ተማሪዎችና መምህራን በአብነት ይጠቀሳሉ። ክረምቱ ለእንቅስቃሴ ምቹ ባለመሆኑ በእረፍት ምክንያት ረዥም ጊዜ ቤት ውስጥ መቀመጥ ከእንቅስቃሴ ጉድለት ጋር ተያይዞ ለሚወለዱ ደም ግፊትና መሰል የጤና ችግሮች እንደሚያጋልጥ ማወቅም ተገቢ ነው ይላሉ የጤና ባለሞያዎች።




«የክረምት ወቅት ውሃ ወለድን ጨምሮ የተለያዩ የመተንፈሻ አካላት ችግር የሚታይበት ጊዜ በመሆኑ በተለይም ከጤና ጋር በተያያዘ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሰዎች በተለይም እንደ አጣዳፊ ተቅማጥና ተውከት (አተት ) ያሉ በሽታዎች በክረምት ወቅት አቅማቸው የጎላ በመሆኑና የመከሰት ዕድላቸውም ሰፊ መሆኑን በመገንዘብ በተቻለ መጠን የራስንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ብሎም ያልበሰሉ ምግቦችን ከመመገብ መታቀብ ያስፈልጋል»

በክረምት ብዙ ሠራተኞች ከቅዝቃዜም ከዝናብም አንጻር ተሰባስበው የመቀመጥ ልምዱ ከፍ ቢልም በአንጻሩ ለተላላፊም ሆነ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድሉ ከፍ ይላል። እናም በክረምቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላለመጋለጥ እንቅስቃሴ ማዘውተር አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ከወባ፣ ኮሌራና መሰል ተላላፊ በሽታዎች ለመዳን ደግሞ ለንጽህና ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ይመከራል።

በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት ሐኪም ዶክተር ሰላም ስዩም እንደሚሉት፣ የክረምት ወቅት ውሃ ወለድን ጨምሮ የተለያዩ የመተንፈሻ አካላት ችግር የሚታይበት ጊዜ በመሆኑ በተለይም ከጤና ጋር በተያያዘ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ሰዎች በተለይም እንደ አጣዳፊ ተቅማጥና ተውከት (አተት) ያሉ በሽታዎች በክረምት ወቅት አቅማቸው የጎላ በመሆኑና የመከሰት ዕድላቸውም ሰፊ መሆኑን በመገንዘብ በተቻለ መጠን የራስንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ብሎም ያልበሰሉ ምግቦችን ከመመገብ መታቀብ ይኖርባቸዋል።

በተጨማሪም ሰዎች በተለይም ያልተጣራ (የቧንቧ) ያልሆነን ውሃ ሲጠጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። በተቻለ መጠን ውሃን አፍልተው መጠጣትና ሌሎች ውሃን ሊያክሙና ከውሃ ወለድ በሽታዎች ሊያጣሩ የሚችሉ ኬሚካሎችን መጠቀም አለባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የአተት በሽታ ማንኛውንም ሰው የሚያጠቃ በመሆኑና በተለይ በሽታው ሕፃናትና አረጋውያን ላይ ሲከሰት ይዞት የሚመጣው ችግርም ከፍ ስለሚል ኅብረተሰቡ ሊወስዳቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች ከፍተኛ መሆን አለባቸው። ለበሽታው አጋላጭ የሆኑና በተለይ ደግሞ ያልበሰሉ ምግቦችን ከመመገብ መቆጠብ ይኖርባቸዋል።

ዶክተር ሰላም እንደሚያብራሩት እንደ ሰላጣ፣ ቲማቲምና ሌሎችም ሳይበስሉ ሊበሉ የሚችሉ የምግብ ዓይነቶች ለእነዚህ በሽታዎች ጥሩ መራቢያ በመሆናቸው ሰዎች እነዚህን ምግቦች ለመመገብ ሲያስቡ በሎሚና ሌሎች የአትክልት ማጠቢያ ኬሚካሎች ተጠቅሞ ማጠብ ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን ደግሞ እነዚህን ያልበሰሉ ምግቦች ሕፃናት እንዳይጠቀሟቸው ማድረግ የበሽታውን የመስፋፋት መጠን በእጅጉ ይቀንሰዋል።

አጣዳፊ ተቅማጥና ተውከት (ኮሌራ) ከሌሎች ወይም ከምናውቃቸው የህመም ዓይነቶች ለየት ያለ ነው። ህመሙ የያዘው ሰውም የማያቋርጥና ወደውሃነት የተጠጋ ተቅማጥ ያስከትላል። ማስመለስ አልፎ አልፎ ትኩሳትና ራስ ምታትም የበሽታው ባህሪያት ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ምልክቶች ሲታዩ ታዲያ በቶሎ ወደ ጤና ተቋም መምጣት ያስፈልጋል። በሽታው የያዛቸውን ሰዎችንም ለይቶ ማቆየት፣ በተመገቡባቸውና በነኳቸው ዕቃዎች ያለመጠቀም የበሽታውን የመተላለፍ መጠኑን በእጅጉ ይቀንሰዋል።

‹‹ሁሉም ተቅማጦች ኮሌራ አይደሉም›› የሚሉት ዶክተር ሰላም ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ሲኖሩ በትክክል የበሽታው ምልክቶች መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባና ሰዎች ችላ ሳይሉ በቶሎ ወደ ሕክምና ቦታ መሄድ እንዳለባቸው ያስረዳሉ። ኮሌራ በባህሪው በተቅማጥና ትውከት አማካይነት በሰውነት ውስጥ ያሉ ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን ሁሉ የሚያሳጣ በመሆኑ በተለይ ሕፃናትና አረጋውያን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ያደርሳል። ከዚህ አኳያ በተቻለ መጠን አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግና የበሽታው መምጫና መተላለፊያ መንገዶችን መገንዘብ እንደሚገባም ነው ዶክተር ሰላም የሚያብራሩት።

በሽታው ሕፃናትና አረጋውያን ከያዛቸው የልብ ምታቸውን በማዛባት በሰውነታቸው ውስጥ ያሉትን ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች አሟጦ በመጨረስ ራስን እስከመሳት ሊያደርስ ይችላል። ስለዚህ ህመሙ ሲሰማ በቶሎ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ጤና ተቋም በማምራት አስፈላጊውን ሕክምና ማግኘትና ከሰውነት የወጡ ጠቃሚ ነጥረ ነገሮችን በቶሎ መተካት እንደሚያስፈልግም ይጠቁማሉ።

ይሁን እንጂ የበሽታው ተጠቂዎች ወደ ሕክምና ቦታ እስኪደርሱ ድረስ በቤት ውስጥ ሕይወት አድን ንጥረ ነገር /ORS/ በመመሪያው መሠረት መጠቀም አልያም ደግሞ በአንድ ሊትር ውሃ ውስጥ 6 የሻይ ማንኪያ ስኳርና 1 ማንኪያ ጨው በመቀላቀል ባስመለሳቸውና ባስቀመጣቸው ቁጥር መውሰድ እንዳለባቸው፤ ይህም ሳይዳከሙ ጤና ተቋም መድረስ እንደሚያስችላቸው ዶክተር ሰላም ያብራራሉ። በተጨማሪም ከጣፋጭ ነገር ውጪ ያሉ ማንኛውንም ሰዎች የሚጠቀሟቸው ፈሳሽ ነገሮችን መውሰድ እጅግ አስፈላጊ መሆኑንም ይመክራሉ።

ዶክተር ሰላም እንደሚገልፁት፣ የኮሌራ የመተላለፍ መጠን በጣም ፈጣንና ከፍ ያለ መሆኑን ኅብረተሰቡ ሊገነዘብ ይገባል። በተቻለ መጠን ህመሙ ያለበትን ሰው ብቻውን ማድረግ፣ በተመገበበትና በጠጣበት ዕቃ ሌላ ሰው እንዳይጠቀም ማድረግ፤ ሕፃናትና አረጋውያን ብሎም ተጓዳኝ በሽታዎች ያሉባቸው ሰዎችን ከአካባቢው ማራቅ ያስፈልጋል።

ኮሌራ እስከ አሁን በአዲስ አበባ ከተማ በወረርሽኝ መልክ ባይታይም በሌሎች ክልሎች ላይ ስለመኖሩ እየተነገረ ነው። አንዳንድ ሰዎችም በኮሌራ ታመው ወደቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል እየመጡ ይገኛሉ። ስለዚህ በተቻለ መጠን ግንዛቤን በማሳደግ ኅብረተሰቡም የራሱንና የአካባቢውን ንጽህና በመጠበቅ የሚመገበውን ምግብና የሚጠጣውን ውሃ ንጹህ በማድረግ ከችግሩ መዳን ያስፈልጋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በበሽታው ከተያዙ ግን ችግሩ ከፍ ያለ ጉዳት ሳያስከትል ወደጤና ተቋም መምጣት ይገባል።

ውሃ የመሰለ ተቅማጥ፣ ማስመለስ፣ ትኩሳትና የአካል መዳከም ካለ ህመሙ ኮሌራ ሊሆን ስለሚችል በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም መምጣት ያስፈልጋል። ታማሚው በቤቱ በቆየ ቁጥር ከተቅማጡና ከማስመለሱ ጋር ከሰውነቱ የሚያጣቸው ጠቃሚ ሚኒራሎች (ንጥረ ነገሮች) ስለሚኖሩ ጉዳቱ ከፍ ይላል። በሌላ በኩል የክረምት ወቅት ከኮሌራ በተጨማሪ የመተንፈሻ አካላት ችግሮችን በማምጣትም ሚናው ከፍ ያለ በመሆኑ ሰዎች እንደ ጉንፋን መሰል ምልክቶች (ትክትክ ዓይነትና ተራዘመ ሳል) ሲኖር ወደጤና ተቋም መሄድ ያስፈልጋል።

በአየር መቀየር ምክንያት የሚከሰቱ በርካታ የመተንፈሻ አካላት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ። በተለይም አስም፣ የቆየ የመተንፈሻ ችግር፣ ሳይነስ ያለባቸው ሰዎች መድኃኒታቸውን በአግባቡ መጠቀም፤ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ከሚያውቁት የህመም ሁኔታ የጨመረ ትንፋሽ ማጠርና መሰል ችግሮችን ያስከተለ ህመም ከተሰማቸው ግን በአስቸኳይ ወደሕክምና ተቋም መሄድ እንዳለባቸው ይመከራል።

በተለይ አሁን ላይ በብዙ ሰዎች ላይ ጉንፋን መሰል ምልክቶች እየተስተዋሉ ነው። ይህ ምናልባት መንስኤው ምንድነው የሚለውን ለማጤን ጥናት ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ከተለመደው የጉንፋን ህመም የተለየ ብሎም ለቀናት የዘለቀ የጉሮሮ ህመምም ይሁን ሳል ካጋጠመው ወደሆስፒታል በመሄድ ምንነቱን መለየት ብሎም ተገቢውን ሕክምና አግኝቶ ከተባባሰ ችግር ራስን ማዳን ይገባል።

የግል እና የአካባቢን ንጽህና የመጠበቅ ዝቅተኛ ልምድ ባለባቸው አካባቢዎችና ያልበሰሉ ምግቦች ጥቅም ላይ በሚውሉባቸው ቤቶች ውስጥ ሁሌም ቢሆን ኮሌራን ጨምሮ አተት ዋነኛ ምልክታቸው የሆኑ የተለያዩ በሽታዎች እንደሚከሰቱ ግልጽ በመሆኑ የግልና የአካባቢ ንጽህና በመጠበቅ ፤ በተለይም በዚህ በክረምት ወቅት ካልበሰሉ ምግቦች ራስን በማራቅ ጤናን መጠበቅ ያስፈልጋል።

# ነፃ ሃሳብ

## ሰርቶ መክበር እንደሚቻል ...

ከገጽ 15 የዞረ

ያልተሟላበት ምክንያት ደግሞ የሕዝብ ሀብትና ድርሻ በጥቂቶቹ ሙሰኞች ስለተሰበሰበ ነው።

መንግሥት ማለት የተቋማትና የክልል መንግሥታት ስብስብ ነው። ሁሉም ደግሞ በተዋረዳቸው መሪዎች ናቸው። ራዕይ ያላቸው፣ በሥልጣን የማይባልጉ፣ ሕዝብ የሚያገለግሉ፣ በሀገር ዕድገት ላይ በጎ የሚያስቡ፣ ከጊዜያዊ ጥቅምና ዝና ይልቅ ለሀገርና ለሕዝብ ዘመናት የሚያሻገር ሥራ የሚሰሩ ጥሩ አመራሮች በመሪነት ዘመናቸው የሙስናን ሰንኮፍ ከሥሩ መንግለው መጣል አለባቸው።

ሁሉም ባለድርሻ አካል በተቋሞቻቸው ውስጥና ከተቋሞቻቸው ውጭ በሚፈጠሩ የሌብነት ስራዎችን በአብነት በመታገልና በማታገል ከሆነ ብቻ ነው ለውጥ ሊመጣ የሚችለው። ለዚህ ደግሞ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። በክፍያቸውና በተገቢ ጥቅማጥቅማቸው የሚያገለግሉ አመራር ሆነው ሌብነትን ንቀውና ተጸይፈው ሁሉም በዘመናቸው ያደገች ሀገር ተገንብታ ለማየት የናፈቁ ከሆኑ ከወዲሁ የሌቦችን እግር መግታት እጆቻቸውንም ማሳጠር አለባቸው።

በዚህ ሀገር ሙስና /ሌብነት/ ጠፍቶ፣ ፍትሕ ነግሶ፣ ልማት ተስፋፍቶ፣ ሀገረ አድጎ ለማየት በብዙዎች ተጽፏል። ለምሳሌ ከመቶ ዓመት በፊት የነበሩ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ በዚህ ዘመን እስካሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችና የፖለቲካ አመራሮች ብዙ ቢሉም ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸውም ድንቅ ሐሳብ አምጥተው እንደታገሉበት ታሪክ ይነግረናል።

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ለሀገር ባደረጉት ውለታ በብዙ የሚጠቀስ ምግባራት ያሏቸው ንጉሠ ነገሥት ናቸው። ለሀገር አንድነት የደከሙ፣ የመንፈስ ጥንካሬያቸውን ያጋቡ፣ በጋፋት ድካማቸውን ማየት ይቻላል። ፕላውዴን እንደመሰከረላቸውም « ከሚገባው በላይ ለጋስና ለወርቅም ሆነ ለገንዘብ የማይሳሱ ናቸው » ሲላቸው፤ አውሮፓውያኑም «ጫማ አልባው ንጉሥ» ይሏቸዋል። ሀገር በእጃቸው ሆኖ የወርቅ ጫማ መጫማት፤ የወርቅ ልቡጥ ልብስ መልበስ ሲችሉ ሀገር ለማቅናት ደፋ ቀና ሲሉ ብዙውን ሕይወታቸው ከተራ ልብስ ያልወጡ ነበሩ። በአንድ ወቅት ይህን መልዕክት አስተላልፈውም ነበር፤

**"በቴዎድሮስ ዘመን ሠራተኛው በሥራው ይኩራ፤ ሌባ ለእጁ ይፍራ፤ ቀማኛ ለአንገቱ ይፍራ፤ ጉቦ የሚበላ ፍርድ የሚያዳላ ወዮውለት፤ እንኳን ከቴዎድሮስ ጋር ከእናቱ ጋር አይኖርም። መኖሪያ ቤቱ መቃብር ይሆናል። ከተራ እስከ ራስ፤ ሠራዊቴ በሙሉ እንደማዕረጉ በሚሰጠው ደሞዝ ይተዳደራል። ሁሉም ሰው እንደአቅሙ በነፍስ ወከፍ ለንጉሥ ይገብራል። ንጉሡም ከነሠራዊቱ ያንን እንደ ድርሻው ተከፋፍሎ ይተዳደራል"**ብለው ነበር።

እዚህ አንቀጽ ውስጥ የሚደንቁ ሐሳቦች አሉ። ሰው መኩራት ያለበት በስራው መሆኑን ይጠቁማል። ይህ ማለት ሠራተኛው በተገቢው ክፍያ የሚኖርበት፤ ለሙስና ለሌብነት እጁን የማይዘረጋበት፤ ሌባ ለእጁ ቀማኛ ለአንገቱ ይፍራ ሲሉም ያጠፋ በጊዜው የሚቀጣበትና ምንም ከለላ የማያገኝበት ተሰርቶ እንጂ ተሰርቆ መብላት የሚያስቀጣበት መሆኑን የሚያሳይ ነው። ዛሬ ላይ ግን ሌብነት በአደባባይ ወጥቶ ፀሐይ ሲሞቅ የማይታፈርበት ያልሰረቀ የማይከበርበት ዘመን መስሏል፤ ጉቦ የሚበላና ፍርድ የሚያዳላ አይቀጡ ቅጣት እንደሚቀጣና እንኳንስ ከንጉሡ ከእናቱ ጋር አይኖርም ሲሉ ሌባ መደበቂያ እንደሌለው ያሳዩበት ጭምር ነው።

ሌብነት ከነገሰ ሀገር ወደፊት መጓዝ አይቻላትም። በሀገር ላይ ሙስና ካልተስፋፋ በቀር ሥር የሰደደ ድህነት አይፈጠርም። ሙስና ከከሰመ ደግሞ ዜጎች የሀገር ሀብትን በተገቢ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ሀገር ያፈራውን የዜግነት ድርሻቸውን ሕዝብ ሊቃማ፣

**ኢትዮጵያ ባላት የሰው ኃይል ሀብት፤ የተፈጥሮና የታሪክ ሀብት በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን ችላ ለሌሎች ጎረቤት ሀገራትም የምትተርፍ ማድረግ ያን ያህል ከባድ አይደለም። ለዚህም ዘላቂ ሰላም በማስፈን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በማድረግና ከሌብነት በጸዳ ለሁሉም ሕዝብ ጠንካራ የሥራ ባሕል በመፍጠር ዕድገት፤ ብልጽግናንና ሥልጣኔን ማምጣት ይቻላል**

ሊነጠቅ አይገባም። ከምንም በላይ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ ሲኖሩ ዳቦና ውሃ የሰው እጅ አይተው መኖር አይገባቸውም። ዛሬ በዚህ ሀገር ውድ የሆነው መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን ናቸው። ግን በፍትሕ መዛባትና በሙስና ማየል ምክንያት የሕዝብ ሀብት ለጥቂቶቹ በመዋሉ ችግሩ የከፋ ሆኗል።

ሁሌም ለጤናማ የኑሮ ዘይቤ ሰርቶ በአቅም መኖር፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ሸምቶ መብላት፣ በሀገር ያለንን ሀብት በተገቢ መጠቀም የኑሮ ሥርዓቶች በሀገሩ መስፈን አለበት። ዳቦና ውሃ፤ መጠለያና አልባስ ማግኘት አለመቻል ራስን እስከማጣት የሚያስመስል ስጋት በዜጎች ልቦና ላይ መፈጠር የለበትም። በየትኛውም ሥነ አመክንዮ ቢታይ የሕዝብ ኑሮ ቤት ውስጥ ቢሆን ሥነ ልቦናዊ ፋይዳው የጎላ ነው የሚሆነው።

የሰውን እጅ በሕይወት፣ በኑሮ ውስጥ ማየት መቼም አያኮራም። መሠረታዊ ፍላጎቶቻችንን በሰው እጅ በልግስና መቀበል በራሱ ለተመጽዋቹ ከባድ ነው። የተለየ ምክንያት ካልተፈጠረ በስተቀር ዜጎች በልግስና መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት አይገባቸውም። ለሥራና ለኑሮ ትግል ሰንፈው ካልፈቀዱ በቀር።

በሀገሪቱ ውስጥ ድሆች ሳይሆኑ የድሃ ድሃ እየበዙ በመጡበት ሁኔታ ትንንሽ ነገሮችን በመደጎም ሥር የሰደደ ድኅነት አይቀረፍም። በእርግጥ ለጋሾች በሰው ዘንድ ተመራቂዎችና በፈጣሪ ዘንድም የበረከት ተቋዳሾች ናቸው። ማንም ቢሆን በመለገሱ አይወቀስም። ድሃ ለባለጸጋ እንኳ ካለው ቢሰጥ ይወደሳል እንጂ አይተችም። መስጠት መጠን የለውም፤ ልብ እንጂ ኪስ አይሰጥምና። ልግስና የሰብዓዊነት ሚዛን መጠበቂያ አንዱ ዕሴትም ነው።

በሀገሪቱ የተለያዩ የመንግሥት አካላት፤ ድርጅቶችና ቡድኖች አልያ በግለሰብና በየሃይማኖታዊ ባሕላት ላይ ለምሳሌ በክርስትና ሃይማኖታዊ ባሕላት ላይ ጾም ማስያዝና ማስፈሰክ፤ በእስልምና ሃይማኖታዊ ባሕላት ላይ ማስፈጠርና መለገስ እንዲሁም የተለያዩ ቁሶችን፣ አልባሳትንና የምግብ ውጤቶች ሸምቶ በልግስና ማቅረብ እየተለመደ መጥቷል። ይህ ተግባር በየጎዳናው፣ በየተቋማትና እስከ ቤት ለቤት ድረስ የሚተገበር በጎ ምግባር ነው።

አንዳንዴ ደግሞ የዚህ ዕድል ተቋዳሾች በዝና ሰማይ የነኑ፣ በሕይወት ወይም በኑሮ መሬት ያሉትን ጭምር በእናስታውሳቸው መርሃ ግብር በየባሕሉ የጎጆአቸውን በር የሚቀበቅቡ ለጋሾች አልጠፉም። የመኝታ ፍራሽ፣ ገንዘብ፣ በግ አንዳንዴም የበዓል ዳቦ ወይም ኬክ ተጨማሪ በማዘጋጀት ዐውድ ዓመትን ያከብሩላቸዋል። ይህ በራሱ የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል ክፋት የለውም። ክፋቱ ሀገር በማገልገል ለሰማይ ለምድር የከበዱ የነበሩ ዜጎች ቤት ባፈራው ባሕልን በቤታቸው ማክበር ሲሳናቸው ማየት ነው። ግን እስከ መቼ ይህ ዓይነቱ መንገድ ያዛልቃል። በተለይ ሀገርን በተሰጥኦዋቸው ሙያ ሲያገለግሉ ኖረው የማታ ማታ የሰው እጅ የሚያዩ አንጋፎችን ማሰብ በጣም ያሳዝናል።

በአንድ ሀገር ተፈጥሮ ካመጣው ድርቅና በሌሎች አደጋዎች ሰበብ ምክንያት የሚመጣ መራብና መታረዝ የሰው ልጆች የጋራ ጉዳይ ሆኖ እየታሰበ መጥቷል። ማንም ሀገር ቢሆን በተፈጥሮ አደጋ ሰውና እንስሳት ሲጎዱ እንኳን በሀገር ውስጥ ያለ ሕዝብ አይደለም በሌላ ክፍላተ አህጉራት ያሉ ሰዎች ሞራላዊ ግዴታቸው ሆኖ የመከራውን ባሕር ያሻግራሉ።

ይህ ዓይነት የሰብዓዊነት ትብብር ባለበት ዓለም በሀገር ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች የኑሮ መወደድ፣ ከፍትሕ መዛባት የተመረተው እንኳን የአቅርቦት ስርጭት ማነስ፣ ሕዝብን በዝባዥና አቆርቋዥ የንግድ ሥርዓት መፍጠርና በየመስኩ የሌብነት/ የሙስና ማበብ ተንሰራፍቶ ዜጎች ችግር ውስጥ ከወደቁ ችግሩ በዋናነት የሚነቃው ከአስተዳደር መናጠብ ነው የሚሆነው። ለዚህ ደግሞ ከማንም በላይ ሙስናን ለመከላከል የሚደረግ ጥረት ከምንም በላይ መቅደም አለበት።

በአንድም በሆነ በሌላ መንገድ የጎዳና ተዳዳሪ፤ የመንገድ ላይ ነዲያን፤ በየቤታቸው ያሉ ተረጂዎች፤ በአረጋውያን መርጃ ያሉና በሌሎችም ተቋማት ያሉ....የድኅነታቸው ዐብይ ምክንያት በሙስና / በሌብነት ድርሻቸው በተለየ መንገድ ተወስዶ እንጂ እንደዜጋ ዳቦና ውሃ፤ እራፊ ጨርቅና ትንሽ መጠለያ... ማጣት አልነበረባቸውም። አንድ ሀገር ሕዝቧ በምግብና በሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶች ራሳቸውን ችለው ለሀገሪቷም ዕድገትና ብልጽግና የሚያመጡ ነገሮች ለማየት አንዱ ሙስናን በመዋጋት ዜጎች ድርሻቸውን እንዲያገኙ በማድረግ ነው።

ኢትዮጵያ ባላት የሰው ኃይል ሀብት፤ የተፈጥሮና የታሪክ ሀብት በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን ችላ ለሌሎች ጎረቤት ሀገራትም የምትተርፍ ማድረግ ያን ያህል ከባድ አይደለም። ለዚህም ዘላቂ ሰላም በማስፈን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በማድረግና ከሌብነት በጸዳ ለሁሉም ሕዝብ ጠንካራ የሥራ ባሕል በመፍጠር ዕድገት፤ ብልጽግናንና ሥልጣኔን ማምጣት ይቻላል። ምንም ያህል ወደተለያዩ የሥራ ዘርፎች ሕዝብን ብናሰማራ የሌብነትን መረብ በጣጥሰን መጣል ካልቻልን የሀገርን ሀብት ጥቂት ግለሰቦች አስግረው ሀብታቸውን ማካበት የዘለለ አይሆንም።

በሀገር ላይ ሙስናን እንደ ሕዝብ ለመታገል ከትንሹ መጀመር እንችላለን። ሙስና ወይም ሌብነት የሰውን መውሰድ ከሆነ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የሚያጋጥሙን የሌብነት ልምምዶችን መዋጋት አለብን። ለምሳሌ ያህል በትራንስፖርት በታሪፍ ዋጋ መገልገል፤ በሸቀጦች ላይ ያለ ምክንያት የሚጨምሩቱን ዋጋ ላይ ቁጥጥር ማድረግ፤ በዳቦ፤ በጤፍ፤ በሥጋና በተለያዩ ቅመማ ቅመሞች ላይ በየባሕላቱ እያስታከኩ ዋጋ የሚያንሩትን ስግብግብ ነጋዴዎችን ገበያ ያወጡትን ባለመሸመት ሁሉ መቅጣት ይገባል።

በተለይ መንፈሳዊ በዓላትን በሥጋና በቅቤ ብቻ መከበር የለበትም በመንፈሳዊ ባሕሉ መወጣት ተገቢ ነው። በባሕላት ደስታ የሚያስፈልግ ቢሆንም ሁሌ በኑሮ እየተጨነቅን መሆን የለበትም። እንደ ሕዝብ የዕለት ተዕለት መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን ላይ ቅጥ ያጣ የዋጋ ንረት በጸጋ መቀበል ተገቢ አይደለም። ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠረው ከባድ የኑሮ ውድነት ሽክም ውጭ ያለው ዓለም ተጽዕኖ ይልቅ በሀገር ውስጥ ያለው የሙስና ጫና ይበልጥ ወገብ ያጎብጣል። ሀገርን እያደኸዩ ካላት ላይ ከመዝገን ሀገርን አሳድጎ ለሁሉም የማይጎድል የሀብት ምንጭ መፍጠር ይቻላል።

በአጠቃላይ እያደር የሚያድጉ፤ እያደርም የሚደኸዩ ሀገራት ይኖራሉ። ማደግም መደኸየትም ያለው በሕዝብ፤ በምሁራን፤ በነጋዴዎችና በመሪዎች ተሳትፎ ነው። ለዕድገትና ለሥልጣኔና ለብልጽግና ሁሉም ድርሻቸው የጎላ ነው። ሕዝብ የሀገር ሀብት ሲዘረፍ ሲያይና ሲሰማ ድምጹን ማሰማት አለበት። ምሁራን በአንድ ወገን በዕውቀታቸው የሀገሪቱን የዕድገት መስመር ማመላከት ሲሆን በሌላ መልክ ደግሞ ዕውቀታቸውን የሙስና መሳሪያ ባለማድረግ መከላከል ነው።

ነጋዴዎች ማለትም በትልልቅ ኢንቨስትመንት ውስጥ ያሉ ባለሀብቶች የገንዘብ ጉልበታቸውን በመጠቀም የሀገሪቱንና የሕዝቡን ሀብት ለመመዝበር የሚቋምጡትን የሀገር ውስጥ፤ ውጭ ባለሀብቶችንና መንግሥታት ስር ሀገር እንዳትወድቅ ሥርዓት ባለው መልክ በሀገር ላይ ንዋያቸውን አፍስሰው ራሳቸውንና ሀገርን ሲጠቀሙ ነው። እንዲሁም በተለያዩ እርከን ያሉ የመንግሥት አመራሮች ሙስናን በሀገር ውስጥ እንዳይስፋፋ ሕግ በማስከበርና ፍትሕን በማስፈን ሀገርን ከድኅነት መታደግ ይቻላል። ሙስና ሥራ ስላልሆነ አሸመድምደነው ሰርቶ መክበር እንደሚቻል ምስክር የምትሆን ሀገር በጋራ ፈጥሮ ማሳየት ከሁሉም ይጠበቃል።

# ተናጋሪው ዶሴ

## በኃይል ከተንኳኳው በር በስተጀርባ...

**ሶሎሞን በየነ**



አስፈሪው የሌሊቱ ጨለማ ቦታውን ለብርሃን ለቋል። ታዲያ ንጋቱ በወፎች ጫጫታ ሲበሰር ዘወትር በጠዋት ተነስታ አምላኳን የማመስገን ልማድ ያላት ወይዘሮ ጨረቃ ሽፈራው፤ እንደ ሁልጊዜው በጠዋት በጸሎት ቤቷ ተንበርክካ አምላኳን እየተማጸነች ነበር። ጸሎት እያደረገች እያለ ከወትሮው በተለየ መልኩ የግቢያቸው በር በኃይል ተንኳኳ። ይህንን ተከትሎ ቤት ውስጥ ያሉ ውሾች ጩኸታቸው አየለ። ይሄኔ የንጋት ጣፋጭ የእንቅልፍ ዓለም ውስጥ የነበረው ባለቤቷ አቶ ፍፁም ሐጎስ፤ ከእንቅልፉ ባኖ በውስጡ "በጠዋት የምን መርዶ ነጋሪ መጣብኝ እያለ" እያብሰለሰለ የሌሊት ልብሱን እንደለበሰ ወደ ግቢው በር ተንደረደረ። እሱም ወደ በሩ ጠጋ ብሎ በሩን ሳይከፍት "ማን ልበል"? አለ። በሩን በኃይል ሲያንኳኩ የነበሩ አካላትም "ፖሊሶች ነን፣ ጥቆማ ደርሶን ነው፣ ለፍተሻ ይተባበሩን" የሚል ድምጽ አሰሙ። እርሱም "የሕግ አካል ከሆኑማ" ብሎ የገቢውን በር ወለል አድርጎ ይከፍትላቸዋል።

በሩ ሲከፍት ሦስት ሲቪል የለበሱና ዘጠኝ አዲሱን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የደንብ ልብስ የለበሱ በድምሩ 12 ሰዎች የግቢውን በር አጥረው በተጠንቀቅ ቁመዋል። ከነዚህ ውስጥ አንዷ ሲቪል የለበሰች ሴት ነበረች። አራቱ ደግሞ ክላሽንኮፍ መሳሪያ ታጥቀዋል። አንዱ ደግሞ የወገቡ ቀበቶ ላይ ካቴና ሽብ አድርጓል። የቤቱ አባወራ ይህንን አቋማቸውንና አለባበሳቸውን ሲያይ የሕግ አካላት እንደሆኑ በሙሉ ልቡ ተማመነ። ወደ ቤት ገብተው እንዲፈትሹም ፈቃደኝነቱን ገለጸላቸው።

ይሄኔ 12ቱም ተንጋግተው ወደ ግቢው ይገባሉ። መሳሪያ ከያዙት አንደኛው ውጭ ላይ የቤቱን ጥበቃ ይዞ ቆመ። ሌሎቹ በጓሮ በር በኩል ተንጋግተው ወደ ቤት ገቡ። አንደኛው ሲቪል የለበሰና መሳሪያ የያዘ ግለሰብ አቶ ፍፁም ሐጎስን ወደ መኝታ ቤት አስገብቶ እንዳይንቀሳቀሱ መሳሪያ ይደግንባቸዋል። እርሳቸውን እንዳይንቀሳቀሱ አንድ ክፍል ቤት ካገቱ በኋላ ቀሪዎቹ ተከፋፍለው የተለያየ የቤቱን ክፍሎች መበርበር ጀመሩ። ሲቪል ከለበሱት አንደኛው ግለሰብ "ቶሎ ቶሎ በደንብ አድርጋቹህ ፈትሹ" እያለ በሳሎን ቤት ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ ትዕዛዝ ይሰጣል።

አቶ ፍፁም ላይ መሳሪያ የደገነባቸው ግለሰብ "ተጠቁመን ነው፣ ዶላር አምጣ" ይላቸዋል። እርሳቸውም "የደበቅሁት ዶላር የለኝም፣ ሕጋዊ ነጋዴ ነኝ" ይሉታል። ሌላኛው ግብር አበር ደግሞ አይኑን አፍጥጦ ወደ እርሳቸው ተጠጋና "አውቀህ ነው የደበቅከውን አውጣው" ብሎ ጎሮሯቸውን አንቆ መተንፈሻ ያሳጣቸዋል። "የደበቅሁት ነገር የለኝም መፈተሽ ትችላላቹህ" ብለው የቤቱ አባውራ መልስ ይሰጣሉ። የተወሰኑት ግብረአበሮች የቤቱን አባወራ በመኝታ ቤታቸው ጉሮሯቸውን አንቀው እያፋጠጡ በተመሳሳይ ደግሞ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ጨረቃ ሽፈራውን፤ መሳሪያ ከያዙት አንደኛው ግለሰብ "የደበቅሽው መሳሪያና ዶላር የት እንዳለ ካስቀመጥሽው ንገሪኝ" ብሎ አፋጦ ይይዛታል። እሷም "እኔ እንኳን የጦር መሳሪያ ለመያዝ ይቅርና ሳየውም እፈራለሁ። ምንም ነገር የለም። ፖሊስ ከሆናቹህ መፈተሽ ትችላላቹህ" ትላቸዋለች።

እነርሱም ሽርኩቻ ሳይቀራቸው ሁሉንም የቤቱን ክፍሎች በርብረው ቤቱን ግልብጥብጡን አውጥተውት በጓሮ በር እየተጣደፉ ወጥተው ይሄዳሉ። ከወጡ በኋላም ነጭ ሚኒባስ መኪና አስነስተው ወደ አያት አቅጣጫ እየከነፉ ሲሄዱ ባልና ሚስት ተደናግጠው የቤታቸው በረንዳ ላይ ቆመው ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄዱ እያዩአቸው እያለ ልጃቸው ሰሎሜ ከመኝታ ቤቷ በራ ወላጆቿ ወዳሉበት በመሄድ "ከልጆች መኝታ ቤት የነበሩ ሁለት ላፕቶፕ ኮምፒውተሮችን እንደወሰዱ" ለእናት እና አባቷ ትነግራቸዋለች።

ልጃቸው ይሄንን ዜና እስክትነግራቸው ድረስ ባልና ሚስት የተፈጸመው ድርጊት የዘረፋ ወንጀል መሆኑን አልጠረጠሩም ነበር። ይህንን መርዶ ከሰሙ በኋላ ባልና ሚስት ወደ ቤት ገብተው ምን ምን ንብረት እንደተዘረፉ ሲያረጋግጡ፤ ከመኝታ ቤት ኮመዲኖ ውስጥ የነበረ ባለ 18 ካራት 23 ግራም ወርቅ ግምቱ 50 ሺ. ብር የሚያወጣ፤ የልጃቸው የመስመር ስልክ የሌለው አንድ ሳምሰንግ ጋላክሲ ኤስ ናይን (Samsung galaxy s9) የእጅ ስልክ ግምታዊ ዋጋው 15 ሺ. ብር የሚያወጣ እንዲሁም አንደኛ ፎቅ የልጆች መኝታ ክፍል ኮመዲኖ ላይ የነበሩ ሁለት ዴል (dell) ላፕቶፕ ኮምፒተሮች እያንዳንዳቸው 30 ሺ. ብር ግምታዊ ዋጋ ያላቸው፤ በአጠቃላይ 125 ሺ. ብር የሚያወጣ ንብረት በ22/04/2014 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12:30 ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ክልል ልዩ ቦታው አያት መንደር ዞን አምስት ፤ መንገድ ዘጠኝ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው የግል ተበዳይ በሆነ ባለ አንድ ወለል መኖሪያ ቤት ውስጥ የተደራጁ የወንበዴ ቡድን በመግባት በጦር መሳሪያ የታገዘ ዘረፋ አካሂደው ይሰወራሉ።

ከዘረፋው በኋላ አቶ ፍፁም ቀጥታ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አቅንተው በእለቱ በቤታቸው በመሳሪያ ታጅቦ የተፈጸመውን የውንብድና ወንጀል ለፖሊስ ሪፖርት ያደርጋሉ። ፖሊስም ወንጀሉ የፈጸሙ አካላት መልካቸው፣ ቁመናቸው፣ አለባበሳቸው፣ ቋንቋቸው፣ ወዘተ. ምን እንደሚመስል ከተበ ዳይና ከአይን ምስክሮች ቃላቸውን ተቀብሎ ወንጀለኞችን ማፈላለጉን ተያያዘው። የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንም ከሶስት ወር ውጣ ውረድ በኋላ ወንጀሉን ፈጽመው ከተሰወሩት ውስጥ አንደኛዋን ተጠርጣሪ በ02/07/2014 ዓ.ም በቁጥጥር ስር አዋለ። ተጠርጣሪዋ ፅጌ ሽለመ ኃይሉ የምትባል ስትሆን፤ ፖሊስ የሰው ምስክሮች ከተጠርጣሪዎች መካከል በፎቶ እንዲለዩ ካቀረበላቸው ምስሎች ውስጥ ይቺ ተጠርጣሪ ወንጀሉን እንደፈፀመች በመጠቆማቸውና የምስክር ቃላቸውን በመስ ጠታቸው ነው።

### የተጠርጣሪ የእምነት ክህደት ቃል

ተጠርጣሪ ፅጌ ሽለመ በቅጽል ስሟ ብርክቲ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን አሞባ ጉደር ከተማ ውስጥ ከአቶ ሽለመ ኃይሉ እና ከወይዘሮ ጌጤ ገለታ ከተባሉ እናትና አባቷ በ1979 ዓ.ም ተወለደች። እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ ወደ አዲስ አበባ በማቅናት ከአንደኛ እስከ ዘጠነኛ ክፍል በመዲናዋ ትምህርቷን ተከታትላለች። በ2000 ዓ.ም ትምህርቷን አቋርጣ በጽዳት ሠራተኝነት በተለያዩ ሆቴሎች ስትሠራ እንደነበር ትናገራለች።

ወንጀሉ በተፈጸመበት ቀን ዮናስ ወይም ሚኪ የተባለው ያልተያዘ የወንጀሉ ፈጻሚ ግለሰብ የሚዘረፍ ቤት እንዳለ በስልክ ደውሎ ያሳውቃታል። እሷም ወንጀሉን ለመፈጸም ተስማምታ ባልቻ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ተገናኝተው ከሌሎች ያልተያዙ የወንጀሉ ፈጻሚዎች ጋር በአንድ መኪና ወደ ግል ተበዳይ ቤት ያቀናሉ። በግል ተበዳይ ቤት እንደደረሱ "ፖሊሶች ነን" ብለው የገቢ በር ካስከፈቱ በኋላ ወላይታው የተባለው ያልተያዘው የወንጀሉ ፈጻሚ ግለሰብ ተበዳይን በቦክስ ትክሻው ላይ ደጋግሞ በቦክስ በመምታት እንዲፈራ ያደርጋል።

ከዛ ተበዳይ እንዲፈራ ከተደረገ በኋላ ቤቱን በመበርበር "ሌሎች ተጠርጣሪዎች ሞባይልና የአንገት የወርቅ ሀብል ሲወስዱ ባላይም፤ በቁጥር ሁለት አይነታቸው ዴል (dell) ሲልቨር አልሙኒየም ከለር ያላቸው የዋጋ ግምታቸው ብር 60 ሺ. የሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒውተሮችን አንደኛ ፎቅ መኝታ ቤት ውስጥ ስበረብር ሳገኛቸው ሁለቱንም ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች አንስቼ ቦርሳዬ ውስጥ ከትቻለሁ። ከግቢው እንደወጣን ሚኪያስ ወይም ዮናስ የተባለው ግለሰብ ላፕቶፖቹን ተቀብሎኛል።

ላፕቶፖቹ በ07/05/2014 ዓ.ም በግምት 3:00 ሰዓት አካባቢ የካ ክፍለ ከተማ የተባበሩት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተሸጠው፤ ሚኪ ወይም ዮናስ በመባል የሚጠራው የወንጀሉ ፈጻሚ ግለሰብ ሁለት ሺ. ብር እንደሰጣት" ትናገራለች። እሷም የዘረፋ ወንጀሉን መፈፀሟን አምና ጥፋተኛ ነኝ ስትል ለፖሊስ የእምነት ክህደት ቃሏን ሰጥታለች። ፖሊስም የተጠር ጣሪዋን የእምነት ክህደት ቃል፣ የምስክሮችን እና የተበዳይን ቃል አደራጅቶ ዐቃቢ ሕግ ክስ እንዲመሰርትባት መረጃውን አቅርቧል።

### ዐቃቢ ሕግ

የ1996 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 671 (1) (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ተከሳሽ ፅጌ ሽለመ በጦር መሳሪያ በመታገዝ በሰው ወይም በንብረት ላይ ወንጀል ለመፈጸም የተደራጀ የወንበዴ ቡድን ጋር በመሆን የማይገባትን ብልጽግና ለራሷ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ቦታ አራት ክልሽንኮቭ መሳሪያ ከያዙ፣ ዘጠኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ ደንብ ልብስ የለበሱና ሁለት የሲቪል ሰው አለባበስ የለበሱ በድምሩ 11 ሰዎች ጋር በመሆን የግል ተበዳይ በሆነው በአቶ ፍፁም ሐጎስ ቤት በመሄድና በር በማንኳኳት በሩ እንዲከፈት ያደርጋሉ። በሩ ከተከፈተ በኋላ "ፖሊሶች ነን፣ ተጠቁመን ነው፣ ቤቱን እንፈትሻለን" በማለት ያልተያዘ ግብረአበሯ "ተበዳይን መሳሪያና ዶላር አምጣ" በማለት የያዘውን መሳሪያ ተበዳይ ላይ በመደገን አንገቱን አንቆ በመያዝ ተከሳሿና ሌሎች ያልተያዙት የወንጀሉ ፈጻሚዎች የተበዳይን ቤት በርብረዋል።

በብርበራውም ተከሳሿ ፅጌ ሽለመ በቁጥር ሁለት አይነታቸው ዴል (dell) የዋጋ ግምታቸው ብር 60 ሺ. የሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒውተሮችን በማንሳት ይዛው በነበረው ቦርሳ በመክተት ስትወስድ፤ ሌሎች ግብራበሮቿ የዋጋ ግምቱ 50 ሺ. ብር የሆነ ባላ 18 ካራት 23 ግራም ወርቅ እና 15 ሺ. ብር የሚገመት ሳምሰንግ ጋላክሲ ኤስ ናይን (Samsung galaxy s9) የእጅ ስልክ በድምሩ 125 ሺ. ብር የሚያወጡ ንብረቶችን በመውሰድ መኪና ውስጥ በመግባት የተሰወሩ በመሆኑ ተከሳሽ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀመችው የከባድ ውንብድና ወንጀል ክስ ተመስርቶባታል።

ዐቃቢ ሕግም ሰባት የሰው ማስረጃ፣ ምስክሮች ተከሳሽን ከሌሎች ተጠርጣሪ ግለሰቦች መካከል ሲመርጡ የሚያሳዩ ምስሎችንና ተከሳሽ በወ/መ/ስ/ህ/ቁ 27(2) መሰረት ለፖሊስ የሰጠችውን የእምነት ክህደት ቃል በማስረጃነት አያይዞ ለፍርድ ቤቱ አቅርቧል። ዐቃቢ ሕግ የሰው ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቦ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በተከሳሿ ላይ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል።

### ውሳኔ

የካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በችሎቱ የተሰየመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በተከሳሽ ፅጌ ሽለመ ኃይሉ ክስ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመስጠት ተሰይሟል። ፍርድ ቤቱም በዚህ ቀን በዋለው ችሎት ተከሳሽ በ12 (በአሥራ ሁለት) ዓመት ጽኑ እስራትና ከማናቸውም ሕዝባዊ መብቷ እንድትታገድ ሲል ውሳኔ አሳልፏል።

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ለጀግኖች ሐውልት ማቆም ይልመድብን !

ቦጋለ አበበ

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ «ጋርመንት» አካባቢ ባለው አደባባይ የተገነባው የክቡር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ መታሰቢያ ሐውልት ተመርቋል። ለዚህ ተወዳጅ የኪነ ጥበብ ሰው ሐውልት መቆሙ ተገቢና መለመድም ያለበት ነው። ለዚህ ታላቅ የሙዚቃ ሰው ሐውልት መቆሙ ብቻ ሳይሆን ሐውልቱ ላይ የሰፈረው ጽሑፍም ድንቅ ነው። በሐውልቱ ላይ ዘመን አይሽሬ ከሆኑት የአሊ ቢራ ሙዚቃዎች አንዱ ከሆነው ሥራ ላይ የተመዘዙ ስንኞች በአፋን ኦሮሞና በአማርኛ ተተርጉሞ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ሰፍሯል :-

**Rabbi moo namumaa**<br>
**Kan seera jallisee ?**<br>
**Haati teenya takkaa**<br>
**Maaltu addaan nu baasee ?**<br>
**አምላክ ወንይስ ሰው ፤**<br>
**ሕግን ያጣመመው ?**<br>
**የአንድ እናት ልጆች ነን ፤**<br>
**የሚለያየን ማን ነው ?**

ይህ ታላቅ መልዕክት ያዘለ ትውልድ አስተማሪ የሆነ ስንኝ በአሊ ሐውልት ላይ እንዲሰፍር መደረጉን ሳያደንቁ ማለፍ አይቻልም። ይህን ትልቅ ነገር ፈፅሞ አንድ ቦታ ላይ የሚታየውን ግድፈት ወይም ስህተት ሊባል ይችላል መጠቆሙም ተገቢ ነው። ሐውልቱ ላይ አሊ የተወለደው 26/05/1948 ነው የሞተው ደግሞ በ06/11/2022 ነው ይላል። ይህ ስህተት ነው። አሊ ቢራ ኢትዮጵያዊ እንደመሆኑ የተወለደበትና ሕይወቱ ያለፈበት የዘመን አቆጣጠር በኢትዮጵያ መሆን አለበት። ምናልባት ሐውልቱን የውጭ አገር ዜጎች የሚመለከቱት እንደመሆኑ እነሱን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ታስቦም ከሆነ በኢትዮጵያም በአውሮፓም ዘመን አቆጣጠር ማስፈር ይቻላል። በእርግጥ ሌሎች ታላላቅ ሐውልቶች ላይም እንዲህ ዓይነት ጥቃቅን ስህተቶች ቢፈለጉ አይጠፉም። ያምሆኖ ወደ ፊት ለሚገነቡ ሐውልቶች ጥንቃቄ እንዲደረግባቸው ትምህርት ይሆናልና መጠቆሙ አይከፋም።

የሐውልት ነገር ሲነሳ በኢትዮጵያ ብዙ አከራካሪ ጉዳዮች አብረው ይነሳሉ። ለምሳሌ ያህል በተለያዩ ዘርፎች ለሀገር ትልቅ ውለታ የሠሩ በርካታ ጀግኖች ሐውልት አልቆመላቸውም የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። እውነት ነው ኢትዮጵያ ለበርካታ ጀግኖቿ የሚገባቸውን ሐውልት ገና አቁማ አልጨረሰችም። ወደ ፊት አቅም በፈቀደ ልክ እንደ አሊ ቢራ በጉልህ የሚታይ ሐውልት አደባባይ ላይ የሚቆምላቸው አያሌ የሀገር ባለውለታና ጀግኖች ይኖራሉ።

እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለባቸው ሐውልት ሊቆምላቸው የሚገባ ነገር ግን ብዙም ትኩረት ሲሰጣቸው የማይታዩ ጀግኖችን በጥቂቱ እንታዘብ። እነዚህ ጀግኖች ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከፍ ያደረጉና ያስከበሩ ብርቅዬ አትሌቶቻችን ናቸው። እነዚህ የኢትዮጵያ ምልክቶች በየከተሞቻችን ሐውልት ሊቆምላቸው እንደሚገባ አያከራክርም። እንኳን ሀገራቸው ሌሎች ሀገራትም ለእነዚህ ብርቅዬ አትሌቶች ሐውልት አቁመው ሲያከብሯቸው አይተናል። ለምሳሌ ሻምበል አበበ ቢቂላ በሮምና ቶኪዮ በሠራቸው ገድሎች ሐውልት ባይቆምለት እንኳን በስሙ በርካታ ጎዳናዎች፣ድልድዮች ተሰይመውለት ይገኛሉ። ሌላኛው የኦሊምፒክ ማራቶን ጀግና ማሞ ወልዴም ቢሆን ስፔን ውስጥ ሐውልት ቆሞለት ይገኛል(በእርግጥ የማሞ ሐውልት በስፔን አራት ጊዜ የሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና በማሸነፉ ነው)። የአፍሪካ እግር ኳስ አባት የሆኑት ይድነቃቸው ተሰማም ሞሮኮ ላይ በስማቸው ስቴድየም ተሰይሞ ይገኛል።

አበበ ቢቂላ አዲስ አበባና አዳማ ላይ በስሙ ስቴድየም ተሰይሞለታል። ነገር ግን አበበ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የአሸናፊነት ተምሳሌት ነውና ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ከተሞች አደባባይ ላይ ሐውልት ሊቆምለት የሚገባ ሰው ነው። እንደ አበበ ቢቂላ ሁሉ ሌሎች በርካታ ዘመን የማይሽረው ታሪክ ያኖሩ አትሌቶችም ሐውልት ሊቆምላቸው እንደሚገባ ጥርጥር የለውም። በዚህ ረገድ ጀግናዋ አትሌት ደራርቱ ቱሉ በአዲስ አበባ ሃያት ተብሎ ይጠራ የነበረው አደባባይ በስሟ ተሰይሞ አበረታች ጅምር ታይቶ ነበር። ይህ መቀጠል አለበት።

እዚህ ጋር ሌሎች ሀገራት ያላቸውን ተሞክሮ ማሳያ እንዲሆን ላንሳ። ጃክ ሌዝሊ፤ የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድንን ማልያ አጥልቆ ታሪክ ከሠራ 100 ዓመታት ሊሞላው ቢሆን እንኳ በቅጡ የሚያስታውሰው ሰው አልነበረም። ይህ የሆነው በቆዳው ቀለም ብቻ ነው። ጊዜው 1925 ነበር። እንግሊዝ ከአየርላንድ ጋር ለነበራት የወዳጅነት ጨዋታ መልማዮች ተጫዋቾችን እየመለመሉ ነበር። በወቅቱ ሌዝሊ የፕላይማውዝ ተጫዋች ነበር። መልማዮቹ የሚጫወትበት ሜዳ መጥተው ሲመለከቱ ሌዝሊን ጥቁር ሆኖ ያገኙታል። በዚህም ምክንያት ሌዝሊ ለእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን የተሰለፈ የመጀመሪያው ተጫዋች በመሆን ታሪክ የሚሠራበትን አጋጣሚ መና ያደርጉበታል። ይኸው ሌዝሊ አሁን ገንዘብ ተዋጥቶለት ሐውልት ሊሠራለት እየታቀደ ነው። እስካሁን ቢያንስ 135 ሺህ ፓውንድ ተዋጥቶለታል። ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ 240 ስፖርተኞችን የሚዘክሩ ሐውልቶች አሉ። ከዚህ የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር አለ። ይህም እንኳን የሀገርን ስም በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ከፍ አድርገው ያስጠሩ ጀግኖች እንደ ሌዝሊ በሆነ አጋጣሚ የተዘነጉ ሳይቀሩ ሐውልት እንደሚቆምላቸው ነው። እኛም ሐውልቶች ከመስብህነት ባሻገር ነገ ሌሎች ጀግኖችን ለመፍጠር ዛሬ ያሉንን ጀግኖች የምናከብርበትና ለመጪው ትውልድ ህያው ታሪካቸውን አስቀምጠን የምናልፍበት አንዱ መንገድ ሐውልት ማቆም ነውና ይልመድብን።

# ዓለም አቀፍ

## ከአሜሪካ ሰማይ ተመትታ የወደቀችው የቻይናዋ ሰላይ ፊኛ መረጃ አልሰበሰበችም ተባለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በአሜሪካ ሰማይ ላይ ከታየች በኋላ ተመትታ እንድትወድቅ የተደረገችው የቻይናዋ ሰላይ ፊኛ ምንም ዓይነት መረጃ አለመሰብሰቧን ፔንታጎን አስታወቀ።

የስለላ ተግባር ስትፈጽም ነበር የተባለችው ፊኛ የሰበሰበችው መረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ የአሜሪካ የደኅንነት ተቋማት ስብርባሪውን በቅርበት ሲመረምሩ ቆይተዋል። የቻይና የስለላ ፊኛ በአሜሪካ ሰማይ መታየቷ እንዲሁም በፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ተመትታ እንድትወድቅ መደረጓ በቤይጂንግ እና በዋሽንግተን መካከል ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ቅራኔን ፈጥሮ ነበር።



የፔንታጎን ቃል አቀባይ ብርጋዲዬር ጄነራል ፓትሪክ ራይደር ትናንት ሐሙስ ለሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ሲናገሩ፤ «ፊኛዋ የደኅንነት መረጃዎችን መሰብሰብ እንደምትችል እናውቃለን» ብለዋል። «ይሁን እንጂ አሁን ባደረግነው ማጣራት አሜሪካን እያቋረጠች ወይም በአሜሪካ ሰማይ ላይ እየበረረች (ፊኛዋ) ምንም ዓይነት መረጃ አልሰበሰበችም» ብለዋል ቃል አቀባይ ብርጋዲዬር ጄነራል ፓትሪክ ራይደር።

ዎል ስትሪት ጆርናል በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት ይህ የቻይና በራሪ አካል የተሠራው አሜሪካ ሠራሽ ከሆነ ቁስ ጨምር ነው ብሏል። የፔንታጎን ቃል አቀባይ ግን በዚህ ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል። የቻይናዋ ፊኛ ተመትታ ከመውደቋ በፊት የካቲት ወር ላይ ለአንድ ሳምንት ያክል በአሜሪካ እና ካናዳ የአየር ክልሎች ላይ ስትበር ቆይታለች።

ፊኛዋ በመንገዷ በአሜሪካ የጦር ካምፖች በላይ በመብረሯ የደኅንነት መረጃዎችን ሳትሰበስብ አትቀርም የሚል ሰፊ ግምት ነበር። ቻይና ግን ፊኛዋ የደኅንነት መረጃዎችን የምትሰብሰብ ሳትሆን ለአየር ትንበያ የምርምር ሥራ የምትሠራ መሆኗን እንዲሁም ወደ ሰሜን አሜሪካ የሄደችው በንፋስ ኃይል ተገፍታ መሆኑን ስትገልጽ ቆይታለች።

ቻይና ይህን ትበል እንጂ አሁንም የቻይና ናቸው የተባሉ ሌሎች የስለላ ፊኛዎች በእስያ ሰማዮች ላይ ታይተዋል። ጃፓን ፊኛዎች በግዛቷ ሲበሩ መመልከቷን ያረጋገጠች ሲሆን፣ ወደፊትም ፊኛዎቹን መትታ ለመጣል መዘጋጀቷን ገልጻለች። ከጃፓን በተጨማሪ የቻይና ፊኛ በታይዋን ሰማይ መብረሯን የቢቢሲ ፓናሮማ ምርመራ አረጋግጧል።

ጃፓን የአሜሪካ የቅርብ አጋር ስትሆን ከሌሎች የውጭ ሀገራት በበለጠ በርካታ የአሜሪካ ኃይሎች በጃፓን ሰፍረው ይገኛሉ።

## የተመድ የጸጥታው ምክር ቤት የማሊን የሰላም አስከባሪ ተልዕኮ ለማቆም ድምጽ ሊሰጥ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የጸጥታው ምክር ቤት ላለፉት 10 ዓመታት በማሊ የዘለቀውን የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ለማቋረጥ ድምጽ ሊሰጥ ነው።

13 ሺህ ወታደራዊ ኃይል ያለው ተልዕኮ ከሁለት ሳምንታት በፊት «ሳይዘገይ» እንዲለቅ ተጠይቋል፡፡ የምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ወታደራዊ መንግሥት ከሁለት ሳምንታት በፊት 13 ሺህ ወታደራዊ ኃይል ያለው ተልዕኮ «ሳይዘገይ» እንዲለቅ ጠይቋል።

በ2021 ማሊ ከሩሲያው ዋግነር ቅጥረኛ ቡድን ጋር ትብብር ከጀመረች በኋላ፤ ሚኑሳ ተብሎ የሚጠራው የተመድ ተልዕኮ ጋር ውጥረት ውስጥ ገብታለች። ለዓመታት የዘለቀው ውጥረት የሰላም ማስከበር የአየር እና የምድር ሥራዎችን ለማቋረጥ የተገደደው የመንግሥት እገዳ ተከትሎ መሆኑን ሮይተርስ ዘግቧል።

የተባበሩት መንግሥታት ሰላም አስከባሪ ኃይሎች ሺዎችን የገደለውን የእስልምና አማጽያን ለመከላከል ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል ተብሏል።

ተልዕኮው ሲነሳ የሀገሪቱ የጸጥታ ሁኔታ ሊባባስ ይችላል ብለው የሰጉት አንዳንድ ባለሞያዎች፤ በቂ መሣሪያ ያልታጠቀው የማሊ ጦርና አንድ ሺህ የሚጠጉ የዋግነር ተዋጊዎች በሰሜንና በመሀል ላይ የሚገኙትን ግዛቶች የተቆጣጠሩ ታጣቂዎችን ይዋጋሉ።

የጸጥታው ምክር ቤት ዲፕሎማት «ይህ የማሊ ውሳኔ ነው። እና እሱን ተግባራዊ ለማድረግ ቢያንስ አሰቃቂ ያልሆነውን መንገድ መፈለግ አለብን» ብለዋል። የማሊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አብዱላዬ ዲዮፕ በዚህ ወር ለጸጥታው ም/ቤት እንደተናገሩት፤ በተልዕኮው እና በማሊ ባለሥልጣናት መካከል «የመተማመን ችግር» አለ ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው።




# መጋቢ አዕምሮ

# አእምሮን እንደ አዲስ መቀየር

አስናቀ ፀጋዬ

የአእምሮን እንደ አዲስ የማስተካከል ጉዳይ በጣም ወሳኝ ነው። ፈረንጆቹ ጋር ደግሞ ይህ በጣም የተለመደ ሀሳብ ነው። እንደውም /reprogram your mind/ or/reprogram your sub conscious mind/ እያሉ የተለያዩ ሀሳቦችን ያነሳሉ። ለመፍትሄዎችም የተለያዩ መጽሐፎችን ይፅፋሉ። ሴሚናሮችን ያዘጋጃሉ። ቪዲዮዎችን ይሰራሉ። በዚህም ሰዎች አእምሯቸውን እንደ አዲስ ይቀይራሉ።

ለምን መሰላችሁ? ኑሮ ያደክመናል። ሕይወት ተደጋጋሚና አሰልቺ ትሆናለች። አእምሯችን ብዙ መጥፎ ነገሮችን ይሸከማል። ቁጭት፣ ጭንቀት፣ ፍርሃት አለብን። በቃ! መጥፎ ስሜቶች በውስጣችን አሉ። ታዲያ እነዚህ ስሜቶች ከአእምሯችን ውስጥ መራገፍ አለባቸው። እንደ ልጅ ጥርት ያለ ሃሳብ ማሰብ አለብን። ንፁህ አእምሮ ያስፈልገናል። አእምሯችንን እንደ አዲስ ለማስተካከል ታዲያ ምን ማድረግ አለብን?



የመጀመሪያው አእምሮህ እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ አለብህ። ለምሳሌ ስልክ ነክቶ ለማያውቅ ሰው ዘመኑ የደረሰበትን የመጨረሻውን የስልክ ምርት አይፎን ሰርቲን ፕሮ ማክስ ገዝተህ ብትሰጠው ‹‹እንዴት የሚያምር የከበረ ድንጋይ ነው? ደሞ እኮ ልስላሴው›› ብሎ ቤቱ እንደተራ እቃ ሊያስቀምጠው ይችላል። ለምን አያውቀውማ! አእምሮህ ለምን እንደሚሰራና እንዴት እንደሚሰራ ካላወክ አጠቃቀሙን አታውቅበትም።

አንዳንዴ አእምሯችን እንዴት እንደሚሰራ ስለማናውቅ ስንጨነቅ መድኃኒት እንውጣለን። ትንሽ ነገር ሲገጥመን ‹‹ምነው ፈጣሪዬ ምን አደረኩህ›› እንላለን። ትንሽ ነገር ሲፈጠርና መጥፎ ስሜት ሲሰማን ፈጣሪን እናማርራለን። በቃኝ እንላለን። ተስፋ እንቆርጣለን። እኔ እኮ አበቃልኝ እንላለን። ሕይወትን ትርጉም እናጣበታለን። ለምን? የአእምሯችን አሰራር አልገባንም። አእምሯችን ነው የተጎዳው። እኛ ግን በአካል ሁሉ ነገራችን ይጎዳል።

አያችሁ የአእምሯችን አሰራር በጣም ወሳኝ ነው። ስለዚህ አንተ ሕይወትህን እየጠላሃት ያለኸው ምን አልባት አእምሮህ እንዴት እንደሚሰራ ስላላወክ ነው። ከዚህ በኋላ ግን መጨነቅ ማቆም አለብህ። መፍራት ታቆማለህ። መጥፎ ስሜቶችና ሃሳቦች አእምሮህን አይቆጣጠሩትም። አዕምሮህ እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ ብቻ ነው ካንተ የሚጠበቀው።

ሁለት አይነት የአእምሮ ክፍሎች አሉ። ንቁ /conscious/ እና ድብቅ /sub-conscious/ ይባላሉ። ንቁ /conscious የአእምሮ ክፍል በጣም ንቃት ውስጥ ሆኖ ነው የሚያገለግለው። ለምሳሌ አንድ ነገር አዲስ ከሆነ ንቁ ሆነን ነው የምንሰማው። አዲስ ነገር ስንለምድ ነቃ ብለን ነው የምናዳምጠው። ለመጀመሪያ ጊዜ ምግብ ያበሰላችሁ ጊዜ አንዳንዱን ሂደት በንቃት ነው የምንከታተለው። ኪ ቦርድ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንተይብ (ታይፕ ስናደርግ) እያንዳንዷን ፊደል እየመረጥን ነው።

ብዙ ጊዜ ግን በቀን ውስጥ አዲስ ነገር የምንለምደው ለጥቂት ሰዓታት ነው። ብዙ ሰዓት ንቁ አይደለንም። ስለዚህ ንቁ /conscious/ የሚባለውን የአእምሮ ክፍል ብዙ ጊዜ አንጠቀምበትም። ስለዚህ በጣም ወሳኙ ሁለተኛውና ድብቅ /sub-conscious/ የሚባለው የአእምሮ ክፍል ነው። ይህ የአእምሮ ክፍል ደጋግመን የምናደርጋቸውን ነገሮች የሚቆጣጠር የአእምሮ ክፍል ነው። በሰውነታችን ውስጥ ከሚካሄዱ እያንዳንዱ ሂደቶች ጀምሮ ለምሳሌ የምግብ ልማትና መተንፈስን ጨምሮ ማንኛውንም የሰውነት ሥርዓቶችን ይቆጣጠራል።

ይህን ብቻ ሳይሆን ልማዶቻችንን፣ ደጋግምን የምናደርጋቸውንነገሮችበሙሉድብቅ/sub-conscious/ ነው የሚቆጣጠረው። ለምሳሌ የኮምፒዩተር ኪቦርድ ላይ ስትፅፍ የሆነ ሰዓት ላይ መልመድ ትጀምራለህ። ስለዚህ ይህ ድብቅ /sub-conscious/ የሚባለው የአእምሮ ክፍል ማስታወሻዎችን ይመዘግባል። ስለሆነም በኪቦርዱ ላይ ኤ የቱ ጋር እንደሆነ ታውቃለህ። ወዲያው ሌሎቹንም ፊደሎች ትነካካለህ። ብዙ ነገሮች ላይ ፈጣን የምትሆነው ድብቁ የአእምሮ ክፍልህ ስለለመደው ነው። ስለዚህ ድብቁ የአእምሮ ክፍል ደጋግመን ያደረግነውን፣ ተደጋግሞ የሰማነውን፣ የተነገረንን፣ ደጋግመን ያየነውን ሕይወታችን ላይ መዝግቦ ያስቀራል። ዋናው የአእምሮ ማስታወሻ ክፍል ነው። በእሱ መንገድ እንድንጓዝ ያደርገናል።

ለዛ ነው አንዳንድ ልጅ በልጅነቱ አትችልም እየተባለ ተደጋግሞ ከተነገረው ትንሽ ከፍ ሲል አልችልም የሚል ስሜት ይሰማዋል። ስለዚህ አይሞክርም። አዲስ ነገር ላይ አይደፍርም። አንዳንድ ልጅ በልጅነቱ አንተ ጎበዝ ነህ ! ጀግና ነህ እየተባለ ያደገ ልጅ ደግሞ ደፈር ይላል። ብዙ ነገር ይሞክራል። ደጋግሞ የሰማውን በሕይወቱ ላይ ይገልጠዋል። በልጅነት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከፍ እያልን ስንሄድ አብረናቸው የምንውላቸው ጓደኞቻችን የሚነግሩን ነገሮች በእኛ ድብቁ የአእምሮ ክፍል ውስጥ ተመዝግበው ይቀራሉ። ድብቁ የአእምሮ ክፍል አብዛኛውን የሕይወታችን ክፍል ይወስናል።

ድብቁ /sub-conscious/ የአእምሮ ክፍል አንድ የተለየ ባህሪ አለው። ሞኝ ነው። ደጋግሞ የተነገረውን ነገር ያስቀራል። መቼም ሞኝ ታውቃላችሁ። የሆነ ነገር ካደረጋችሁት ‹‹እሱ እኮ እንዲህ አድርጎኝ›› ይላል። ቂም ነው የሚይዝባችሁ። ልክ ‹‹ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም›› እንደሚባለው። ሞኝ ውለታ ከዋላችሁለትም የሆነ ቀን አስታውሶ ‹‹እሱ እኮ እንደዚህ አድርጎልኝ›› ይላችኋል። በቃ! ድብቁ የአእምሮ ክፍል ልክ እንደሞኝ የሰበሰበውን፣ ደጋግሞ የሰማውን መዝግቦ ያስቀራል።

እንግዲህ ላዛ ነው አንተም የምትጨነቀው። አየህ! የሚያስጨንቁ ጉዳዮችን ደጋግመህ ትሰማለህ። ስለዚህ በሕይወትህ ትጨነቃለህ። የዘራኸውን ታጭዳለህ። የምትዘራው መጥፎ ጭንቀት፣ መጥፎ ሀሳብ፣ መጥፎ ነገር ከሆነ እሱ በሕይወትህ ይገለጣል። አሁንም የምትጨነቀው ለዛ ነው። ደስ የሚለው ነገር ግን ይህ ድብቁ የአእምሮ ክፍልህን መቀየር ትችላለህ። እንዴት አድርገህ? እየደጋገምክ ለአእምሮህ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን በመንገር። አዳዲስ ነገሮችን በአእምሮህ ውስጥ በመዝራት።

አእምሯችን እንደመሬት ነው። የሚዘራበትን መምረጥ አይችልም። መሬት አፍ አውጥቶ ስንዴ ዝሩብኝ አይልም። እኛ ሰዎች ነን መሬቱ ላይ የምንዘራው። ግን ደግሞ ስንዴ ፈልገን ስንዴ ከዘራን መሬቱ ስንዴ ያበቅላል። አእምሮህ አንተ የምትፈልገውን ነገር ነው የምትጭንበት። የምትሰማው ነገር ወሳኝ ነው። ጥሩ ነገር ከሰማህ በአእምሮህ ውስጥ ጥሩ ነገር እየዘራህ ነው።

አየህ! ከዚህ በኋላ አእምሮህን አዲስ ማድረግ አይደል ዓላማህ? ስለዚህ አእምሮህን የሚያስተካክል ነገር መስማት ትጀምራለህ። የምትሰማው ነገር መንፈሳዊ ነገር ሊሆን ይችላል። መልካም ነገር፣ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ሊሆንም ይችላል። ከዚህ ውጭ ግን ሌላ ነገር አትሰማም። ሌላ ነገር አታደርግም። ትጠነቀቃለህ። ለምትዘራው ነገር ተጠንቀቅ። የአእምሮ በርህን ጠብቅ። አየህ! ከዚህ በኋላ መጥፎ ዜና መስማት የለብህም። ለምን? መጥፎ እንድታስብ ያደርግሃል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በትዝታ መኖር ማቆም ይኖርብሃል። ምን አልባት ስለትናንት እየደጋገምክ ታስብ ይሆናል። ትላንት ስለደረሰብህ መጥፎ ነገር፣ ስለገጠመህ ቁጭት፣ በጣም የሚያስቆጨህን አጋጣሚዎች ታስባቸዋለህ። ጭንቀትህ ስለትናንት ነው። ስለዚህ ትላንትን በዛሬ ውስጥ እየኖርክ ነው ማለት ነው። አእምሮህ ደጋግመህ የምታስበውን ነው የሚሰጥህ። ትላንትናን ካሰብክ ትላንትናን ዛሬም ትደግመዋለህ። ሕይወት ተደጋጋሚ ትሆናለች። አሰልቺ ትሆናለች። የትናንቱን ዛሬም ትኖረዋለህ።

ታዲያ ምን ይሻላል? ነገን በዛሬ ውስጥ መኖር መጀመር አለብህ። ነገን እያሰብክ ዛሬ ላይ ጠንክር። ነገ በሕይወትህ ይገለጣል። አየህ! መልካም ነገሮችን ደጋግመህ ስታስብ መልካም ነገር በአእምሮህ ውስጥ እየዘራህ ስለሆነ መልካም ነገር በሕይወትህ ትገልጣለህ። የቀንም የሌሊትም ህልመኛ መሆን አለብህ። የቀን ህልመኞች መሆን በራሱ ሕይወታችንን ይቀይረዋል። ቀን ላይ ዝም ብለን ስንቀመጥ መልካም ነገሮችን ብናስብ ‹‹እንዲህ ባደርግ፣ ይሄን ባሳካ፣ ይሄ ቢኖረኝ›› ብንል አእምሯችንን መልካም ነገር እየመገብነው ነው።

ድብቁ የአእምሮ ክፍል አንተ ተኝተህም ይለፋል። አንተ የምትፈልገውን ነገር ለመስጠት የማያደርገው፤ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። አንዳንዴ ቁጭ ስትሉ ከሰው ጋር እያወራችሁ የሆነ ሃሳብ ብልጭ ብሎላችሁ አያውቅም? እርግጠኛ ነኝ ያውቃል። ምክንያቱም ድብቁ አእምሮ ደጋግሞ እያሰበ ነበር። አንተ ሌላ ነገር ውስጥም ብትሆን አእምሮህ መልሱን ሲያገኝ መስራት ይጀምራል።

አየህ! ስለነገ ህልምህና መልካም ነገር ካሰብክ የሆነ ሰዓት ላይ በሕይወትህ ድብቁ የአእምሮህ ክፍል ይገልጠዋል። ፈጣሪህም ተአምሩን የሚያሳይህ በድብቁ የአእምሮ ክፍልህ ነው። ታዲያ የቀን ህልመኛ ብቻ ሳይሆን የሌሊትም ህልመኛ መሆን አለብህ። ልትተኛ ስትል በጣም የምትፈልገውን ነገር አጥብቀህ እያሰብክ መተኛት አለብህ። እውቁ የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን ‹‹ልተኛ ስል በጣም ልፈታው የምፈልገውን ሳይንሳዊ ችግር እያስብኩት እተኛለሁ። እኔ ግን የማስበው ፈትቼዋለሁ ብዬ ነው። ጠዋት ስነሳ ግን ያን ችግር ፈትቼው፤ መፍትሄውንም አግኝቼው እነቃለሁ›› ይላል።

ስለዚህ የትኛውንም የዚህ ዓለም ችግር እንደፈታኸው አስበህ የምትኖር ከሆነ የሆነ ሰዓት መፍትሄው በሕይወትህ ይገለጣል። ድብቁ የአእምሮ ክፍል ስራውም ይህ ነው። ለዛ ነው የቀንም የሌሊትም ህልመኛ መሆን ያለብህ።

በሶስተኛ ደረጃ ውስጥህ ነው ወሳኙ። ወዳጄ! ውጫዊ ነገሮችና ውጫዊ ሁኔታዎች ያንተን ውስጣዊ ሰላምና ደስታ ሊወስኑት አይገባም። መፍቀድ የለብህም። ምክንያቱም ለምሳሌ ሰዎች ሲያደንቁህ ደስ የሚልህ ከሆነ፣ ፊት ሲነሱህ፤ የልባቸውን አውጥተው መጥፎ ነገር ሲናገሩህ አንተ የሚከፋህ ከሆነ ያንተን ውስጥ እየተቆጣጠረው ያለው ውጫዊ ዓለም ነው። ዓለም ስትገላበጥ ውስጥህ መገላበጥ የለበትም። ከውጭ ወደ ውስጥ መኖር ማቆም አለብህ። ከውስጥ ነው ወደውጭ መኖር ያለብህ።

ውስጥህ ሰላምና ደስታ ካለ ዓለም አብራህ ትስቃለች። አብራህ ትደምቃለች። ሕይወትህን የሚወስነው ውስጣዊ ነገር ነው። አየህ! መለወጥና መቀየር የምትጀምረው ከውስጥ ወደ ውጭ መኖር ስትጀምር ነው። አለበለዚያ ይች ዓለም አትሞላም። ስለዚህ ዓለም በተቀየረች ቁጥር ውስጥህ የሚቀየር ከሆነ መቼም ደስተኛ አትሆንም። ሕይወትህ ላይ ጭንቀቶችና መጥፎ ሀሳቦች የሚቆጣጠሩህ ውጫዊ ነገሮችን እያየህ ነው።

አየህ! እንደዛ እንዲሆን መፍቀድ የለብህም። አንተ ሁልጊዜም የሰው ልጅ ነኝ ብለህ ማመን አለብህ። ‹‹እኔ ሁልጊዜም ደስተኛ ነኝ፤ በፈጣሪዬም ደስተኛ ነኝ፤ ጤና ሰጥቶኛል›› በል። ያለህን እያየህ በውስጥ እርካታ ሊኖርህ ይገባል። ያኔ ውጭህም ያምራል።

በአራተኛ ደረጃ አካባቢህን ምረጥ። አንዳንዴ አንተ በጣም አቅም አለህ። በጣም ትችላለህ። ሕይወትህ ላይ የጎደለህ ነገር የለም። ፈጣሪህ የሰጠህ ብዙ ችሎታዎች አሉህ። ብቃትህን እንዳታወጣው ያደረገህ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አካባቢህም ሊሆን ይችላል። ታዲያ አእምሮህን እንደ አዲስ ማስተካከል የምትፈልግ ከሆነ መቆረጥ ያለበትን ቁረጥ። መቀጠል ያለበት ነገር ካለ ደግሞ ቀጥል። ከጥሩ ሰዎች ጋር ዋል።

አካባቢህ አንተን ይወስንሃል። ለምሳሌ ማድቤትህ ውስጥ ምግብ እያበሰልክ አንድ ሰው መጥቶ ቆሻሻ ቢደፋብህ ትተናነቀዋለህ። ለምን? ምግቡ ሆድህ ውስጥ ስለሚገባ ለምትበላው ታስባለህ። አእምሮህ ውስጥ ለሚገባው ነገርም ማሰብ መጀመር አለብህ። አእምሮህ ውስጥ መጥፎ ነገር፣ ቆሻሻ ለሚበትኑ ዜናዎች፣ ሃሳቦች፣ መጥፎ ሰዎች፣ እንደማትችል ለሚነግሩህ ሰዎች ቦታ መስጠት የለብህም።

አካባቢህን በደምብ አጥናው። ላንተ የሚመጥን ከሆነ አእምሮህ እንደ አዲስ መሰራት ይጀምራል። የምትሰማው ነገር በጣም ወሳኝ ነው። ሕይወትህ ላይ የሚገለጠውም ደጋግመህ የሰማኸው፣ ያደረከው፣ የምትውለው ቦታ ነው። የዛሬ አምስት አመት ያደረካቸው ነገሮች አሁን ያለህበትን ወስነዋል። የዛሬ አምስት አመት የምትደርስበትን የሚወስኑት ደግሞ አሁን የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህ አካባቢህን ምረጥ።

አምስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ የመደጋገም ኃይል ሲሆን ይህም ወሳኝ ነው። ከባድ ነገሮች ቀላል የሚሆኑት ከደጋገምናቸው ብቻ ነው። አንድን ነገር ደጋግመን ስናደርገው አእምሮን ያንን ነገር ቀለል አድርጎ ለመስራት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። በአእምሮን እየደጋገምን አንድን ነገር ስንሰራ በቀላሉ ነገሩን እንድንከውን ጥርጊያ መንገድ ያመቻቻል።

ስለዚህ የመደጋገም ኃይል ወደሕይወታችን እንዲገባ ማዳበር አለብን። አንተ የምትደጋግመውን ነው ህይወትህ ላይ ምታገኘው። ደጋግመህ የምትሰማውና የምታየው ነገር በጣም ወሳኝ ነው። ስለዚህ በእጅ በእግርህ ብለህ አእምሮ ማሰብ ያለበትን እንዲያስብ አድርግ። እየደጋገምክ ለአእምሮህ ጥሩ ነገር ንገረው።

# መሠረተ ልማት

## ለትውልድ የሚተላለፉ የግንባታ ተቋራጮችን የማፍራት ግብ

አንተነህ ቸሬ

የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ችግሮች ጠቅለል ተደርገው ሲገለፁ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜና ዋጋና እንዲሁም በሚፈለገው ጥራት አለማጠናቀቅ በሚለው ክፍተት ላይ የሚያርፉ እንደሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። በተለይ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች ከዚህ አኳያ ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አስተዳደር (ማኔጅመንት) ችግር እንዳለባቸው ይጠቆማል። የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአቅም ክፍተቶች ይስተዋሉበታል፤ ዓለም አቀፍ የገበያ ተለዋዋጭነት፣ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች መማር አለመቻል፣ ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ እንዳይሆን አድርገውታል፡፡

የዘርፉን ችግሮች በጥናትና ምርምር በመታገዝ የመፍታትና የግንባታ አስተዳደርን የማሳደግ ኃላፊነት የተሰጠው የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትም (Construction Management Institute) ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ከ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ታምራት ሙሉ ያስረዳሉ፡፡

### የ'ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት' ምንነት

‹‹ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት›› ማለት አንድን ግንባታ በጊዜ፣ በዋጋ እና በጥራት መምራት፣ ወይም ግንባታን ጊዜውንና ጥራቱን ጠብቆ በተያዘለት ጊዜና የውል ዋጋ ማጠናቀቅ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ግብ ፕሮጀክቶችን በዋጋ፣ በጊዜና በጥራት ማጠናቀቅ ነው፡፡

### የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ተግባራትና ኃላፊነቶች

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በደንብ ቁጥር 289/2005 የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንትን ማሳደግን ግብ ካደረጉ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ኃላፊነቶችና ተግባራት መካከል የፖሊሲ ግብዓቶችን በማመንጨት እንዲተገበሩ ማድረግ፤ ተግባር ተኮር የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ሥልጠናዎችን መስጠት፤ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች ዓለም አቀፋዊ ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ የሚያደርግ የምዘናና የብቃት ማረጋገጫ (ሰርቲፊኬሽን) እንዲኖር ማመቻቸት፤ ለኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እድገት የሚረዱ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉና እንዲሰርፁ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ተቋራጭ፣ አሰሪ እና አማካሪ በተደራጀ መልኩ የሚሠሩበትን የአሠራር ሥርዓት እያጠኑ እንዲተገበር ማድረግ፤ በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዘርፍ የማማከር አገልግሎት መስጠት፤ በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዘርፍ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ ለኮንስትራክሽን እድገት አስተዋፅዖ የሚያደርጉ መረጃዎችን እያሰባሰቡና እየመዘኑ ለዘርፉ ግብዓት እንዲሆኑ ማድረግ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚስተዋውቁና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያተኮሩ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን መስጠት፣ ተመሳሳይ ተግባር ካላቸው የግልና የመንግሥት ተቋማት በትብብር መሥራት፣ ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲቀመሩ ማድረግ፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እድገት አስፈላጊ የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወንና ተቋማቱ የጥናትና ምርምር ማዕከላት እንዲሆኑ ማገዝ የሚሉትም የኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊነቶቹና ተግባሮቹ ናቸው፡፡

ኢንስቲትዩቱ በሰንዳፋ ከተማ የልህቀት ማዕከል እያስገነባ ነው፡፡ ማዕከሉ ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ትልቅ ተቋም ስለሚሆን ማዕከሉን ማስተዳደር በተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ ይካተታል፡፡ የልኅቀት ማዕከሉ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የሰው ኃይል ማበልፀጊያ ተቋም ነው፡፡ ማዕከሉ ግንባታዎች ሳይፈርሱ የግንባታ ጥራትን ለመፈተሽና ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሠራሮችና መሣሪያዎች (Non-Destructive Testing Methods) እንዲሁም የጥራት ማረጋጋጫ



ኢንጂነር ታምራት ሙሉ፣

ተግባራት የሚከናወኑባቸው የቤተ-ሙከራ ማዕከላት ይኖሩታል፡፡

የማዕከሉ ግንባታ በሁለት ምዕራፎች የሚከናወን ሲሆን፣ የመጀመሪያውን ምዕራፍ በሦስት ዓመታት፣ ቀሪውን ደግሞ በሁለት ዓመታት በማከናወን ማዕከሉ ከአምስት ዓመታት በኋላ በሙሉ አቅም ሥራ እንዲጀምር ይደረጋል፡፡ የግንባታው 17 በመቶ ሥራ በ2016 ዓ.ም ይጠናቃል ተብሎ ታቅዷል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ተዘጋጅቶ ለመንግሥት የቀረበው የተቋሙ የደንብ ማሻሻያ፣ ኢንስቲትዩቱ የምዘናና የብቃት ማረጋገጫ ሥራውን ከማመቻቸት ባለፈ በራሱ የምዘናና የብቃት ማረጋገጫ ሥራ እንዲያከናውን ይጠይቃል፡፡

### የኢንስቲትዩቱ የበጀት ዓመቱ ዋና ዋና ተግባራት

ኢንስቲትዩቱ በዘንድሮው የበጀት ዓመት በኢንዱስትሪው ውስጥ በሥራ ላይ ለሚገኙ 2442 ተቋራጮች፣ አማካሪ መሐንዲሶች ሌሎች የዘርፉ ተቋማት ባለሙያዎች ተግባር ተኮር ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ ይህ ሥልጠና የፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅምን በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ የሚያግዝ ነው። የምንመድባቸው አሠልጣኞች በዘርፉ በቂ ልምድና ዝግጅት ያላቸው ናቸው፡፡ ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከ20ሺ በላይ ለሚሆኑ ባለሙያዎች ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ሰጥቷል፡፡

ለ180 ባለሙያዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ (Project Management Professionals) እንዲሆኑ የሚያስችላቸውንና ዓለም አቀፍ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ዕድል የሚፈጥርላቸውን ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ ባለፈው ዓመት ይህ ሥልጠና ለ120 ባለሙያዎች ተሰጥቶ ነበር፡፡

ኢንስቲትዩቱ በ2015 የበጀት ዓመት ያከናወነው ሌላ ተግባር የ‹ቢም› (Building Information Modeling) ቴክኖሎጂ ስልጠና ነው፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ የዲዛይን ሥራዎችን በማስተባበር የጊዜና የገንዘብ ብክነት እንዳይኖር የሚያደርግ ነው፡፡ በተለያዩ ባለሙያዎች የሚሠሩ የዲዛይን ዝግጅት ሥራዎች የተናበቡ እንዲሆኑ ለማድረግ ቁልፍ ሚና ያለው ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ዘንድሮ 243 ባለሙያዎች ሥልጠናውን ወስደዋል፤ ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከ400 በላይ ባለሙያዎችን በ‹ቢም› ቴክኖሎጂ አሰልጥኗል፡፡ አማካሪ መሐንዲሶችን ጨምሮ የዘርፉ መንግሥታዊ ተቋማት ባለሙያዎችና የዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ሥልጠናውን ወስደዋል፡፡ ቴክኖሎጂው የተበላሸውን የኢንዱስትሪውን ገፅታ ለመገንባት እና ሥራን በእውቀት ለመምራት ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡

የኮንስትራክሽን ዘርፉ እየተመራ ያለው ባለሙያዎች ተመዝነው ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ ስላልሆነ የብቃት ምዘና መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ መመሪያው ሲጸድቅ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ባለሙያዎች በጥንቃቄ በሚዘጋጅ የፈተና ሥርዓት አማካኝነት ብቃታቸው ይመዘናል፤ ለፈተናው የሚያግዙ ግብዓቶችም እየተዘጋጁ ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የኮንስትራክሽን ዘርፉን ለማዘመን የሚያግዙ የአሠራር ሥርዓቶችንም ያስተዋውቃል። ለአብነት ያህል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና ሃሳቦችን ይዘው የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን የሚያበረታቱ እንዲሁም የሥራ ቅብብሎሽ እንዲኖር የሚያስችሉ አሠራሮች የሚመሩባቸውን መመሪያዎችን አዘጋጅ ቷል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከሰባት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር አንድ ባለሙያ ከረዳቶቹ ጋር ሆኖ በቀን ምን ያህል ሥራ መሥራት እንደሚችል የሚያመለክት የምርታማነት መለኪያ (Productivity Norm) እያዘጋጀ ነው፡፡ ኢንስቲትዩቱ የምክር አገልግሎቶችንም ይሰጣል፡፡ በቂ ባለሙያ ለሌላቸው ተቋማት የሙያ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ኢንስቲትዩቱ ለብዙ ተቋማት ሥራዎች ሙሉ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን አከናውኗል፡፡

የተቋማት ፕሮጀክት የመምራት ደረጃን (Organizational Project Maturity) የማሳደግ ሥራ በዚህ ዓመት የተከናወነ ሌላው ተግባር ነው፡፡ ይህ አሠራር በዓለም አቀፍ መመዘኛ አምስት ደረጃዎች አሉት፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ (በተቋማት ፕሮጀክት የመምራት ደረጃ) የምትገኘው ከአንድ እስከ ሁለት ባለው ወሰን ውስጥ ነው፤ ይህም አነስተኛ የሚባል ነው፡፡ ይህን ደረጃ በ10 ዓመት ውስጥ ወደ አምስት/አራት ለማድረስ የታቀደ ሲሆን፣ በአምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ሦስት ለማድረስ እየተሠራ ነው፡፡ ለዚህ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ተዘጋጅተው የአሠልጣኞች ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ከተቋማት ኃላፊዎች ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የመሠረተ ልማት ቅንጅት እጦት እያስከተለ ያለውን ችግር በማጥናት በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ከተሠማሩ ተቋማት ጋር ውይይት አድርጓል፤ ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆን ቴክኖሎጂንና አማራጭ የግንባታ ግብዓቶችን (ለምሳሌ ከአፈር የሚሠሩ ብሎኬቶችን) አስተዋውቋል፡፡ ተቀባይነት ያገኙት ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች ደግሞ ብሔራዊ ደረጃ (National Standard) እንዲወጣላቸው እየሠራ ነው፡፡ የ‹‹ቢም›› ቴክኖሎጂ አስገዳጅ ብሔራዊ ደረጃ እንዲኖረው የሚያስችሉ ግብዓቶች ተሟልተው ደረጃው ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ቀርቧል፤ በቅርቡ ይፀድቃል ተብሎም ይጠበቃል፡፡

### የሀገር በቀል ተቋራጮች አቅምና ችግሮች

የሀገር በቀል ተቋራጮች ከዚህ ቀደም በጥሩ እድገት እየተጓዙ የነበረ ቢሆንም መልሰው ተዳክመዋል፡፡ የእውቀትና፣ የአደረጃጀት ችግሮች አሉባቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ተወዳዳሪ መሆን አልቻሉም፡፡ ለዚህ ችግር ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል አንዱ ተቋማቱ በኮርፖሬት ደረጃ የተደራጁ አለመሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት በአንድ ግለሰብ ስም ተሰይሞ፣ ግለሰቡ ሁሉንም ኃላፊነት ይዞ ሥራ ይጀምራል፡፡ ግለሰቡ በሆነ ምክንያት ሥራውን ሲያቆም ድርጅቱም አብሮ ይከስማል፡፡ ተቋማቱ የአንድ ሰው ተቋማት ሳይሆኑ የኮርፖሬት አሠራር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሰውየው ኖረም አልኖረም ተቋማቱ እንዲቀጥሉ የእውቀት ሥራ መሥራት ይገባል፡፡

የኮርፖሬት አሠራር ስልት (Corporate Culture) አንድ ተቋም በአንድ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ሥርዓት ባለው አሠራር (System) ሥራውን እንዲያከናውን የሚያስችል ነው፡፡ ይህ ስልት ዝርዝር የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋትና ውሳኔዎች በተገቢው ጊዜ እንዲወሰኑ በማስቻል፣ የፕሮጀክት አፈፃፀም ውጤታማና ተወዳዳሪ እንዲሆን ያደርጋል።

ክፍያዎች በተገቢው ጊዜ አለመከፈላቸው ተቋራጮቹን አዳክሟቸዋል፡፡ ሥራ ለማግኘት ሲባል ብቻ አዋጭ ያልሆነ (በጣም ዝቅተኛ) ዋጋ ያቀርባሉ። ገበያን በሚገባ አጥንቶ ለፕሮጀክት የሚመጥን ዋጋ ያለማቅረብ ችግር አለ፡፡ ይህ ደግሞ ሥራው እንዳይሠራና ሀገርም ኪሳራ እንዲገጥማት ያደርጋል፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ጎድቶታል፡፡

ስለሆነም ‹‹ተቋራጮቹ ለሥራው የሚመጥን ዋጋ አስገብተዋል ወይ?›› የሚለውን ጉዳይ በጥንቃቄ መመልከት ይገባል፡፡ የግዥ ሥርዓቱ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ እንዲያሸንፍ ዕድል የሚሰጥ (Least Evaluated Bid) ነው፡፡ ይህ የግዥ ሥርዓት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለብዙ ዓመታት የቆዩና ልምድ ያላቸው ተቋራጮች ከሥራ እንዲወጡ አድርጓቸዋል። ስለሆነም ‹ተቋራጮቹ ለሥራው የሚመጥን ዋጋ አስገብተዋል ወይ?› የሚለውን ጉዳይ በጥንቃቄ መመልከት እና የግዥ ሥርዓቱን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

የውጭ ሀገራት የሥራ ተቋራጮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሥራ በሚጀምሩበት ጊዜ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች ወሳኝ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንዲያሳተፉ የሚያስችል አሠራር (Joint Venture System) ተዘጋጅቷል፡፡ በ10 ዓመት ውስጥ በሀገር ውስጥ ከሚወጡ ዓለም አቀፍ ጨረታዎች መካከል 75 በመቶው የሀገር ውስጥ ተቋራጮች የገበያ ድርሻ እንዲኖራቸው ታቅዷል፡፡

ኢንጂነር ታምራት ‹‹የሀገር ውስጥ ተቋራጮች የአቅም ክፍተት አለባቸው፡፡ ክፍተቶቻቸውን ለማስተ ካከልም የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ለሥራ ተቋራጮች በብዙ ዘርፎች ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል። የእኛ ሀገር የሥራ ተቋራጮች የ10 ዓመት ብቻ ታሪክ ባለቤት እየሆኑ ነው፡፡ ለትውልድ የሚተላለፉ ተቋራጮችን ማፍራት አለብን ብለን እየሠራን ነው›› ይላሉ፡፡

ከዚህ ቀደም የሥራ ተቋራጮችን አቅም ለመወሰን ተቋራጮቹ ያላቸውን ማሽኖችና ሌሎች መሣሪያዎችን ከግምት ውስጥ የማስገባት አሠራር ይተገበር ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ተቋራጭ እውቀቱ ካለው ማሽኖችን ተከራይቶ እንዲሠራ በማድረግ ተቋራጩ ያለውን አቅም ለሀገር ልማት መጠቀም ይቻላል፡፡ ብዙ አቅም ያላቸው ባለሙያዎች፣ ማሽኖች ስለሌሏቸው ብቻ ለብዙ ዓመታት ተቀጣሪ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ተቋራጭ የሁሉም ማሽኖች ባለቤት ሊሆን እንደሚገባ የሚያስገድደው መስፈርት አስገዳጅ መሆን እንደሌለበት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ያለውን ሀብት በአግባቡ የሚያስተዳድር የአሠራር ሥርዓት መፍጠርም አስፈላጊ ነው፡፡ ተቋራጮችን አቀናጅቶ ማሠራት በጣም ይጠቅማል፡፡ ትልቅ የአመለካከት ችግር አለ፡፡ የጥቅም ግጭትና ቅሬታ እንዳይፈጠርም የሚገኘውን ትርፍ ተቋራጮቹ በሥራው ላይ ባላቸው አበርክቶ መሠረት በማስላት መከፋፈል ይገባል፡፡

‹‹በባለሙያ እየተመሩ ያሉ ተቋማት አሉ፤ በባለሙያ የማይመሩ ተቋማትም አሉ፡፡ በአመዛኙ ግን የኮንስትራክሽን ዘርፉ በባለሙያ እየተመራ አይደለም›› የሚሉት ኢንጂነር ታምራት፣ ‹‹አሠራራችንን ፕሮፌሽናሊዝምን የሚጋብዝ ከሆነ፣ አሳማኝ ያልሆነና ዘርፉን የሚጎዳ ዋጋ ይዘው የሚቀርቡ ተቋራጮችን ከጨዋታው ውጪ የምናደርግበት አሠራር ከተፈጠረ፣ የሚጠየቁት የምዘና መስፈርቶች የተቋማትን ብቃት መመዘን የሚያስችሉ ከሆኑ፣ ልምድ ያላቸው፣ በኢንዱስትሪው ላይ ብዙ ዋጋ የከፈሉ ፣ ሀገርን ሊገነቡ የሚችሉ ከገበያ የወጡ ተቋራጮች ወደ ገበያው ሊመለሱ ይችላሉ›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

### ቀጣይ እቅዶች

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ዘርፉን ለማሳደግ በቀጣዩ በጀት ዓመት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ባለሙያዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውንና ዓለም አቀፍ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ዕድል የሚፈጥርላቸውን ሥልጠና አጠናክሮ መቀጠል አንዱ ነው፡፡ በዚህም 180 ለሚሆኑ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ለሚመሩ ተቋማት ባለሙያዎች ይህ ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ከተለያዩ ተቋማት ለተውጣጡ 200 ባለሙያዎች የ‹ቢም› እና ለሦስት ሺ 800 የዘርፉ ባለሙያዎች የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሥልጠናዎች የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ለአንድ ሺ ባለሙያዎች የብቃት ምዘናና ማረጋገጥ ሥራ ለመሥራት አቅዷል፡፡ የልኅቀት ማዕከሉን 17 በመቶ ግንባታውን ማጠናቀቅም የኢንስቲትዩቱ የቀጣዩ ዓመት እቅድ ነው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከማዕድን ዘርፉ በሚገባ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ ርምጃዎች ይጠናከሩ!

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ወደ ብልጽግና ለምታደርገው ግስጋሴ መሠረታዊ አቅም አድርጋ የምትጠቀመው የሰው ኃይሏን እና የተፈጥሮ ሃብቷን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተፈጥሮ ሃብት በባሕሪው አላቂ እንደመሆኑ በአግባቡ እና በቁጠባ ሊጠቀሙበት ካልተቻለ የሚፈለገውን ሀገራዊ ፋይዳ ሳያበረክት አለሁ እያለ ማምለጡ አይቀሬ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብቷ በተለይም በከበሩ ማዕድናት የበለጸገች ናት፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ኢትዮጵያ በወርቅ፣ በኦፓል፣ በጀሶ ድንጋይ፣ በድንጋይ ከሰል፣ በዕምነበረድ፣ በፖታሽ፣ በታንታለም፣ በብረት፣ በነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ፣ እና ሌሎች ማዕድናት የታደለች አገር ናት፡፡ በዚህ መልኩ በጥናት የተለዩ ብቻ ሳይሆኑ፤ ገና በጥናት እየተለዩ ያሉ በርካታ ማዕድናት ስለመኖራቸውም ነው የሚገለጸው፡፡

ይሄንን ፈጣሪ ያደላት ሃብቷ ደግሞ አላት ከመባል የዘለለ በአግባቡ አልምቶ መጠቀምን በእጅጉ የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ከለውጡ ማግስት እንደ ሀገርም ዘርፉን እንደሚመራው ተቋምም ኢትዮጵያ ከማዕድን ዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ተነድፈው፤ አቅጣጫዎችም ተቀምጠው ወደሥራ ተገብቷል፡፡

ከተቀመጡ አቅጣጫዎች መካከል የወጪ ንግድ ማዕድናትን በዓይነትም በመጠንም ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፤ ለሀገር ውስጥ የማዕድን ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ማዕድናትንም በሀገር ውስጥ መተካት አቅጣጫዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ሂደትም ዘመናዊ የማዕድናት ግብይት ሥርዓት መዘርጋት ቁልፍ ተግባር ተደርጎ ተወስዷል፡፡

በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ መሠረትም፣ የማዕድን ዘርፉ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የሀገራዊ ልማቱ አቅም እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ ይሄን ሚናውን እንዲወጣ ከሚደረግባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ማሳደግ ሲሆን፤ ለዚህም የማዕድን ምርቱን ማሳደግ እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

ለአብነት፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ እና የባሕላዊ አምራቾችን በመደገፍ ጭምር በ2012 በጀት ዓመት ይመረት የነበረውን ሦስት ነጥብ ሁለት ቶን ወርቅ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 137 ቶን የማድረስ፤ በዚሁ ልክ የውጪ ምንዛሪ ግኝት ድርሻውን የማሳደግ ዕቅድ ተይዟል። ከዚህ አኳያ በማዕድን ዘርፉ ላይ የተወሰዱ ዘርፈ ብዙ ተግባራት አበረታች ውጤት እያሳዩ ብቻ ሳይሆን ከፍ ያለ የውጭ ምንዛሪን እያስገኙም ጭምር ነው፡፡

ይሁን እንጂ ዛሬም ድረስ ዘርፉን በእጅጉ እየተፈታተነው የሚገኘው የማዕድናት ሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ ሲሆን፤ ይሄም በሀገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች ላይ ጎልቶ የሚስተዋል ነው፡፡ ሂደቱም ሀገር ከዘርፉ የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ እያደረጋት ይገኛል፡፡

ለምሳሌ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቀደም ሲል በባሕላዊ መንገድ እንኳን እየተመረተ በሳምንት እስከ አስር ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ይደረግ ነበር፡፡ በክልሉ ሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ እየተበራከተ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በሳምንት ሁለት ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ያልተቻለበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር፡፡

ይሄ ሐቅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብቻ አይደለም፤ በኦሮሚያም፣ በደቡብም፣ በጋምቤላም፣ በሲዳማም፣ በሁሉም ክልሎች ያለ ነው፡፡ ይሄ ሕገወጥ ተግባር ደግሞ በተለያየ ቪዛ ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ የውጪ አገር ዜጎች፣ እንዲሁም ለግል ጥቅማቸው በሚለፉ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ባሉ አካላት ጭምር የታገዘ፤ በሕጋዊ የኢንቨስትመንትና ንግድ ሽፋን የሚደረግለትም ነው፡፡

በዚህ መልኩ በሚፈጸም ሕገወጥ የማዕድናት ዝውውር ታዲያ ሀገር እንደ ሀገር ካላት ሃብት ተጠቃሚ እንዳትሆን ብቻ ሳይሆን፤ ሂደቱ ጥቂት ሕገወጦችን ማዕከል አድርጎ የሚዘወር እንደመሆኑ በሕጋዊ መንገድ በዘርፉ የተሠማሩ አካላትንም የልፋታቸውን እንዳያገኙ አድርጓቸዋል፡፡

ለምሳሌ፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ክልሉ በ2014 በጀት ዓመት 2ሺ300 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ገቢ አድርጓል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ ሦስት ሺ ዘጠኝ ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ለማድረግ አቅዶ ወደ ሥራ ቢገባም፤ በክልሉ በተንሰራፋው ሕገወጥ የማዕድን ማውጣትና ኮንትሮባንድ ንግድ ምክንያት በበጀት ዓመቱ መገባደጃ ድረስ ከ482 ኪሎ ግራም መሻገር አልቻለም፡፡

ይሄ ደግሞ ችግሩ ምን ያህል ስር እንደሰደደ እና ሀገር ዋጋ እየከፈለች ስለመሆኑ አንድ ማሳያ እንደመሆኑ፤ ችግሩን መከላከል እና ከመሠረቱ ምንጩን ማድረቅ ተገቢ ነው፡፡ መንግሥትም ይሄንን ለመግታት የሚያስችሉትን ተግባራት እያከናወነ ሲሆን፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተለያዩ አከባቢዎች በሕገወጥ የወርቅ ማውጣት እና ኮንትሮባንድ ግብይት ላይ የተሠማሩ የውጭ አገር ዜጎችን ጨምሮ፣ ተባባሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡

ይሄን ተከትሎ በተወሰደ ሰፊ ኦፕሬሽንም መጠኑ ከፍ ያለ የወርቅ ማዕድን ከየሱቁ፣ ከየመኖሪያ ቤቱና ሌሎችም ስፍራዎች እየተያዘ ይገኛል፡፡ ይሄ ርምጃ ሕገ ወጦችን ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደረገ ጅምር ተግባር ሲሆን፤ በሕገወጦች ከሀገርና ሕዝብ ጉሮሮ ተነጥቆ ለኮንትሮባንዲስቶች ሲሳይ ሲሆን የቆየው የሀገር ሃብትም ወደ ብሔራዊ ባንክ ቋት እንዲመለስ ዕድልን የሰጠ ነው፡፡

በዚህም በክልሉ አሁን ላይ በሳምንት ከአስር ኪሎ ግራም በላይ ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ እንዲገባ አስችሏል፡፡ ይሄ ጅምር ከወዲሁ ያሳየው ውጤት ደግሞ ሀገር ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ከማስቻል አኳያ ሕገወጥ ተግባሩን መቆጣጠር እንዲሁም የግብይት ሥርዓቱን ማዘመን ተገቢ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም ሀገር ከማዕድን ሃብቷ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያስችሉ ርምጃዎችን የመውሰድ ተግባሩ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሰርቶ መክበር እንደሚቻል ምስክር የምትሆን ሀገር በጋራ እንፍጠር

በመኩሪያ አለማየሁ

**«በኢትዮጵያ እጅግ ያማሩ ደመግቡ፣ ቆንጆዎችና ውብ ሰዎች አሉባት። ርህራሔ ያላቸውም እንደ እግዚአብሔር ነው። በመንገድ ለሚያልፍ የሚሆን ሰው ድግስ ያዘጋጃሉ። ምንም ቢሆን መንገደኛ የሚበላውን አያጣም። በዕድሜያቸው ከመቶ እስከ መቶ እስከ መቶ ሃያም እስከ መቶ ሰላሳም ይኖራሉ። ነውርና ክፉ ነገር በራሳችው የተጠላ ነው። የጤና ምንጮች የሆኑ የውሃ ወንዞች አሏቸው። በጠጣቸው ጊዜም ሰውነታቸው ይታደሳል፤ በሀብትም እጅግ የበለጸጉ ናቸው»**

**- ስለ ትናንታችን ሔሮዶቶስ በአንድ ወቅት ያለው ።**

እውነት ብሏል፤ ሥጋዊ ውበትና ደምግባት ከኑሮ (ከማዕድ) ይመጣል። ለራስ ተርፎ ለመንገደኛም የሚበላውን ደግሶ ማዘጋጀት ከልብ ደግነትና የሚሰጡትን ካለማጣት ይገኛል። የሀገሩን ማለት የሕዝብን ኑሮ « በሀብት እጅግ የበለጸጉ ናቸው» ሲል ምን ያህል ዘመኑ ፍትሐዊ እንደነበር ያሳያል። በዛ ዘመን ሕዝቡ በርህራሔ የተሞላና ነውርና ክፉ ነገርም በኑሮ ዕሴቱ የተጠላበት ሲል ለዛሬ ማንነታችን ትልቅ ማስተማሪያ ነው። በጊዜው ሌብነት/ ሙስና/ የተጨማለቀ ዘመን ቢሆን አይደለም ለሌላ ሕዝብ ለራስን አይተረፍም ነበር። ሀገር ከሙስና ሲጸዳ ሕዝብ ሔሮዶቱስ በገለጸው ይዘት ይገኛል።

ዛሬ ላይ ሙስና በሀገር ላይ ስለገነነ፤ በዕድገትና በሥልጣኔ ለጎረቤት ሀገሮች ምሳሌ መሆን አይደለም የሕዝቡ ኑሮ ሙሾው ዕለት ተዕለት መራር ዜማ ሆነ። በዚህ ሀገር ላይ ሙስናን በመዋጋት ህልውናውን ከስሩ መንግሎ መጣል ወይም በማሽመድመድ መፍትሔ ማምጣት በራሱ ብዙ ሜጋ ፕሮጀክቶችን የማሳካት ያህል ያስቆጥራል። ሌብነትን እንደባሕል ለማሳደግ የምንለማመድበት፤ የሰረቀን ጠላት የገደለ ያህል የሚወደስበት፤ ሌቦችና ግብራበሮቻቸው በስራቸው የሚኮሩትን የምናበረታታ እንመስላለን። ሰርቶ ከማግኘት፤ ነግዶ ከማትረፍ ይልቅ በቁም ገድሎ ከትውልድ የሀገር ሀብት የሰበሰቡትን ምድር ላይ ከሚኖሩበት ተርፎ ለሰማይ ቤታቸው የሚስፈልግ የሚመስላቸው ሙሰኞች ሞልተውናል።

ይህ የመሰለ የሌብነት ሥርዓት በዚህ ሀገር ላይ የተፈጠረው በብዙ ምክንያት ነው። ለምሳሌ ሥልጣን ሀገርና ሕዝብን በቅን ልቡና ከማገልገል ውጭ የሀብት ምንጭ ሲሆን፤ በዝባዥ የሆኑ ባለሀብቶች ሀገርን ለከፍተኛ ብልጽግናቸው መሠረት ሲያደርጓት፤ ምሁራኑ በጥበባቸው የሀገር ችግር ከመፍታት ይልቅ የገንዘብ ማግኛ መሳሪያ ሲያደርጉ ነው። የሀገሬ ሰው አንድ ትልቅ ብሒል አለው። «ባዶ ቂጡን ያደገ ሱሪ ሲገዛ ይኖራል።» ይላል። በዚህ መንገድ መጥቶ በሙስና የተዘፈቀ ሰው በአንድ ጣት ለሚቆጠር ዕድሜው ያለውንና የመጪውን የትውልድ ሀብት በየሰው ሀገር ካዝና የሚያከማች አለ። እንደባለተረቱ የትናት ድኅነቱን አብዝቶ ስለሚፈራ ነው። ለዚህም እንደነብር ጅራት ከያዘ አለቅ የሚለው።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው የትናንት ድኅነቱን ስለሚፈራ ዛሬ በእጁ ያለውን ከበቂ በላይ ሀብት እንኳ ቢይዝም አይጠግብም። ፍርሃቱ ደግሞ ልክ እንደአህያዋ ነው። ‹ አህያዋ በለስ ቀንቷት አንጀቷን ዘርግፎ ራት የሚያደርጋት ጅብ አንገቱን ነክሳ ብትገደለው እንኳ መንከሷን አታቆምም አሉ። ታዲያ አሳዳሪዋ ብረት (ጉጠት) አግሎ አፏን አስነክቶ በማስለቀቅና የሞተውን ጅብ አርቆ ጥሎ ነው ነጻ የሚያወጣት። አልያ ጅቡ ተነስቶ የሚበላት ነው የሚመስላት። በዚህች ሀገርም ብዙ ሙሰኞች እንዲህ ስለሚመስሉ መስረቅ ቢያቆሙ ድኅነታቸው እንደጅቡ ዞሮ የሚዘነጥላቸው ስለሚመስላቸው የገንዘብና የንብረት ጥም አልቆርጥ የሚል የሙስና ሱስ ውስጥ ይዘፈቃሉ። በዚህ አካሄዳችን ከቀጠልን ነገ የሙስና ማገገሚያ /እንደሱስ ማገገሚያ ሳያስከፍትልን አይቀርም።

ሙሰኛ ሰው በሀገሩ ለምን ተፈጠረ ቢሉ ሃይማኖተ ቢስና የሰውነት ደረጃ ላይ ያልደረሰ ሰብዕናን ገንዘብ ያደረገ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል። ሰውነት ከሌለ ደግሞ ሙትነት ይነግሳል። ለዚህ እኮ ነው ሊቃውንቱ ‹ሙስና መሞት፣ መበስበስ ነው› የሚሉት። በሙስና ሰበብ ለሚንገላታ፣ ለሚራብ፣ ለሚታረዝ፣ ለሚሰደድ--- ሕዝብ ድርሻውን በመስጠት ከእርኩሰት መንጻት ይቻላል። ሙስና የግለሰብንና የሀገርን ሀብት የሚነጥቅ እንጂ የሚለግስ እጅ የለውምና የባለሙሰኞች እጅ እንዲሰበስቡ ማድረግ ሀገርን ከድህነትና ከጥፋት መታደግ ይቻላል። አልያ የሙስና ሀገር ማሕጸኗ ሰፊ በመሆኑ በቃኝን ስለማታውቅ ለዕድገትና ለብልጽግና የሚደረግ መንገድ አይኖርም።

ይህ ክፉ ግብር መግታት የሚቻለው ደግሞ በሕግና በሕግ ብቻ ነው። ያለ ሕግ ፍትሕ አይመጣም። ያለ ሕግ በሥርዓት መኖር አይቻልም። ምክንያቱም ገነት እንኳን በአንዲት በለስ የታጠረች ነበረች። አምላክ ፍትሓዊ በመሆኑ ለአንድ አዳምና ለአንድ ሔዋን ሕግ ስለተላለፉ ቅጣት ወስኖባቸዋል። ዓለምም ሚዛን ጠብቃ የምትኖረው በሥርዓትና በሕግ ብቻ ነው። ሕግ ሲጣስ ሥርዓት ሲዛባ የዓለም መልክ ይቀየራል። በሀገርም ሕግ እስካልተተገበረና እስካልተከበረ ድረስ ሌቦች ፊት ሆነው ሀገርን ወደመቀመቅ ያወርዷታል። በየተቋሙ ሌብነት ሲደራ በየሰፈሩ እንኳን ዘራፊ ይበረታል። በዚህም ሕዝብ በሁለት ሰይፍ ይመተራል።

ሀገር የምትድነው ፍትሐዊ በሆነ ሕግ ብቻ ነው። በተግባር ያጠፋን በመቅጣት፤ የሰራን በመሸለም ነው። በፍጥረት ውስጥ ደግሞ እንደ ሰው ሕግ የሚሽር የለም። ሌሎቹ በጥንት ደመነፍሳዊ ሕጋቸው እስከዛሬ አሉ። የሰው ልጅ ግን ሕግ የሚሽርና ሥርዓት የሚያፈርስ ብቸኛው ፍጥረት ነው። መስመር የሚይዘው ደግሞ በየብዙኃኑ መገናኛ ለይስሙላ ትምህርት በመስጠት፣ የግንዛቤ ማስፋፊያ በማቅረብ የሚሆን አይደለም። ምክንያቱም በሙስና ባሕር ውስጥ የሚዋኘው ሌላው ትምህርቱ የሚሰጠው ለተሰረቀው ሕዝብ መሆኑ ማሰብ በጣም ያበሳጫል። ያማልም። ያለጥርጥር ፈር ማሲያዝ የሚቻለው የሕዝብ፣ የሀገርን ሀብትና የግለሰብን ድርሻ የዘረፈን የዘረፈውን በመንሳትና ላጠፋውም ተመጣጣኝ ቅጣት በመቅጣት ነው።

በዚህ ዓለም ላይ ማንም የማንንም ድርሻ ሊነሳ አልተፈጠረም። ለዚህም ምንም ዓይነት ሙብት አልተሰጠም። ሁሉም ዜጋ የድርሻውን፣ የልኩን፣ የድካሙን ዋጋ ሰርቶ የሚከፈለው፣ ነግዶ የሚያተርፈው፣ ዘርቶ ምርት የሚሰበስበው፣ አልምቶ የሚቆጥረው ለላቡ ልክ አለው። ሁሉም የድካሙን ቢወስድ ሁሉም በደረጃው ያድጋል። በአንጻሩ በየፈርጁ ሀገር ሲያድግም አብሮ ይታደጋል።

ዛሬ በሀገሩ የዝና፣ የስኬት፣ የስም..... መለኪያው ገንዘብና ገንዘብ ብቻ ሆነ። መታፈር፣ መከበር በገንዘብ ሆነ። እምነት፣ ጥበብ፣ ፍልስፍና፣ ክህሎት፣ ዕውቀት.... ዋጋ የማያወጡ የሆኑ መሰለ። ይህ መንገድ ከቀጠለ ምን አይነት ትውልድ ልናፈራ ነው? ምን አይነት ሀገር ልንሰራ ነው? ምን አይነት እሴት ልንገነባ ነው? ታምኖ መስራትና ተግቶ ማትረፍ ካልተወደደ የባንዲራ አከል ከፍ አድርገን የምናከብራቸው በዘረፋ፣ በማጭበርበር እንዲሁም በጉልበትና በሥልጣን ሀገር ያደኸየውን ከሆነ፤ ሰርቶ በማትረፍ መክበርና መኩራት መቼ ይመጣ ይሆን? ሰው መሆን ማለት እኮ ከልክ ያለፈ የሀብት ባሕር ውስጥ በመዘፈቅ ብቻ አይደለም የሚሰምረው።

በዚህ ሀገር ላይ ደግሞ ብዙኃኑ ሕዝብ የሚፈልገው በቀዬው በሰላም መኖርና ለኑሮው መሠረታዊ ፍላጎቱ እንደሀገሯ ዕድገት ማግኘት እንጂ የቀን ሕልሙን ሕዝብ በጋራ አይጠብቅም። ዛሬ የብዙ ችግሮች ምንጭ የሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎት

ወደ 9ኛው ገጽ ዞሯል

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# «ኢንተርፕረነርሺፕ ሲስፋፋ ኢትዮጵያ ትፋፋለች»

## -ዶክተር ወረታው በዛብህ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዕምሮ ኢንተርፕረነርሺፕ ማስፋፊያ አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ሥራ ፈጣሪዎችን ለማፍራት የ30 ዓመት ግብ አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ያለ ኩባንያ ነው። ኩባንያው 51 አባላት ያሉት ሲሆን፣ 47ቱ በኩባንያው የሰለጠኑ ናቸው። ኩባንያው ወደ ተቋም የመቀየር ዓላማ ያነገበ ነው፤ ዓላማውን ዕውን ለማድረግ ከፍለው ከሚሰለጥኑ ሰልጣኞች በተጨማሪ በተለያዩ አማራጮች የስልጠና እንዲሁም የማማከር አገልግሎት ለሚፈልጉም አገልግሎቱን እየሰጠ ይገኛል።

ኩባንያው ከፍለው ከሚሰለጥኑት በተጨማሪ መለወጥ ለሚፈልጉ ሰዎች በተለያዩ አማራጮች የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) ስልጠናን በመስጠት ብዙዎችን ከህልማቸው ማገናኘት መቻሉን ይገልጻል። ላለፉት ሦስት ዓመታት 167ኛ የደረሰ የዩቲዩብ ፕሮግራምን ጨምሮ በአሀዱ ሬዲዮ የስኬት መንገድ በሚል ርዕስ የኢንተርፕረነሺፕ ስልጠናን አጠናክሮ እየሰጠ ይገኛል።

ዶክተር ወረታው በዛብህ የአዕምሮ ኢንተርፕረነርሺፕ ማስፋፊያ አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር መሥራች ከሆኑ ግለሰቦች መካከል አንዱ ናቸው፤ የቦርድ አባልና ዋና ሥራ አስፈጻሚም ሆነው ይሠራሉ። በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ዶክትሬት ዲግሪ አላቸው። አማርኛን ጨምሮ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛና ሩሲያኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገራሉ።

ራዕይ ያላቸው ሥራ ፈጣሪዎችን ለማፍራት እያደረጉ ካሉት እንቅስቃሴ አስቀድሞ በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር ነበሩ። ከመምህርነታቸው በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ፒያሳ ካምፓስ ዲን እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ፋይናንስ ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን ዶክተር ወረታው ሠርተዋል።

በዚህ ወቅት የሕይወታቸውን መንገድ የቀየረ አንድ ክስተት መፈጠሩን ዶክተር ወረታው ያስታውሳሉ። ጊዜው ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። ኢንተርፕራይዝ ኢትዮጵያ የሚባል ተቋም ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ እርሳቸውን ጨምሮ አምስት መምህራንን የኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ለተማሪዎች እንዲሰጡ ይፈልጋል። በቅድሚያ ግን አምስቱ መምህራን ተማሪዎቹን ማሰልጠን የሚያስችላቸውን ስልጠና ለ15 ቀናት እንዲያገኙ ተደረገ።

ስልጠናውን ባገኙ ማግስት ዶክተር ወረታው የሕይወት መንገዳቸውን ማስተካከል እንዳለባቸው በግልጽ መረዳት ቻሉ። በ15 ቀናት ስልጠና ያገኙት ዕውቀት ሚሊዮኖችን መፍጠር የሚያስችላቸው እንደሆነ ይረዳሉ። ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች መሠረቶቹ የቢዝነስ ሰዎች፣ ኢንቨስተሮች፣ ቱሪስቶችና ሌሎች እንደሆኑ በመረዳት እነዚህን ሰዎች የመፍጠር እልህ ከስልጠናው ማግኘት እንደቻሉ ነው ዶክተር ወረታው የገለጹልን።

ከስልጠናው በኋላ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የማስተማር ኃላፊነት ብቻ ይኑረኝ። ማዕረጎቹ አያስፈልጉኝም በማለት መምህር ብቻ ልሁን በማለት ቢሮውን አስረክበው የጊዜ ነፃነታቸውን አረጋገጡ። ይህን የጊዜ ነፃነት በመጠቀምም ተንቀሳቅሰው የተግባር ትምህርቶችን ተከታተሉ። ‹‹እኔም የራሴ አለቃ ነኝ፤ ተቆንጥሮ የሚሰጥ ሥራ ሠርቼ ራሴን ቤተሰቤንና ሀገሬን መለወጥ አልችልም›› በሚል እልህ ከላይ ታች ማለትን ከስልጠናው ማግስት ጀመሩ። ተስፋ ሳይቆርጡ ብዙ ጊዜ ወድቀው መነሳታቸውም ለዚሁ ነው።

የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) ስልጠና የሰጣቸው ተቋም ኢንተርፕራይዝ ኢትዮጵያ በወቅቱ በጥሩ ደመወዝ የቀጠራቸው ሲሆን፤ ከስልጠናው ጋር በተያያዘም ሁለት ጊዜ ኡጋንዳ በመጓዝ በኢኮኖሚና ማህበራዊ በኩል ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን ይናገራሉ። ከሁሉም በላይ ግን ኡጋንዳ ካምፓላ 40 ሰልጣኞችን ለማሰልጠን ሄደው ከፍለው ለመሰልጠን የተዘጋጁት 200 ሰዎች እንደነበሩ ያስታውሳሉ። ኢትዮጵያን ወክለው ኡጋንዳ ላይ 40 ሰልጣኞችን ሲያሰለጥኑ ያገኙት ግብረመልስ ኢትዮጵያ ውስጥ የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) ማሰልጠኛ ተቋም መክፈት እንዳለባቸው ነው። ይህ ሃሳብ እዚያው ኡጋንዳ ላይ ተጠነሰሰ።



የሃሳብ ጥንስሳቸውን መሬት ለማሳረፍ ሲነሱ አስቀድመው ከተቀጣሪነት መውጣትና ወድቀው ለመነሳት ወስነው ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ጥለው የወደቁ ቢሆንም፣ ወድቀው ሳይቀሩ በብዙ ብርታት ተነስተዋል። ‹‹ማንኛውም ፍሬ ሳይበሰብስ እንደማይበቅል፤ ሳይበቅል እንደማያፈራ ሁሉ፤ እኔም እንደ ፍሬዋ በብዙ ነገር ተፈትኜ ብዙ ጊዜ ወድቄ ለመነሳት ወስኜ ሁሉንም አልፌዋለሁ›› ይላሉ።

‹‹ኢንተርፕረነርሺፕ ሲስፋፋ ኢትዮጵያ ትፋፋለች፤ የኢትዮጵያ ሀብት ከአንገት በላይ ያለው/አእምሮ/ የልጆቿ አካል ነው›› የሚሉት ዶክተር ወረታው፤ ይህን ለማድረግ ትልቁ መሣሪያ የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) ልማት እንደሆነም በጽኑ ያምናሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተገባ ነገር እንዳይስፋፋ የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) መስፋፋት አለበት። ይህን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ከልጆቿ አንገት በላይ ያለውን አካል (አእምሮ) መጠቀም ሲቻል እንደሆነም ይናገራሉ።

እርሳቸው ወደ ዘርፉ በገቡበት ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ አንድም የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) መጽሐፍ አለመኖሩን ያስታወሱት ዶክተር ወረታው፤ ሰባት መጽሐፍቶችን በግላቸው በጋራ ደግሞ ስድስት በድምሩ 13 መጽሐፍቶችን እንዲሁም ሰባት ማሰልጠኛ ተንቀሳቃሽ ምስል (በሲዲ) አዘጋጅተው አንድ ሚሊዮን ባለራዕይ ዜጎችን ለማፍራት እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ገልጸዋል። መጽሐፍቶቹ በተለያዩ ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በኦሮሚኛና በትግርኛ የተዘጋጁ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ፈጠራ ካልተስፋፋ ያልተገባ ነገር እንደሚስፋፋም አስረድተዋል።

ዛሬ ላይ የሥራ ፈጠራ (የኢንተርፕረነርሺፕ) ለማስፋት መንግሥትን ጨምሮ በግለሰብ ደረጃም ብዙ አማራጮች እየመጡ እንደሆነና ይህም እንደሚበረታታ የጠቀሱት ዶክተር ወረታው፤ አዕምሮ ኢንተርፕረነርሺፕ ማስፋፊያ አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር የማሰልጠንና የማማከር ሥራውን በስፋት እየሠራ እንደሆነ ይገልጻሉ። በዚህም በእስካሁን ቆይታቸው በርካታ ባለራዕዮችን መፍጠር እንደቻሉም ተናግረዋል።

በተለያየ ጊዜና ቦታ የሚሰጡትን ስልጠናና የማማከር ሥራ ሳይጨምር በመደበኛው ዙር ብቻ እየከፈሉ ለሚሰለጥኑ ሰልጣኞች አንድ ሺ ጊዜ ስልጠና መስጠቱን ጠቅሰው፣ በስልጠናው ተጠቅመው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና ሀገራቸውን ማገዝ የቻሉ ኢትዮጵያውያን በርካታ መሆናቸውንም አብራርተዋል። ሩቅ ሳይሄዱ በቅርብ ካሉት እርሳቸውን ጨምሮ የኩባንያው አባል የሆኑ 47ቱ አባላት የዚህ ውጤት መሆናቸውን እና ስኬታማ እንደሆኑ ተናግረዋል። አብዛኞቹም የራሳቸውን ድርጅት ከፍተው ለብዙዎች ሥራ ዕድል መፍጠር የቻሉት በርካቶች እንደሆኑም አመልክተዋል።

በማዕከሉ ስልጠና ያገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ባለራዕይ ሰልጣኞች ስለመኖራቸው የጠቀሱት ዶክተር ወረታው፤ እነዚህ ሰልጣኞች አሁን ላይ የማይታዩ ነገር ግን ወንዝ ሆነው የሚፈስሱ ናቸው ሲሉ ይገልጻሉ። ምናልባትም ፍሬያቸው የሚታየው ወደፊት እንደሆነ ገልጸው፤ ኩባንያው ከሁለት ሰዎች ጀምሮ እንደሚያሰለጥንም አመላክተዋል።

‹‹አሜሪካ በአምስት ኢንተርፕረነሮች ነው የተቀየረችው›› የሚሉት ዶክተር ወረታው፤ እነዚህን ሀገር የመቀየር አቅም ያላቸውን አምስት ኢንተርፕረነሮች ለማግኘት በርካቶችን ማሰልጠን የግድ መሆኑን ይገልጻሉ። እነዚህ ሰዎች ሲገኙ ኢትዮጵያ ድህነት፣ ስደት፣ ረሃብና ጦርነት አጀንዳዎቿ አይሆኑም ይላሉ።

እርግጥ ነው ኢትዮጵያ የታደለች ሀገር ናት፤ እንደ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ጸጋ የታደሉ ሀገራት በዓለም የሉም ሲሉ ዶክተር ወረታው ይገልጻሉ። ባለራዕዮቿና ህልም ያላቸው ልጆቿ ጥቂቶች መሆናቸውን በመጥቀስም፣ ሠርቶ ከመብላት ውጪ ወደፊት መጓዝ አልተቻለም ወደኋላ ቀርተናል ይላሉ። ሌሎች ያደጉ አገራት ተሞክሮ የሚያመለክተው ሠርቶ ከመብላት ባለፈ ማትረፍረፍ፣ ለትውልድ ጥሎ ማለፍ የሚል ነው። እኛም ይህን ማድረግ ይጠበቅብናል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለዚህም ሀገር የሚቀይሩ ኢንተርፕረነሮች መፈጠር ይኖርባቸዋል፤ ኢንተርፕረነሮች ሲፈጠሩ ትላልቅ ፋብሪካዎች፣ የእርሻ ቦታዎች፣ ሆቴሎች፣ የትምህርትና የሕክምና ተቋማትና ሌሎችን መገንባት ይችላሉ። ተቋማቱን ለትውልድ አስተላልፈው እነሱ ግን ያልፋሉ። ለዚህም በሀገር ደረጃ ብዙ መሠራት አለበት።

ብዙ መደፈን ያለባቸው ክፍተቶች እንዳሉም ጠቅሰው፣ የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ ኢትዮጵያ የመቶና የሁለት መቶ ዓመት ዕቅድ የሌላት መሆኑን ትልቅ ክፍተት ሲሉ ገልጸውታል። የዛሬ መቶና ሁለት መቶ ዓመት የሕዝቡ ቁጥር በእጥፍ ይጨምራል፤ ስለዚህ «ምን እመገበዋለሁ፣ ምን ይሠራል፣ መኖሪያውስ ወዴት ይሆናል» የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችሉ የረጅም ጊዜ እቅዶችን አቅዶ የመንቀሳቀስ ክፍተት ከእያንዳንዱ ቤት አንስቶ እስከ ቤተመንግሥቱ እንደሚታይ ዶክተር ወረታው አመልክተዋል። ይህን ችግር ለመፍታት የረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊና ወሳኝ እንደሆነም አስረድተዋል። ሥራ ፈጣሪዎች በዕቅድ እንደሚመሩ ጠቅሰው፣ እርሳቸውም የፈጣሪን ፈቃድ በማስቀደም የ30 ዓመት ዕቅድ አዘጋጅተው እንደሚንቀሳቀሱ ይናገራሉ።

«ኢትዮጵያ ሁሉም ነገር የተሰጣት ታላቅ ሀገር ብትሆንም እንደታላቅነቷ ሕዝቦቿ አላደጉም ዛሬም ረሃብና ጦርነት መገለጫዎቿ ናቸው» የሚሉት ዶክተር ወረታው፤ ይህም ራእይ ያለው ካለመሆን ጋር ተያይዞ የመጣ ችግር እንደሆነ ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ወንዞች በከንቱ እየፈሰሱ፣ መሬቱ እያለ መጠቀም አለመቻሉን ጠቅሰው፣ ሁሉን የተሰጣት ኢትዮጵያ የሕዝቦቿ ሰላም፣ አንድነትና ፍቅር ግን መወሰዱንና ሕዝቡ በማይጠቅመውና በማይመለከተው ጉዳይ እየገባ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን እያጠፋ እንደሆነ ነው ያብራሩት። ለዚህም ቁልፉ ችግር ኢትጵያ ውስጥ የፈጠራ ጥበብ ክህሎቶች የዳበሩ አለመሆናቸውንና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ አለመቻሉን ያመለክታሉ።

«ቢዝነስ ላይ ያለው አመለካከት ትክክል አይደለም፤ በተለይም ሀገርን ለትልቅ ህልም ማነሳሳት ከፖለቲከኞቹ ይጀምራል፤ እንዲህ ዓይነቱ መነሳሳት አብዛኞቹ ፖለቲከኞቹ ዘንድ የለም» የሚሉት ዶክተር ወረታው፤ ለዚህም ሕዝቡ በልቶ አደር እንጂ አትረፍርፎ አደር እልህኛ መሆን አልቻለም ብለዋል። የሚገባንን መሥራት አልቻልንም፤ በመሆኑም ሁልጊዜ ተጨማሪ የቤት እጥረት፣ የምግብ እጥረት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እጥረት፣ የመማሪያና የትምህርት ጥራት እጥረት ሌሎችም እጥረቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተደራረቡና እየተነባበሩ መምጣታቸውን ነው ያስረዱት።

ሁሉም ነገር ሞልቶ የተትረፈረፈባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር፣ ሀገሪቱ ሀብቶቿን ተጠቅማ መልማት፣ ማደግና መለወጥ እንድትችል እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት አለበት ሲሉ ገልጸው፣ የዚህ የቤት ሥራ ከቤተሰብ እንደሚጀመርም አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ቤተሰብ ልጁን ሥራ ወዳድ፣ እውነተኛ፣ ሀሰትን የሚጠየፍ፣ ሀገር ወዳድና የሰው ገንዘብ የማይመኝ አድርጎ ካሳደገው ሀገር መገንባት ከዚያ ይጀመራል። ለመብላት መሥራት የግድ እንደሆነና ‹‹ማንኛውም ሰው ተግቶ መሥራት ከቻለ ካሰበበት መድረስ ይችላል›› የሚለውን በመርህ ደረጃ ትውልዱ ውስጥ ማስረጽ ከተቻለ ለቀጣዩ ትውልድ ተደራራቢ ችግር አይቀመጥም።

ራስን መገንባትና ማልማት ላይ ብዙ መሥራት ያስፈልጋል። በተለይም ከአንገት በላይ (አእምሮ ላይ) ያለው ልማታችን አስፈላጊና ትክክለኛው ቦታ ላይ አልደረሰም። አእምሮ ላይ የሚካሄደውን ልማት ትክክለኛው ቦታ ላይ ለማድረስ አንባቢ፣ ተመራማሪና ሥራ ፈጣሪ ትውልድ መፈጠር ይኖርበታል። ገበሬው የሙያ ትምህርት ያስፈልገዋል፤ አንባቢና ተመራማሪ ሊሆን ይገባል። እንደ ትናንት ሁሉ ዛሬም በበሬ የሚያርስ አርሶ አደር ሊኖር አይገባም። አርሶ አደሩ ነገ ያደገና በትራክተር የሚያርስ፣ በኮምባይነር የሚወቃ፣ ምርቱን በመኪና የሚሰበስብ፣ አግሮ ፕሮሰሲንግን ፈጥሮ ለአካባቢው ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችልና የመንደሩ አልሚ መሆን አለበት። የአርሶ አደሩ ምርት ሲበዛ የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩ ፋብሪካዎች ይበዛሉ። ስለዚህ ዓመቱን በሙሉ የሚሠሩ ኩባንያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ያስፈልጋሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ የተቀጣሪነት አስተሳሰብ እየቀነሰ ስለመምጣቱ የጠቀሱት ዶክተር ወረታው፤ በቀጣይም ተቀጣሪ መሆን የማያዋጣ እንደሆነ ትውልዱ እየገባው እንደሆነም ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ተቀጥሮ መሥራት የቤተሰብን ፍላጎት ሊያሟላ አይችልም። ተቀጣሪውም ቢሆን ተጨማሪ ሥራ መሥራት ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ መሠረታዊ ፍላጎት አለማሟላቱ ይቀጥላል።

የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ እየተቀየረ መሆኑን ጠቅሰው፣ መፍትሔው በእያንዳንዳችን መዳፍ ውስጥ መሆኑንም አመልክተዋል። በቀጣዩ በጀት አመት መንግሥት አዲስ ሠራተኞችን አይቀጥርም የሚሉ መረጃዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ ይህም የተመረቀ ሁሉ ሥራ እንደማይጠብቀው አውቆ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆን ወጣቱን የሚያነሳሳ ትልቅ ዕድል መሆኑን አመላክተዋል።

እንደተባለው መንግሥት አዲስ ቅጥር የማይፈጽም ከሆነ ለተማረው ኃይል የብድር አገልግሎት ማመቻቸት፣ የማምረቻ ቦታ ማዘጋጀት፣ ስልጠና መስጠትና ማምረቻ ማሽኖችን ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚጠበቅበት ዶክተር ወረታው ያመለክታሉ። እነዚህ ሁሉ የተሟሉለት ወጣት በሀገሪቱ ውስጥ የሚታዩ ክፍተቶችን ሁሉ መሙላት የሚችል ዕድለኛ ትውልድ እንደሆነ ጠቁመዋል።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## “ልጄን አደራ! ”

መልካምሥራ አፈወርቅ



### እንደመነሻ ...

ዛሬም በርካታ ጉዳዮች መፍትሄ ከሚያገኙበት፣ ጥብቅ ቋጠሮዎች ላልተው ከሚፈቱበት ስፍራ ላይ ነኝ። በዚህ ቦታ የብዙ ሰዎች ዕንባ ታብሷል፡፡ የአይታመኔ ታሪኮች መጨረሻ አምሯል፡፡ የብዙሃኑ ፈታኝ ሕይወት ተቀይሯል፡፡

ዛሬ በሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር ግቢ የሚገኙ ነፍሶች ትናንትን በሻካራማ መንገዶች አልፈዋል። አብዛኞቹ የተስፋ መቁረጥን ስሜት አሳምረው ያውቁታል። ጥቂት የማይባሉትም በሽክማቸው መከበድ ሰው ሆነው መፈጠርን እስከ መጥላት የደረሱ ናቸው ፡፡ በወቅቱ በርካቶቹ ሰማይ የተደፋባቸው ያህል ተሰምቷቸው ያውቃል፡፡

ከእነዚህ ነፍሶች ጥቂት የማይባሉት በከፋ ችግር፣ በህመምና ባይተዋርነት ሲሰቃዩ ነበር፡፡ የትናንት ጨለማ አልፎ ዛሬ እስኪነጋም ከጎናቸው የቆመ «አይዟችሁ » ባይ ወገን አልነበራቸውም፡፡ ሁሉም በሚባል ሁኔታ በሰው መሀል ሆነው ሰው በማጣት ተሰቃይተዋል፡፡ እንደ ሰው ወግ አጉራሽ፣ አልባሽ፣ አስታማሚ ደጋፊን ተርበዋል፡፡

ከጎናቸው ዕንባቸውን የሚያብስ፣ ብሶታቸውን የሚያደምጥ አለመኖሩ ለብዙ ችግሮች ሲዳርጋቸው ነበር፡፡ የዛሬን አያድርገውና ትናንትን እያንዳንዳቸው በሆነባቸው ሁሉ አዝነዋል ፣ ተክዘዋል ፣ አምርረው አልቅሰዋል፡፡

ዛሬ እነዚህና ሌሎች በመልካም ልብና በቸር እጆቿ በምትታወቀው ወይዘሮ ሙዳይ መሪነት ዕንባቸው ታብሷል፡፡ ታሪካቸው ተቀይሯል፡፡ ካሉበት፣ ከወደቁበት፣ ለማንሳት የሚፈጥነው የግቢው ቅንነት በብዙ ፈተናዎች መሀል እያለፈ ደግፏቸዋል፡፡ ቀድሞ በሁኔታዎች ክፋት የጠሉትን ማንነት ሽሮም «ሰው» መሆናቸውን መስክሯል፡፡

ዛሬም በሙዳይ ደጃፍ ጨቅላ ህጻናት ፣ በዘንቢል፣ በጨርቅ ተጠቅልለው ይጣላሉ፡፡ የተቸገሩ፣ ያዘኑ፣ ቀን የጨለመባቸው ወገኖች ዕለት ከዕለት ከግቢው ይደርሳሉ። በኤች አይ ቪ የተያዙ፣ በከፋ ህመም የተፈተኑ፣ በማጣት መንጣት ሆድ የባሳቸው ሁሉ መጠጊያ ማደሪያቸው የሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር ነው፡፡ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የያዙት አይነኬ ታሪክ አላቸው፡፡ የአብዛኞቹ ሕይወት በመልከ ብዙ ሚስጥር የተሸበበ ነው፡፡ እነዚህ ባለታሪኮች በአንድም በሌላ ምክንያት እግራቸው ወደ ሙዳይ ግቢ አድርሷቸዋል፡፡

እንዲህ በሆነ ጊዜ ፊት የሚነሳቸው፣ በር የሚዘጋባቸው አይኖርም፡፡ መከፋታቸውን የሚያ ውቁ፣ መቸገራቸውን የሚረዱ ልበ ቅኖች አቅፈው ይደግፏቸዋል፡፡ ውሎ አድሮ ያለፈ ታሪካቸው ይቀየራል፡፡ የከፋ ሕይወታቸው ይለወጣል፡፡ እነሱም ከቁስላቸው አገግመው ለሌሎች መፍትሄ ለመሆን የፈጠኑ ይሆናሉ፡፡

### ከሙዳይ አንደበት...

ዛሬም ከወይዘሮ ሙዳይ ጋር ብርቱ ወግ ይዘናል። ጨዋታችን ብዙ ታሪኮችን የሚያውሳ ፣ በርካታ የሕይወት ገጠመኞችን የሚዳሰስ ነው። ወይዘሮዋ ካለፉት ታሪኮች እያስታወሰች በትዝታ ታወጋኛለች። በምሰማው እየተገረምኩ በዝምታ ማዳመጤን ይዣለሁ፡፡

እየሰማሁት ባለው እውነት ያለፈ ታሪካቸውን የቀየሩ፣ ሕይወታቸውን የለወጡ በርካቶች መሆናቸውን አውቄያለሁ፡፡ በአብዛኞቹ የሕይወት ገጠመኞች መሀልም የሙዳይ በጎ አድራጊ ሰፊ እጆች አርፎበታል፡፡ ታሪክ በራሱ ጊዜ ቢያልፍም «ነበር» ብሎ ይወሳ ዘንድ ግድ ነውና ከብዙዎቹ መሀል የጥቂቶቹን ልንመዝ፣ ልናስታውስ ወደናል፡፡ እነሆ! ከእውነታዎቹ አንዱ ፡፡

### ከሲታዋ ሴት

ማንም ከሰዎች መሀል ተቀምጣ ቢያያት ስለእሷ የተለየ ቅጥነት ለማወቅ አይቸገርም፡፡ ይህች ሴት ከተለመደው አካላዊ አቋም ወጣ የሚያደርጋት ብዙዎች አይተው የሚደነቁባት ከሲታ ሰውነቷ ነበር፡፡ ቀጭን ነች፡፡ «ቢይዟት ትሰበራለች» ይሏት አይነት ነፍሰ ስስ ፡፡

በአጋጣሚ ሴትዬዋን ያያት ሁሉ ከመገረም አልፎ «ክው» ብሎ መደንገጡ አይቀሬ ነው፡፡ ከአካሏ የተጣበቀው ቆዳዋ ስጋ ይሉት አንዳች ነገር ያለበት አይመስልም፡፡ በግልጽ የሚነበበው ዘርዛራ አጥንቷ አንድ ሁለት ብሎ ይቆጠር ይመስላል፡፡

የሚገርመው ጉዳይ አብራት የምትኖር ልጇም ከእሷ ጋር መምሰሏ ነው፡፡ እሷም እንደ እናቷ ድርቅ ያለ ሰውነት ፣ ክስት ያለ አቋምና ገጽታን ይዛለች፡፡ ከሲታዎቹ እናትና ልጅ አይለያዩም፡፡ ክፉ ደግ ቀናትን፣ አስቸጋሪ ጊዜያትን አብረው ተሻግረዋል፡፡

ሙዳይ ዛሬም ይህችን ሴት የምታስታውሳት የተለየ ቅጥነቷን ከሰዎች ግርምታ ጋር አያይዛ ነው፡፡ ዓመታት ቢያልፉም በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ዛሬም ድረስ አትዘነጋም፡፡ በአጽም የቀረ የሚመስል አቋሟ፣ እንደ እንጨት የደረቀ ሰውነቷ፣ የተጎሳቆለ ማንነቷ አሁንም ትዝ፣ ትውስ ይላታል፡፡

በጎ አድራጊዋ ሴትዬዋን በግቢው ከሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ጋር አዛምዳ ማኖር ጀምራለች፡፡ እንዲህ መሆኑ ግን በታሰበው መንገድ አልቀጠለም፡፡ የነዋሪው ሰላም መናጋት፣ የግቢው ዝምታ መደፍረስ ይዟል፡፡ የተለየ ባህርይዋ፣ ተደባዳቢነቷ ብዙዎችን አውኳል። ሙዳይ በየጊዜው በምታየው ፣ በምትሰማው ጉዳይ ተቸግራለች ፡፡

ከዚህ በኋላ በእሷ ማንነት በግቢው ከሌሎች ጋር ማኖር አይቻልም፡፡ እውነቱን ስታውቅ መፍትሄ ያለችውን አማራጭ ሞከረችና ተሳካላት፡፡ ከቀበሌ ሰዎች ጋር ተማክራ ለእሷ የሚሆን ማረፊያ ክፍል አገኘች፡፡ ከግቢው አውጥታ፣ የሚያስፈልጋትን አሟልታ በነጻነት ማኖር ጀመረች፡፡

አሁን ሴትዬዋ ከግቢው ውጭ ድጋፍ ከምታደርግላቸው ሰዎች መሀል አንዷ ሆናለች፡፡ ይህች ሴት ባሻት ጊዜ አንድ ሳምንት ምግብ ይሉትን አትቀምስም። አንዳንዴ ደግሞ ጠርሙስ ሙሉ አረቄ ግጥም አድርጋ ትጠጣለች፡፡

አሁንም ከሰዎች አትስማማም፡፡ የቀረቧትን ትጣላለች፡፡ ያገኘችውን ሁሉ እየተሳደበች፣ ትውላለች። ልጇን ጨምሮ በእጇ የገቡትን መደብደብ ልማዷ ነው። ሙዳይን ለማግኘት ሰበብ የምትሻው ሴት ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ታስጠራታለች፡፡ እሷን ማየትና ማግኘት ባሻት ጊዜ ከአፏ አትነጥላትም፡፡ ተደጋጋሚ መልዕክት ሲደርሳት ከስራ ጊዜዋ ቀንሳ ካላት ሰዓት ሸራርፋ ካለችበት ትደርሳለች፡፡ ስታገኛት ግን ምክንያቷ ሁሉ ያንስባታል፡፡

ስለ እሷ ስራ ብትፈታም፡፡ አትጨክንባትም ተረጋግታ እንድትኖር መከራ አጽናንታ ትለያታለች፡፡ ባመማት በደከማት ጊዜም ፈጽሞ አትርቃትም፡፡ ሁሌም ለልጇ እንድትኖር ትመኛለች፡፡ ስለጤናዋ አትሰለችም፡፡ መቼም ቢሆን ሀኪም ቤት ለመውሰድ ትፈጥናለች ፡፡ መድኃኒቷን ለመግዛት ትሮጣለች፡፡

### የሀኪሙ ውጤት

አንድ ቀን ሙዳይ ይህችን ሴት ለማሳካም ከአንድ ሆስፒታል ወስዳ በወቅቱ ጥሩ ስም ከነበረው ሀኪም ዘንድ ታቀርባታለች፡፡ ሙሉ ምርመራ ያደረገላት ሀኪም ስራውን እንደጨረሰ የሚለው የሚናገረው ጠፋው፡፡ ሴትዬዋን የቱን መርምሮ የቱን እንደሚተው ጨንቆታል፡፡ በእሷ ውስጠት ኩላሊት ፣ ጉበት፣ ሳንባ ይሏቸው ክፍሎቿ በሙሉ አልቀዋል፡፡

ይህ አይነቱ እውነት ያልተለመደና ያልታሰበ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ችግር ይዛ በሕይወት መቆሟ፣ ያስደንቃል። ዶክተሩ በግርምታ ውስጥ ሆኖ ለሙዳይ የደረሰበትን የምርመራ እውነት አሳወቃት፡፡ ከዚህ የህክምና ውጤት በኋላ ሳምንት ትቆያለች ያለ አልነበረም፡፡ እሷ ግን ከነችግሮቿ በሕይወት መኖር ቀጠለች፡፡

ሙዳይ ባለችበት ሆና የሴትዬዋን ውሎ አዳር ትከታተላለች፡፡ እንደቀድሞው ግን በጠራቻት ቁጥር ወደእሷ አትሮጥም፡፡ ከራሷ መክራ ከመሄድ ታቅባለች። ሴትዬዋ ይህን ስታውቅ ሙዳይን የማግኘት ጉጉቷ ጨመረ። በየቀኑም መልዕክተኞች እየላከች መጥታ እንድታያት ጎተጎተች፡፡

አሁን ሙዳይና ያቺ ሴት ከተያዩ ቆይተዋል። ለአፍታ እረፍት የሌላት ወይዘሮ በየቀኑ ወደእሷ መሄዱን ካቆመች እንደዋዛ ጊዜያት ተቆጥረዋል፡፡ እንደልማዷ ሰዎችን መላክ ባታቆምም ሙዳይ ጉዳይዋ እየበዛ፣ ጊዜዋ እያጠረ ነውና ሀሳቧን መሙላት አልሆነላትም፡፡ ይህ እውነታ ሁለቱን በአካል ሳያገናኝ ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡

### ከሁለት ዓመታት በኋላ...

አንድ ቀን የሙዳይ የእጅ ስልክ ደጋግሞ አቃጨለ። ድንገት አንስታ የደዋዩን ማንነት ጠየቀች፡፡ ከስልኩ ውስጥ ለሁለት ዓመታት ሳታያት የቆየችውን ሴት ድምጽ ጎልቶ ተሰማት፡፡ እስከዛሬ ሰዎችን ስትልክ የቆየችው ሴት ዛሬ እንዲያደወልላት ስልክ ለምና በድምጽ እያወራቻት ነው፡፡ ደዋይዋ እየደጋገመች ሙዳይን ትጠይቃለች፡፡ ስላመማት፣ ስለጨነቃት በአካል መጥታ እንድታያት ትማጸናለች፡፡

ሙዳይ የእሷ ቃል በጆሮዋ በደረሰ ጊዜ እስከዛሬ ተሰምቷት በማያውቅ ሁኔታ ውስጧ ተረበሸ። እስካሁን የምትሻውን ሁሉ እየላከች የፍላጎቷን ስትሞላ ቆይታለች፡፡ ወደእሷ ላለመሄዷ የራሷ በቂ ምክንያትም ነበራት፡፡ አሁን ግን ይህን ጉዳይ ሰበብ እያደረገችው አይደለም፡፡ «ተነስተሽ ሂጂ» የሚል ቃል ሹክ እያላት ነው። ተማጽኖዋን፣ ልመናዋን መናቅ አልሆነላትም፡፡ የእጇን ስራ ጣለች፡፡ ከምትሄድበት ቀረች፡፡ ጊዜው እየመሸ ነው። አልተዘናጋችም፡፡ ጊዜ ሳትፈጅ መኪናዋን አስነስታ እሷ ወደምትገኝበት ሰፈር ከነፈች፡፡

### “ልጄን አደራ! ”

በስፍራው ስትደርስ እስከዛሬ ወደ እሷ ስትልካቸው የነበሩትን ሰዎች አገኘች፡፡ ሁሉም ሙዳይ ዛሬ ሞልቶላት በመምጣቷ ተደስተዋል። ሰላም ብላቸው ወደውስጥ ስትዘልቅ ታማሚዋን አገኘቻት፡፡ ዛሬም እንደቀድሞው ፊቷ እንደገረጣ፣ አጥንቷ እንዳገጠጠ፣ አፏ እንደደረቀ ነው። ታማሚዋ ገና ስታያት «እንኳን መጣሽልኝ» በሚመስል አቀባበል ፈገግ ለማለት ሞከረች፡፡

በወቅቱ ነፍሰጡር የነበረችው ሙዳይ ይህ ገጽታዋ ውስጧን ረበሸው፡፡ ስለ እሷ በቅርበት ብታውቅም ሁለት ዓመታትን ሳታያት ቆይታለች፡፡ ዕለቱን የልቧን ማወቅ፣ የፍላጎቷን መረዳት ብትፈልግ በለመደችው የፍቅር ስሜት ወደታማሚዋ ቀረበች። ህመሙ ብሶባታል፡፡ አቅም እንዳነሳት ጉልበት እንደከዳት ያስታውቃል፡፡ ይህ የገባት ሙዳይ ወደግል ሆስፒታል ልትወስዳት መምጣቷን ነገረቻት፡፡

ታማሚዋ በግድ ፈገግ እያለች የምትለውን ሁሉ ሰማች፡፡ አሁን ሙዳይ ልብሷን እንድትለብስ፣ ከአልጋው እንድትነሳ እያገዘቻት ነው፡፡ እሷም እንደምንም ራሷን አበርትታ ለመቆም፣ ለመራመድ እየሞከረች ነው፡፡ በድንገት ግን ያልታሰበው ሆነ ፡፡

ታማሚዋ ከሙዳይ እጅ አምልጣ ሸርተት ብላ ወደቀች፡፡ ሁኔታው ያስደነገጣቸው ከወደቀችበት ሊያነሷት ፈጠኑ፡፡ የታሰበው አልሆነም የወደቀችው ሴት ዳግም አልተነሳችም፡፡ በአንድ አፍታ ትንፋሽዋ በህቅታ ተቋጭቷል ፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት በሙዳይ ጆሮ ውል ያለው ቃል በህሊናዋ ተመላለሰ፡፡ ታማሚዋ በጭንቅ ውስጥ ሆና ለሙዳይ ይህን የአደራ ቃል ትደጋግም ነበር ፡፡ «አደራ !ልጄን አደራ»

### ሽሽት ...

ሙዳይ የሴትዬዋን ድንገቴ ሞት አምኖ መቀበል ተስኗታል፡፡ የሁኔታው አስደንጋጭነት ያስደነበራቸው የአካባቢው ሰዎች ሟችን እንስተው እንደወጉ ማስተካከልና መገነዝ አልፈለጉም፡፡ ለአመታት መታመሟን፣ ያለቅጥ መክሳት፣ መቅጠኗን ያውቁ ነበርና ሊቀርቧት አልፈለጉም፡፡ ሙዳይን አጋፍጠው ሸሹ፣ራቁ፡፡

ሙዳይ ምርጫ አልነበራትም፡፡ ለመውለድ አንድ ሳምንት ቢቀራትም፡፡ ቀድሞ ያጋጠማትን ተመሳሳይ ተሞክሮ ተጠቅማ በድፍረት ሟችን ለመገነዝ ጎንበስ ቀና አለች፡፡ ያሰበችው ተሳካ፡፡ አካሏን አስተካክላም «አደራ» ወዳለቻት ልጇ ፊቷን ዞረች፡፡ ትንሽዋ ልጅ ሁሉም ጉዳይ መጠናቀቁ የገባት ይመስላል፡፡ ልብሶቿን ሰብስባ ከሙዳይ ጉያ ተወሸቀች፡፡ እንደልጅ አልተረበሸችም፣ ስታለቅስ፣ ስትተክዝ አልታየችም፡፡

ወይዘሮ ሙዳይ ዛሬ ላይ ሆና ያንን ቀን ስታስታውስ በዓይኖቿ ትኩስ ዕንባ ያለማቋረጥ ይወርዳል፡፡ ያቺ ሴት ከዓመታት በኋላ አጣድፋ የጠራቻት አንድም ለስንብት፣ አንድም ለአደራ ቃል መሆኑ ሲገባት በሆነው ሁሉ ትገረማለች፡፡

በወቅቱ እንደቃሏ ልጇን ተቀብላ ቀብሯን በወጉ ፈጽማለች፡፡ ይህ ታሪክ ዛሬን በትዝታ ስታወጋው ለሌሎች ምሳሌ እንደሚሆን አይጠፋትም፡፡ በእሷ ህሊና ደግሞ ዘወትር ከምታስባቸው፣ ሁሌም ከማትዘነጋቸው አስገራሚ እውነታዎች መሀል አንደኛው ሆኗል፡፡ የከሲታዋ ሴት ታሪክና አሳዛኙ የሕይወቷ መጨረሻ፡፡

# ስፖርት



# የክልል ክለቦች ቻምፒዮና ወደ ጥሎ ማለፍ ፉክክር እየተሸጋገረ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ የክልል ክለቦች እግር ኳስ ቻምፒዮና በሀዋሳ ከተማ እየተካሄደ ይገኛል። ውድድሩ በወንዶች አንደኛ ሊግን የሚቀላቀሉ አራት ቡድኖችን እንዲሁም በሴቶች ከፍተኛ ሊግን የሚቀላቀሉ ሁለት ክለቦችን የሚለይበት መድረክ ነው፡፡

ውድድሩ በሁለቱም ፆታ በድምቀት የቀጠለ ሲሆን፤ ዛሬ አስራ አንደኛ ቀኑን አስቆጥሯል። በከፍተኛ ፉክክር ታጅቦ የቀጠለው የወንዶች ውድድር በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሜዳ እየተካሄደ ሲሆን፣ ለ25 ቀናት የሚቆይ ይሆናል። በቻምፒዮናው ከአስር ክልሎችና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች የተወጣጡ ክለቦች የሚፎካከሩበትም ነው። በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መሪነት ከሚካሄዱ ውድድሮች አራተኛ እርከን ላይ የሚቀመጠው የክልል ክለቦች ቻምፒዮና ወደ የኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ ውድድር የሚቀላቀሉትን ክለቦች ለመለየት አጋጊ ፉክክር የሚታይበት ሆኗል፡፡

በቻምፒዮናው ከሰኔ 14/2015 ዓ.ም ጀምሮ 31 ክለቦች በስምንት ምድቦች ተከፍለው ውድድራቸውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ። እስከ ሐምሌ 8/2015 ዓ.ም በሚቆየው ውድድር በእያንዳንዱ ምድብ አራት ክለቦች ተደልድለው የምድብ ማጣሪያቸውን ወደ ማገባደዱ ተቃርበዋል።

ከምድብ 1-15ኛ ካምፕ ሀዋሳ፣ ሚቶ፣ ኩርሙ ጉሌ፣ ቤሮ ወርቅ፤ በምድብ 2 ቃላድ አምባ፣ ጎንደር አራዳ፣ ወንዶ ገነት፣ መንጌ ቤኒሻንጉል፤ ምድብ 3 ናቲ ዩኒቲ፣ ቡልቡላ አሜን፣ ዋልያ ድሬዳዋ፣ ሱሉልታ ቢ ምድብ 4 አማያ፣ ቦሌ ገርጂ፣ ገንደ አብዲ ቦሩ፣ ዱል አዛህቢ፤ ምድብ 5 መታፈሪያ ክፍሌ፣ ደምበጫ ከተማ፣ ቢኢ ከተማ፣ ማያ ሲቲ፤ ምድብ 6 ምበቦ ዳዲበን፣ ኛንግላንድ፣ መልካ ኖኖ፣ ፍቅር በአንድነት፤ ምድብ 7 ቦረና መካነ ሰላም፣ ጊምቢ ከተማ፣ አርባ ምንጭ ዙሪያ፣ ሠመራ ሎጊያ፤ ምድብ 8 ቲሊሊ ከተማ፣ ደንቢ ዶሎ፣ የኛ ፣ የኛ አዲስ ከቴ በስምንቱ ምድቦች የተደለደሉ ክለቦች ናቸው።



የክልል ክለቦች ቻምፒዮና በሁለቱም ፆታ በሀዋሳ እየተካሄደ ይገኛል፣

የኢትዮጵያ ክልል ክለቦች ቻምፒዮና የክልል ክለቦች ተሰጧቸውን የሚያሳዩበት እና የወደፊት ኮከቦች የሚወጡበት ወሳኝ መድረክ ነው። በብሔራዊ ቡድን ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ለሚፈልጉ እና በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ፕሮፌሽናል ክለቦችን ቀልብ ለመሳብ ለሚፈልጉ ተጫዋቾች እንደ መወጣጫ ሆኖም ያገለግላል። በመላ አገሪቱ የሚገኙ የእግር ኳስ አፍቃሪዎች በዘንድሮው ቻምፒዮና የሚደረጉትን አስደሳች ጨዋታዎችና ፉክክሮች በጉጉት እየተከታተሉም ነው።

ቡድኖቹ ጠንካራ የምድብ ጨዋታዎችን በማካሄድ ላይ ሲሆኑ ወደ ጥሎ ማለፍ ለመቀላቀል ጥረት በማድረግ ላይም ናቸው። ወሳኝ ድሎችን ለማስመዝገብ እና በውድድሩ የበለጠ ግስጋሴ ለማድረግ የሚያሳዩት እንቅስቃሴም በተጠባቂነቱ ቀጥሏል። በቀጣይ ከእያንዳንዱ ምድብ የሚያልፉ ቡድኖች የጥሎ ማለፍ ውድድራቸውን የሚያደርጉ ይሆናል።

በዚህም በ2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ የሚሳተፉ አራት ክለቦች ይለዩበታል። እስከ አሁን በሁሉም ምድቦች በተደረጉ ጨዋታዎች የተሻሉ እንቅስቃሴዎችና ተመጣጣኝ ፉክክሮች ተደርገዋል። በጎሎች የታጀቡና ለተመልካች የማይሰለቹ ጨዋታዎች ተመልካቹን ይበልጥ ጉጉት እንዲያድርበት አድርገዋል፡፡ ቡድኖቹ አብዛኞቹን የምድብ ጨዋታቸውን ያደረጉ ሲሆን ጥሎ ማለፉን የሚቀላቀሉትም ከወዲሁ እየተለዩ ይገኛሉ።

ሌላኛው የኢትዮጵያ ሴቶች የክልል ክለቦች ቻምፒዮና በተመሳሳይ በሀዋሳ ከተማ አርቴፊሻል ሜዳ እየተካሄደ ነው። ዘጠኝ ክለቦች በሁለት ምድብ ተደልድለው ውድድራቸውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የሴቶቹ ውድድር ከተጀመረ አንድ ሳምንት የሞላው ሲሆን የተለያዩ ቡድኖች በሚያደርጉት ፉክክር ያልተጠበቁ ውጤቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ ቢሾፍቱ ከተማ፣ ኤግልስ ዲላ፣ አምቦ ጎል ፕሮጀክት፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ እና ደብረማርቆስ በምድብ አንድ ሲደለደሉ ሰሌክት ኮሌጅ፣ ሲዳማ ፓይለት ፕሮጀክት፣ ገበዝ ማርያም ከተማና ጉለሌ ክፍለ ከተማ በምድብ ሁለት ተደልድለው ውድድራቸውን በማድረግ ላይ የሚገኙ ቡድኖች ናቸው። በውድድሩ ላይ አንደኛና ሁለተኛ የሚወጡ ክለቦች በቀጣይ በ2016 ዓም የሚካሄደውን የኢትዮጵያ ሴቶች ከፍተኛ ሊግ የሚቀላቀሉ ይሆናል። እንደ ወንዶቹ ሁሉ የሚደረገው ፉክክር ቀላል የሚይባል ሲሆን ቡድኖቹ እርስበርስ በሚያደርጉት ግንኙነት ጠባብ በሆኑ ውጤቶች እየተሸናነፉ ቀጥለዋል።

ውድድሮቹ ዛሬም በወንዶችና በሴቶች በተለያዩ ሜዳዎች ቀጥለው የሚካሄዱ ሲሆን ቀሪ ከምድቡ የሚያልፉ ክለቦች ተለይተው ይታወቃሉ። በወንዶች 16ቱን የሚቀላቀሉና በሴቶች ደግሞ ወደሚቀጥለው ዙር አላፊ ክለቦችን ለመለየት የሚደረገው ፍልሚያም ተጠባቂ ይሆናል።